# አማርኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስረኛ ክፍል






# ፲ኛ ክፍል

# አማርኛ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# ፩ኛ ክፍል

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


የአዘጋጆች

አናንያ ደርሶ አዱኛ

ደስታው አንዳርጌ አሸናፊ

ጌታሁን ስዩም በላቸው

ገምጋሚዎችና አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድኅን

ዳንኤል አስራት መንግስቴ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

ትንቢት ግርማ ሃይሉ

ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬህይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ

አቀማመጥ እና ስዕል

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

©የመጽሐፉ ሀጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣አስፈላጊውን በጀትበማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛሙያዊናአስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶዘላለም ሙላቱ፣

እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁ ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገፅ

መግቢያ ______ iv

ምዕራፍ አንድ (፩) ቋንቋና ማህበሰብ ______ 1

ምዕራፍ ሁለት (፪) ባህላዊ ጋብቻ ______ 14

ምዕራፍ ሶስት (፫) ሴቶች እና እድገት ______ 31

ምዕራፍ አራት (፬) በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ______ 48

ምዕራፍ አምስት (፭) የቋንቋ ለዛ ______ 66

ምዕራፍ ስድስት (፮) የታላላቆች ሚና ______ 85

ምዕራፍ ሰባት (፯) ረጅም ልቦለድ ______ 101

ምዕራፍ ስምንት (፰) ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ______ 118

ምዕራፍ ዘጠኝ (፱) ሥራ ፈጠራ ______ 137

አባሪዎች ______ 152

ዋቢ ጽሑፎች ______ 152

ሙዳዬ ቃላት ______ 154

ፊሊጣዊ አነጋገር ______ 155

የኢትዮጵያ ቁጥሮች ______ 157

የአማርኛ የፊደል ገበታ ______ 157

# መግቢያ

የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር፣ እንዲሁም የዕውቀት ዘርፍ የሆኑትን የስነ ጽሁፍ እና የስነልሳን ዕውቀትን ማዳበር ነው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት በመርሀ ትምህርቱ ላይ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር፣ እንዲሁም የቃላት እና የሰዋስው ዕውቀትን ለማጎልበት የሚያስችሉ ይዘቶች ተካተዋል፡፡

የቋንቋን ትምህርት ዋነኛ ዓላማዎች ለማሳካት ከሚያስችሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ እንዲለወጥ ወይም በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሚያችሉ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የመርሀ ትምህርት ማሻሻል ወይም ለውጥ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ይህ አዲስ የመማሪያ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ይህ የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ትኩረት የተሰጣቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ ግልጽና ሳቢ በሆነ መልኩ እንዲካተቱ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሁፎችን በመስጠት የተባበሩትን እያመሰገንን ስለመጽሀፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎች እና ከሌሎች አካላት የሚቀርበውን አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ (፩) ቋንቋና ማህበረሰብ

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁበኋላ:-

- መረጃዎችን በማዳመጥ ትወያያላችሁ።
- ውይይት በማድረግ የተገኘውን ውጤት በቃል ታንፀባርቃላችሁ።
- ሰፊ ርዕሰ-ጉዳይን የያዘ ጽሁፍ በማንበብ ተደራሲያንን ትለያላችሁ።
- በጽሁፋችሁ ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ትጠቀማላችሁ።
- ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- ጥምር ቃላት በመመስረት በዓረፍተነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

## ቋንቋ እና ጽሕፈት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ቀጥሎ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ዓውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ሀ. ቋንቋ ድምጻዊና አንደበታዊ የሰው ልጅ መግባቢያ ነው፡፡

ለ. ስለቋንቋ አጀማመር ሊቃውንት የተለያዩ መላምቶችን ሲሰነዝሩ ኖረዋል፡፡

ሐ. የስነ-ሰብ ተመራማሪዎች የቋንቋ ጥንተ አመጣጥን ጠቅለል አድርገው በሁለት ይከፍሉታል፡፡

መ. ቀለማዊ ሥርዓተ-ጽሕፈት የሳባ ፊደላትን ይጠቀማሉ፡፡

፪. ቋንቋና ጽሕፈት ስላላቸው ግንኙነት ግምታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

### የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎች

፩. መምህራችሁ ስለ ‹‹ቋንቋ እና ጽህፈት›› በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡ ሲነበብ በጥሞና እያዳመጣችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎችን እንዲሟሉ አድርጓቸው፡፡

ሀ. ____________ሰብአዊ የሆነ ፍጡር ሁሉ ሊግባባበት የሚችል መሳሪያ ነው፡፡

ለ. በጽህፈት ስርዓት የመጀመሪያው የአፃፃፍ ዘዴ________________ነው፡፡

ሐ. በ__________እና በ________መካከል ተፈጥሯዊ የሆነ ዝምድና የለም፡፡

መ. ለመማር ከባድ፣ ለመጠቀም ውስብስብ የሆነ የአፃፃፍ ስርዓት ____________ነው፡፡

ሠ. የቋንቋ የት መጣነት መላምቶች_____________እና_________ናቸው፡፡

## አዳምጦ መረዳት

፩. ቀጥሎ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፡፡ በየግላችሁ እያዳመጣችሁ አስፈላጊውን ማስታወሻ በመያዝ፤ በቡድን እየተነጋገራችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ንግግር ምንድን ነው?

ለ. የጽህፈት ዓይነቶች የሚባሉት እነማን ናቸው?

ሐ. አማርኛ ቋንቋ የሚከተለው የጽህፈት ስርዓት ምንድን ነው?

መ. በስዕላዊ የአጻጻፍ ስርዓትና በፊደላዊ የአጻጻፍ ስርዓት መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ፡፡

ሠ. ቁስ አካላውያን ስለ ቋንቋ አጀማመር የሚሰነዝሩትን መላምት ግለፁ፡፡

፪. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ማሰብ የምንችለው ሰብለ ቋንቋ ስላለን ነው አለች፡፡

ለ. ሀገሮች ኢትዮጵያ ብዙ ልሳነ ከሚባሉ ተጠቃሽ ነች፡፡

ሐ. የሚለዋወጥበት ቋንቋ ብቻ የተሰጠ፣ አንዱ ከሌላው ለሰው ልጅ ጋር ሀሳብ ታላቅ የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡

፫. የሥርዓተ ጽሕፈት የሽግግር ደረጃዎችን በቅደም ተከተል አስፍሩ፡፡ (ቃላዊ ሥርዓተ ጽህፈት ስዕላዊ ሥርዓተ ጽህፈት ፊደላዊ ሥርዓተ ጽህፈት ቀለማዊ ሥርዓተ ጽህፈት)

ሀ. --------------- ለ. --------------- ሐ.-------------- መ. -----------------

፬. ‹‹ኮረና›› በሚል ርዕስ ከተለያዩ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ያዳመጣችኋቸውን መረጃዎች ተጠቅማችሁ አንድ ድርሰት ጻፉ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ከሚከተሉት የመወያያ ሃሳቦች ውስጥ አንዱን በመምረጥ እና ከታች

የቀረበውን የውይይት መመሪያ መሰረት በማድረግ የቡድን ውይይት አድርጉ፡፡

ሀ. ሀገር ልትበለፅግ የምትችለው እኛ ዜጎች ምን ስናደርግ ነው?

ለ. ሀገር በቀል የሆኑ እውቀቶቻችን ምን ምን ናቸው?

## የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

### ውይይት ምንድን ነው?

ውይይት ማለት በማንኛውም አጋጣሚ የተፈጠረን ችግር ለመፍታት ወይም ደግሞ በአንድ አሰራር ላይ የነበረን መርህ ለመቀስቀስ እንዲሁም አዲስ ሃሳብ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ሲባል ጊዜና ቦታ ተዘጋጅቶለት፣ ርዕስ ተነድፎለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚከወን የሃሳብ ልውውጥ ነው፡፡ ውይይትን ከጭውውት እና ክርክር የተለየ የሚያደርገው ችግርን መፍታት ተቀዳሚ ዓላማው በማድረጉ ነው፡፡ አንድ ውይይት ስኬታማ እንዲሆን የሚከተሉትን ቅድመ ዝግጅትና አቀራረብ ሊከተል ይገባል፡፡

የውይይት ዝግጅት

- በውይይት አብረናቸው ልንሳተፍ የምንችልባቸውን አድማጮቻችን መለየት (ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ የህይወት ፍልስፍናቸውን ወዘተ...) ቀድመን መገንዘብ አለብን፡፡
- ርዕሰ ጉዳዩን ጠንቅቆ መረዳትና በታዳሚዎች የእድሜና የእውቀት ደረጃ ልክ የርዕሱን ጥልቀት መወሰን
- መረጃ ማሰባሰብና መለየት (ከባለሙያ፣ ከቤተ-መጽሐፍ፣ ከመገናኛ ብዙኀን)

የውይይት አቀራረብ

ውይይት በምንሳተፍበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡን ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ ማክበር
- ማስታወሻ መያዝ

- ተራን ጠብቆ ማቅረብ
- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- ሃሳብን በግልፅና በማስረጃ ማቅረብ
- የእኔ ሃሳብ ብቻ ይሁን አለማለት ወዘተ… የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ቃላዊ ዘገባ የሚለውን አጭር ማስታወሻ ከነበባችሁ በኋላ በአካባቢያችሁ የተከሰቱ ወቅታዊ ነገሮችን በመመልከት (ከመገናኛ ብዙሃን በመከታተል) አጭር ዘገባ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**ቃላዊ ዘገባ**

ቃላዊ ዘገባ ያየነውን፣ ያነበብነውን እና ያዳመጥነውን ጉዳይ በራሳችን የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር የሚቀርብበት ነው፡፡ይህን ተግባር በምንከውንበት ጊዜ

- በቂ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣
- አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን (የሰው፣ የቦታ፣ ስሞችን፣ ቀንና ሰዓቶችን፣ ቁጥሮች ወዘተ… ) በማስታወሻ በመያዝ በቃል ማቅረብ፣
- አድማጭ ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል መስጠት የሚሉት የተለመዱ የቃል ንግግር አቀራረብ መመሪያ ናቸው፡፡

በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር) (2007፡95) በሥነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

## ቋንቋና ሰው

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ቋንቋ እና ሰው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ቋንቋና ሰው ምን አይነት መስተጋብር ያላቸው ይመስላችኋል?

ሐ. ቋንቋ ባይኖር የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

መ. በዚህ ርዕስ ምን ምን ጉዳዮች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ግምታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ፡፡

ሠ. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ስለ ቋንቋ እና ሰው የሚያትቱ ናቸው፡፡ ስለፍቻቸው የምታውቁትን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ

በቃል ግለጹላቸው፡፡

ሀ. ቋንቋ ለ. ምርምር ሐ. ሰው መ. ቃል አልባ ተግባቦት

## ቋንቋ እና ሰው

ቋንቋን ከሰው፣ ሰውንም ከቋንቋ፣ አንዱ ከአንዱ ለይቶ ለመናገርም ሆነ ለማሰብ በፍጹም አዳጋች ይሆናል፡፡ ስለ ስብእናው፣ ስለ ማህበራዊ ግንኙነቱ፣ ስለአመለካከቱ ስለ ባህሉ ወዘተ… ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ለመከራከርም ሆነ ‹‹ለመስበክ›› የቋንቋው መኖር ግድ ነው፡፡ የቋንቋው መኖር በግዴታ መፈረጁም ለሰው ልጅ ህልውና እጅግ አስፈላጊ በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ ‹‹የሰው ልጅ የመግባቢያ ቋንቋ ባይኖረውስ? ያለ ቋንቋ መኖር አይቻለውም?›› ይህ ጥያቄ በዘመናት ውስጥ አከራካሪ መሆን ብቻ ሳይሆን ከትናት እስከ ዛሬ ምርምር እየተደረገበት ያለ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ጥያቄው ሁሉንም ሰው በጋራ የሚያግባባ ዓለምአቀፋዊ ምላሽ ያልተገኘለት ‹‹ድፍን እንቁላል›› ይሉት ዓይነት የምርምር አጀንዳ እንደሆነ መቀጠሉም ለዚህ ነው፡፡ የሰው ልጅ ግን በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ‹‹አጉራ ጠናኝ›› ብሎ ሳይረታ ዛሬም ድረስ ምርምሩን በስፋት እያከናወነ ይገኛል፡፡ የሰው ልጅና የቋንቋን ቁርኝነት በተመለከተ ሁለት ማሳያ የሆኑ ታሪኮችን እናንሳ፡፡

ተማሪዎች እስኪ ንባባችሁን ገታ አድርጋችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

ሀ. እስካሁን ያነበባችሁትን ምን ያህል ተገንዝባችኋል?

ለ. ሁለቱ ታሪኮች ሊያነሱ የሚችሉትን ሃሳብ በማጤን ግምታችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው?

## ታሪክ አንድ

በምርምር ዘርፍ ከፍተኛ ፍላጎት ያለው የቀድሞው ጀርመን መራሔ መንግስት ንጉሰ ነገስት ዳግማዊ ፍሬዴሪክ (እ.ኤ.አ ፲፩፻፺፰-፲፪፻፶ ) ዓ.ም የነበረው ከተወለዱ የሳምንት ዕድሜ ያልሞላቸው ህጻናትን ወደ ቤተ-መንግስት

በማስገባት ያለምንም ጣልቃ ገብነት በተፈጠሮ ሂደት ብቻ አፋቸውን እንዲፈቱ ሞክረውባቸው ነበር፡፡

ለህጻናቱ ሞግዚቶችም ምግብን እና ሌሎችን ማቅረብ እንዳለባቸው ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ እንዲሁም በቃል አልባ ተግባቦት (Non Verbal Communcation) ዘዴ ከህጻናት ጋር ለመግባባት እንዳይሞክሩ የሚያግድ ትዕዛዝም ሰጥተው ነበር፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ ግን ውጤቱ መና መቅረቱ ይፋ ሆነ፡፡ ምክንያቱም ህጻናቱ ሞቱ፡፡ ለምን ለሚለው ደግሞ ‹‹ማንኛውም ህጻን (ሰው) ለመኖር የሚያስፈልጉት መሰረታዊ ነገሮች ቢሟላለትም ያለ መግባቢያ ቋንቋ፣ ያለፍቅር ቃል፣ ያለ አፍቃሪ ጠረንና እሹሩሩ ለብቻው ተዘግቶበት እንዲኖር ቢፍርድበት መኖር አይቻልም፡፡›› የሚል ሆኗል፡፡ ስብእናው ያለ መግባቢያ ቋንቋ  ወይም ያለ ቃል አልባ ግንኙነት እንዲኖር አይፍቅድለትም፡፡

## ታሪክ ሁለት

አምስት ሰዎች ሽልማት ለሚያስገኝ የዝምታ ውድድር ተመርጠው ጸጥታ በሰፈነበት ክፍል ውስጥ አብረው እንዲቆዩ ተዘጋባቸው፡፡ በቆይታው ወቅት እርስ በርስም ሆነ አንዱ ከሌላው ጋር በምንም ሁኔታ እንዳይነጋገሩና በየትኛውም ዓይነት የቃል አልባ ግንኙነት እንዳይግባቡ ጥብቅ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

አንደኛ የወጣው ሰው በዝምታ እንደጸና ሳይናገር የቆየው ለስምንት ቀናት ብቻ ሲሆን ሦስቱ ያለ ንግግር የቆዩት  ለሁለት ቀናት ነበር፡፡ ሌላኛው ሰው የቆየው ለአንድ ሰዓት ያህል ብቻ ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት ተጠቃሽ ታሪኮች የሚያስረዳን ጤናማ ሰው ከብጤው የሰው ልጅ ጋር ወይንም ከፈጣሪው ጋር፣ አልያም ከየትኛውም ፍጡር ጋር በንግግርም ሆነ በቃል አልባ ግንኙነት ከመግባባት ቢታቀብ ውጤት አልባ ከመሆን እንደማይዘል አስረግጦ ያስታውሰናል፡፡

(ጌታቸው በለጠ የጥበባት ጉባኤ 2004 ፤ 4-7 በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ)

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. የሰው ልጅ ስለ ስብእናው፣ ማህበራዊ ግንኙነቱ፣ አመለካከቱ፣ ባህሉ ወዘተ... ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ እንዲሁም ለመከራከር ቋንቋ አስፈላጊ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. ‹‹የቋንቋው መኖር በግዴታ መፈረጁም ለሰው ልጅ ህልውና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡›› በሚለው ሃሳብ ትስማማላችሁ? ወይስ አትስማሙም? በምክንያት አስደግፋችሁ መልሱ፡፡

ሐ. በታሪክ አንድና ሁለት መካከል ያለው የሃሳብ አንድነት እና ልዩነት ምንድን ነው?

መ. አንደኛ የወጣው ተወዳዳሪ ዝም ብሎ የቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነበር? ህጻናቱ የሞቱት በምን ምክንያት ነበር?

፪. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ጥንድ ጥንድ በመሆን ዓውዳዊ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኂላ ዓረፍተነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ብጤ ለ. ጻና ሐ. አፍቃሪ መ. ቃል አልባ ሠ. ጠረን

ረ. እሹሩሩ ሰ. መና ሸ. መስበክ ቀ. ዓለምአቀፍ በ. ስብእና

፫. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን እንዲሁም ስርዓተ ነጥቦችን ለይታችሁ አውጡ፡፡

፬. ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃል በመፈለግ ጻፉ፡፡

ሀ. ቁርሾ
ለ. መረን
ሐ. ነቁጥ
መ. ህቡዕ
ሠ. ጨረፍታ
ረ. ዚቀኛ
ሰ. ሀመልማል
ሸ. ምንዝር
ቀ. ነጻብራቅ
በ. እንቦቀቅላ

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. ቋንቋ እና ሰው ከሚለው ጽሁፍ የተረዳችሁትን በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡ በምትጽፉበት ጊዜ አያያዥ ቃላትን፣ ሥርዓተ ነጥብን እንዲሁም የሃሳብ

ፍሰቱ (ቅድም ተከተሉ) የጠበቀ መሆን መቻል እንዳለበት እንዳትዘነጉ፡፡

፪. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የአንቀጽ ባህርያትን የጠበቁ ናቸው፡፡ ነገር ግን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው አልተቀመጡም፤ ስለሆነም ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ንጉስ እንኳን ቢመጣ ምግብ ላይ አንነሳም፡፡
2. እህሉን በአክብሮትና በፀጥታ እንበላዋለን፡፡
3. ሲሉ አባቶች ይመክራሉ፡፡
4. ገበታ ክቡር ነው፡፡
5. ምግብ እየበላን እያለ ማንም ሰው ቢመጣ እንብላ እንለዋለን እንጂአንነሳለትም፡፡
6. ተቀምጠን እያለ ማንም ሰው ቢመጣ በከበሬታ ተነስተን ኖር ብለን አንቀበለውም፡፡

፫. ገላጭ ቃላትን እና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም የመጣችሁበትን ሰፈር ‹‹ሰፈሬ›› በሚል ርዕስ ገላጭ በሆነ መንገድ ሁለት አንቀጽ ያለው አጭር ድርሰት ጻፉ፡፡ አንቀጻችሁን በምትጽፉበት ጊዜ የሚከተሉትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ተጠቀሟቸው፡፡

- ሰው ባገሩ ወይራ ነው፡፡
- ወፍ እንዳሃገሯ ትጮኻለች፡፡
- ውሻ በሰፈሩ ይጮኻል፡፡

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### የቃላት ሚና

፩. ቀጥሎ የቃላት ሚና የሚል ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ አምስት አምስት ገላጭ ቃላትን ከጽሁፍ ወይም ከመገናኛ ብዙኃን በመፈለግ (በማዳመጥ) አምጡ፡፡

**የቃላት ሚና**

ቃላት በቋንቋ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ቃል የሌለው ቋንቋ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡ እነዚህ ድምጾች በስርዓት ተቀናጅተው ቃልን የመመስረት ደረጃ ሲደርሱ

ለድርሰት ጽሁፍ ያላቸው ሚና ጉልህ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ገላጭ ቃላትን በመውሰድ ሰፈራችንን፣ አካለ ቁመናችንን፣ መልክዓ ምድርን ወዘተ … ገልጾ ምስል ከሳች በሆነ መልኩ መጻፍ ይቻላል፡፡

፪. በሚከተለው አጭር ጽሁፍ ውስጥ ሃሳብን የበለጠ ሊገልፁ የሚችሉ ቃላት ተካተዋል፡፡ በመሆኑም ገላጭ ቃላት የምትሏቸውን ለይታችሁ አውጡ፡፡

… ዶ/ር ደስታ ይባላል፡፡ ቀጥ ብሎ የተሰደረ አፍንጫውና ጎላጎላ ያሉ ዓይኖቹ ቀይዳማ ፊቱ ግርማን አላብሰውታል፡፡ ተክለ ሰውነቱ ረዘም ያለ ሆኖ ደልዳላ ነው፡፡ የእጅና የእግር ጡንቻዎቹ በትክክል መስመራቸውን ይዘው የፈረጠሙ ናቸው፡፡ ከደረቱ ወጣ ያለ ሆኖ፤ ሆዱ ከጀርባው ሊጣበቅ ትንሽ ነው የሚቀረው፡፡ (ዳዊት ወንድማገኝ ፣ 209፡1)

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

### ጥምር ቃላት

ጥምር ቃላት ሁለት ሊጣመሩ የሚችሉ የተለያዩ ቃላት ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት በተናጠል የተለያየ ፍቺ ከሚሰጡት በተጨማሪ ሌላ አዲስ ፍቺ ወይም የነበረውን የተናጠል ፍቺ የበለጠ የሚያጠናክሩ ቃላት ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሀ. ቤት + መጽሐፍ = ቤተ-መጽሐፍ

ለ. ህግ + መንግስት = ህገ-መንግስት

ሐ. ወጥቶ + አደር = ወታደር

መ. ወዝ + አደር = ወዛደር

ጥምር ቃላት አንዳንድ ጊዜ በንዑስ ጭረት(ንዑስ ሰረዝ) አንዳንዴ ደግሞ ያለ ስርዓተ ነጠብ የሚጣመሩበት ጊዜ አለ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለት የተለያዩ ተጣማሪ ቃላት ሲጣመሩ ጥምርነታቸውን ረስተው አንድ ቃል የሚመስሉበት አጋጣሚ አለ፡፡በምሳሌ ‹‹ሐ›› እና ‹‹መ›› የቀረቡት ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህ ጥምር ቃላት የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን ለመመስረት ጉልህ

ሚና አላቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሀ. ኢትዮጵያ የራሷን ህገ-መንግስት ቀርጻ መተዳደር ከጀመረች በርካታ ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡

ለ. ወዛደር ለሀገር ግንባታ የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡

፩. በሚከተለው ሳጥን ውስጥ ተጣማሪ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ይገኛሉ፤በመሆኑም ተጣምረው ትክክለኛ ፍቺ ሊያስገኙ የሚችሉ ቃላትን መስርቱ፡፡

ለምሳሌ፡- ዓለም አቀፍ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወፍ | አቀፍ | ምድር | ሥርዓት | ዘራሽ |
| ወዶ | ማር | ዓመት | መልካ | |
| ግብ | ገብ | ምህረት | ዓለም | ሥነ |

፪. ከላይ በመሰረታችኋቸው ጥምር ቃላት በአምስቱ ሁለት ሁለት ዓረፍተነገር ስሩባቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ዓለምዓቀፍ ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ዓለምአቀፍ ዲፕሎማሲዎች መቀመጫ ናት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቋንቋና ሰው ያላቸውን መስተጋብር እንዲሁም የሰው ልጅ ያለ መግባቢያና ቋንቋ የመኖር ህልውናው አደጋ ውስጥ እንደሚገባ አመላካች የሆኑ የተለያዩ ሁለት አስተማሪ ታሪኮችን ተመልክታችኋል። ቋንቋ የሰው ልጅ ስሜቱን፣ ሃዘኑንና ደስታውን፣ ማህበራዊ ግንኙነቱን፣ ሰዋዊነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ባህሉን ወዘተ...ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ለመከራከርም ሆነ ለማስተማር የቋንቋው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተገንዝባችኋል።

ስለ ቃላት ሚና በተለይም ደግሞ ቃላት በድርሰት ውስጥ ያላቸውን ሚና ተመልክተናል። ገላጭ ቃላት ተጠቅመን መልካዓ ምድርን፣ ቁመናንና ማንኛውንም የሚገለጹ ነገሮች መጻፍ እንደምንችል ተመልክታችኋል።

በተጨማሪም ስለጥምር ቃላት አመሰራረትና ሲመሰረቱ ምን እንደሚመስሉ ተገንዝባችኋል። ጥምር ቃላት በንዑስ ጭረት ወይም ያለ ንዑስ ጨረት ይመሰረታሉ። በእነዚህም ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዴት እንደሚመሰረት ተረድታችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ቋንቋ በሰው ልጆች ወይስ የሰው ልጆች በቋንቋ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ? የራሳችሁን ግላዊ አመለካከት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

፪. ቃል አልባ መግባቢያ መንገዶች የሚባሉትን በመዘርዘር ለመምህራችሁ ግለጹ።

፫. ከሚከተሉት ሁለት የድርሰት መጻፊያ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ገላጭ ቃላትን በመጠቀም ባለ ሁለት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. የኔዋ ሞናሊዛ　　　　ለ. ለምለሚቷ ሀገሬ

፬. በሚከተሉት ጥምር ቃላት ፍቻቸውን የሚገልጽ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ሀ. በትረ መንግስት　　　　ለ. አመለቢስ

ሐ. ቀዶ ጥገና　　　　መ. ሥነ-ዘዴ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለቋንቋ እና ሰው ምንነት በቃል እና በጽሁፍ መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን መሰረት በማድረግ መወያየት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የቃል ዘገባ አቀራረብን መመሪያ ተከትየ ያነበብኩትንና የተወያየሁበትን በቃል ማቅረብ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ቋንቋ እና ሰው ያላቸውን መስተጋብር ለጓደኞቼ በቃል መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የቃላትን ሚና በመረዳት ገላጭ ቃላትን ተጠቅሜ አንድን ነገር መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7. | ሁለት ሊጣመሩ የሚችሉ ቃላትን በማጣመር ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት (፪) ባህላዊ ጋብቻ

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች :-

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሌሎችን ንግግር በማዳመጥ ግብረ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- የጽሁፍን ሀሳብ አገናዝባችሁ ታነባላችሁ፡፡
- የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሀሳባችሁን በፅሁፍ ትገልጻላችሁ፡፡
- ትምህርታዊ እና ቴክኒካዊ ቃላትን በጽሁፍ እና በንግግር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- አስረጅ፣ መጠይቃዊ እና ትዕዛዛዊ ዓ.ነገሮችን በጽሁፋችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

## የተቋረጠው ጋብቻ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን እየተወያያችሁ የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

ሀ. ባህላዊ ጋብቻ ማለት ምን ማለትነው?ጋብቻ ሊቋረጥባቸው የሚችሉ ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

ለ. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ‹‹የተቋረጠው ጋብቻ›› በሚል ርዕስ ከቀረበ ምንባብ ውስጥ የወጡ ናቸው፡፡ ፍቻቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ነገረ ፈጅ
ለ. ሲቃ
ሐ. አንኮራፉ
መ. አምቻነት
ሠ. መልከ ቀና
ረ. ባለጋሻ

ሐ. መምህራችሁ ከፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ ውስጥ ‹‹የተቋረጠው ጋብቻ›› በሚል የተቀነጨበ አንድ አጭር ጽሁፍ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተ ደግሞ ጽሁፉን በጥሞና አዳመጣችሁ፤ከታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡ በምታዳምጡበት ጊዜ ፍቻቸውን የማታውቋቸው አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟችሁ ማስታወሻ መያዝን አትዘንጉ፡፡

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. የፊታውራሪ አሰጌንና የሰብለ ወንጌልን ጋብቻ ደስ ብሏቸው የተቀበሉትን ሰዎች ዘርዝሩ፡፡

ለ. ጋብቻው የተቋረጠባቸውን ምክንያቶች በቃል ግለጹ፡፡

ሐ. ‹‹የተቋረጠው ጋብቻ›› በሚል ርዕስ የተነበበላችሁን ምንባብ አጠቃላይ መልዕክት በቡድን ከተነጋገራችሁበት በኋላ ለመምህራችሁ በቃል ግለጹላቸው፡፡

መ. ባህላዊ ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው? ከቤተሰቦቻችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቃችሁ በመምጣት ያገኛችሁትን መልስ በክፍል ውስጥ በየተራ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ቀጥሎ የክርክር ምንነት፣ አዘገጃጀትና አቀራረብን የሚመለከት ማብራሪያ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም ማብራሪያውን በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ከቀረቡላችሁ የመከራከሪያ ርዕሶች መካከል አንዱን ምረጡ። በመቀጠል መምህራችሁ በሚመሰርቱላችሁ ቡድን መሠረት ክርክር አድርጉ።

ሀ. የባህላዊ ጋብቻ ተጽእኖ ከወንዶችና ከሴቶች በየትኞቹ ላይ ጎልቶ ይታያል?

ለ. ባህላዊ ጋብቻ ከጥቅሙና ጉዳቱ የትኛው ይበልጣል?

ሐ. አርበኝነት የሚገለጸው በጦርነት በመሳተፍ ወይስ በሌላ ጉዳይ ነው?

### ክርክር

ክርክር በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል በአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተለያየ አቋምን በማራመድ የሚደረግ ሥርዓት ያለው እሰጣ ገባ ወይም የሃሳብ ሙግት ነው። ክርክር በተለያየ አጋጣሚ ሊከወን ይችላል። ለአብነት ያክል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ዕውቀት ለማግኘት ይከራከራሉ።
- ከሳሽና ተከሳሽ ፍትህ ለማግኘት በፍርድ ቤት ይከራከራሉ።
- ፖለቲከኞች ለመመረጥና ሃገር ለመምራት በመገናኛ ብዙኀን ይከራከራሉ። ወዘተ… ተከራካሪዎቹም ለማሸነፍ ዝግጅት ያደርጋሉ።

  በመሆኑም በክርክር አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጊዜ የሚነሱ ነጥቦችን ቀጥለን እንመለከታለን።

፩ የክርክር ዝግጅት

- በርዕሰ ጉዳያችን ዙሪያ መረጃ መሰብሰብ (ከቤተ-መጽሐፍ፣ ከባለሙያ.....)
- መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
- ክርክሩን ከማቅባችን በፊት ልምምድ ማድረግ፣
- ወደክርክር ከመቅረባችን በፊት (አለባበሳችንን፣ ንጽህናችንን እንዲሁም

የአሸናፊነት ሥነ-ልቦናን ይዘን መቅረብ መቻል) አለብን።

፪. የክርክር አቀራረብ

- አድማጭን በማመስገን የመከራከሪያ ርዕሳችንን ማስተዋወቅ፣
- ሃሳባችን በግልጽና በተረጋጋ መንፈስ በልበ ሙሉነት በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
- ሃሳባችን በተገቢው የአካል እንቅስቃሴ እያጀቡ ማቅረብ፣
- በሌላ ሃሳብ ላይ ያሉ ተከራካሪዎችን ሃሳብ በጽሞና በማዳመጥና ማስታወሻ መያዝ፣
- የምናቀርበው መረጃ የተከራካሪዎችን አቅም /ችሎታ/ ያገናዘበ መሆን
- ለክርክር የተሰጠን ጊዜ ማክበር እና በአግባቡ መጠቀም፣
- ከርዕሳችን እንዳንወጣ መጠንቀቅ፣
- በመጨረሻም አመስግነን ሃሳባችንን መቋጨት መቻል አለብን።

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

## የየም ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የምታውቋቸው የጋብቻ ዓይነቶች ስንት ይመስሏችኋል? ስማቸውን ግለፁ።

፪. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ‹‹የየም ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ›› በሚለው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ስለፍቻቸው የምታውቁትን በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ሀ. ስብጥር ለ. ጥምር ሐ. ዕደ-ጥበብ መ. አጃቢ

፫. ቀጥሎ የየም ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ የሚል ምንባብ ቀርቦላችኋል። በመሆኑም ቡድን ከመሰረታችሁ በኋላ በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ ግምታችሁን ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ።

## የየም ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ



የየም ብሔረሰብ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በዋናነት በልዩ ወረዳው ውስጥ በሚገኙ 1 የገጠርና 2 የከተማ ቀበሌዎች የሚኖር ሲሆን፤ በጉራጌና በሃድያ ዞኖች ውስጥም ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር በስብጥር ይኖራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በርካታ የብሄረሰቡ አባላት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ውስጥም ይኖራሉ፡፡ የብሄረሰቡ ዋነኛ የኢኮኖሚ መስረት ጥምር ግብርና ሲሆን እንሰት፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ አተር፣ አደንጓሬ፣ ምስር፣ ኮክ እና ቦይና ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከእርሻ ስራው ጎን ለጎን የከብት እርባታና የእደጥበብ ስራዎችንም ያከናውናሉ፡፡

የብሄረሰቡ አፍ መፍቻ ቋንቋ ‹‹ የምሳ ›› ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በምስራቅ ኦሚዋ

ቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ በድምቀት ከሚከናወኑ ስርዓቶች አንዱ የጋብቻ ስርዓት ነው፡፡ በብሄረሰቡ አምስት ዓይነት የጋብቻ ዓይነቶች አሉ፡፡ በቤተሰብ የሚፈጸም ጋብቻ (ዛታግሩ)፣ ድንገተኛ ጋብቻ (ራራግሩ)፣ የጠለፋ ጋብቻ (ቦአገሩ)፣ በደላላ የሚፈጸም ጋብቻ (ዘክኛ) ወይም (ዛካግሩ) እና የፍቅር ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ (ሹኖግሩ) በመባል ይታወቃሉ፡፡

*ተማሪዎች ማንበባችሁን ገታ አድርጉና እስካሁን በአነበባችሁት ጽሁፍ ያገኛችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ለመምህራችሁ ግለጹላቸው፡፡ ቀጥሎ ምንባቡ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ግምታችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡*

‹‹ዛታግሩ›› ሁለቱ ተጋቢዎች ሳይተዋወቁ በወላጆቻቸው መልካም ፍቃድ /ስምምነት/ ብቻ የሚፈጸም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ ‹‹ራራግሩ›› ደግሞ ሳይታሰብ በድንገት የሚፈጸም ጋብቻ ሲሆን፣ ልጆቹም ሆኑ የልጅቷ ወላጆች ስለጋብቻው አንዳች ዕውቀት ሳይኖራቸው ወይም ሳይሰሙ አግቢው ጎረምሳ ከቤቱ ደግሶ ፈረሱን ጭኖና አጃቢ አስከትሎ ሽማግሌ በመያዝ በድንገት ወደ ልጅቷ ቤት ሄዶ በደጅ በመገኘት የሚፈጸም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጋብቻ ተቀባይነት ባያገኝም እንኳን የሚከፈለው የጥሎሽ መጠን ከተለመደው መጠን ከፍ ይላል፡፡ ‹‹ዛካግሩ›› በሶስተኛ ወገን አገናኝነት በሁለት ጥንዶች መካከል የሚፈጸም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የማግባባት ተግባር የሚፈጸመው በሴቶች አማካኝነት ሲሆን፤ አግባቢዋም ይህንን የምታደርገው ከአግቢው የገንዘብ ወይም የሌላ ነገር ጥቅም ለማግኘት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ጥቅማጥቅሙን ለማግኘት ስትልም ወንዱ ለከጀላት ሴት የተለያዩ የማግባቢያ ስልቶችን ተጠቅማ ጋብቻ እንድትፈጽም ታደርጋለች፡፡ ይህ አይነቱ ጋብቻ ባብዛኛው ተፈጻሚ የሚሆነው በተለያየ ምክንያት ባሎቻቸውን ፈትተው ወይም በሞት ተነጥቀው በተቀመጡት ሴቶች ላይ ሲሆን አልፎ አልፎ ባላገቡ ሴቶች ላይም ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡

‹‹ሹኖ ግሩ›› ደግሞ በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ ሲሆን ሁለቱ ወጣቶች ከወላጆቻቸው ዕውቅና ውጭ በድብቅ ፍቅር ጀምረው በድንገት ልጅቷ ከጸነሰችሁለቱምጥንዶች በአንድ ላይ ለመኖር ሲሉ የሚፈጽሙትጋብቻነው:: ከላይ ከተጠቀሱት የጋብቻ ዓይነቶች መካከል ከተወሰኑት በስተቀር አብዛኞቹ በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ ሲደረጉ አይስተዋልም:: በብሄረሰቡ የጋብቻ ዕድሜ ለሴት ልጅ ፲፰ ዓመት ሲሆን፤ ለወንድ ልጅ ደግሞ ! ዓመት ነው:: ወንዶች ከ ፲፭ ዓመት እስከ! ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገረዙ ሲሆን፣ የሴት ልጅ ግርዛት ግን በብሄረሰቡ ዘንድ የተለመደ አይደለም::

(ዳግማይ ነቅዓጥበብ፣ አዲስ ፲፰፻፹፱፣ 2007::)

## አንብቦ መረዳት

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል የሆኑትን ‹‹እውነት›› ስህተት የሆኑትን ‹‹ሀሰት›› በማለት ከነምክንያታችሁ በጽሁፍ መልሱ::

ሀ. የየም ብሄረሰብ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ምንጩ ግብርና ሲሆን ጎን ለጎን የአደን ስራዎችንም ያከናውናሉ::

ለ. በቤተሰብ የሚፈፀም ጋብቻ በተጋቢዎቹ ስምምነት የሚፈፀም የጋብቻ ዓይነት ነው::

ሐ. አብዛኞቹ የየም የጋብቻ ዓይነቶች አሁን ላይ ተግባራዊ ሲደረጉ ይታያሉ::

መ. በደላላ የሚፈፀም ጋብቻ ብዙውን ጊዜ የማግባባት ተግባሩ የሚቋጨው በሴቶች በኩል ነው::

ሠ. በየም ብሄረሰብ ጋብቻ የሚፈፀመው ለወንድ ልጅ በ፲፰ ዓመት ሲሆን ለሴት ልጅ ደግሞ በ፲፭ ዓመት ነው::

፪. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መነሻ በማድረግ የቀረቡ ናቸው:: ጥያቄዎችን በቡድን እየተወያያችሁ በቃል መልሱ::

ሀ. የየም ብሔረሰብ በወረዳው ውስጥ ከየትኞቹ ብሔረሰቦች ጋር ተሰባጥሮ ይኖራል?

ለ. ‹‹ዛካግሩ በሶስተኛ ወገን አገናኝነት በሁለት ጥንዶች መካከል የሚፈጸም ጋብቻ አይነት ነው::›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሐ. ‹‹የብሔረሰቡ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረታቸው ጥምር ግብርና ነው::
›› ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?

መ. የየም ብሔረሰብ አፍ መፍቻ ቋንቋ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሠ. ድንገተኛ ጋብቻ በየም ባህል ተቀባይነት የሌለው ለምንድን ነው?

፫. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ የሆኑትን በ ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተፈፃሚ | ሀ. ዘዴ |
| 2. ጥሎሽ | ለ. አገናኝ |
| 3. ስልት | ሐ. ፈለገ |
| 4. ከጀለ | መ. ተግባራዊ |
| 5. ደላላ | ሠ. ስጦታ |
| | ረ. መላሽ |

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

### የድርሰት ክፍሎች

ድርሰት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን አካቶ ይይዛል:: እነዚህም መግቢያ፣ ሐተታ እና መደምደሚያ ናቸው::

ሀ. መግቢያ:- ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ ቀድመን የምንጽፈው ተግባር መግቢያ ነው:: መግቢያ ድርሰታችን ስለምን እንደሚተነትን ለአንባቢ የምንነግርብት የደርሰት ክፍል ነው::

ለ. ሐተታ:- ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ በመግቢያ ላይ የሰፈሩ ሃሳቦች በዝርዝር የምናቀርበት ነው:: በዚህ ድርሰት ክፍል የርዕሰ ጉዳያችን ዋና ሃሳብ የሚሰፍርበት ክፍል ነው::

ሐ. መደምደሚያ:- ከመግቢያው አንስተን እስከ ሐተታ ድርሰት ያለውን ሃሳብ ጠቅለል አድርገን የምናሰፍርበት ነው::

(ደበበ ኃይለጊዮርጊስ ፣ 2012:298)

፬. ቀጥሎ አንድ አንቀጽ ቀርቦላችኋል:: በአንቀጹ ውስጡ ሶስቱ የድርሰት ክፍሎችን ይገኛሉ:: እነዚህን ሶስት የድርሰት ክፍሎች ነጣጥላችሁ በደተራችሁ

ጻፉ፡፡

የአውራ አምባ ማኅበረሰብ አባላት የጋራ ፍልስፍና፣ የህይወት ዘይቤና የአኗኗር ዘዴ ከአብዛኞቹ የሀገራችን ማኅበረሰቦች አቋም የተለየ ይመስላል፡፡ ማህበረሰቡ ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚለይባቸውንም ሆነ የሚመሳሰልባቸውን ልምምዶቹን የሚገልጸው በተግባር ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ የጋራ መግባቢያ በሆነው የአካባቢ ቋንቋ ፣ ማህበረሰቡ በተለማመደው ዘዬና የቃል አልባ ግንኙነት ጭምር ነው፡፡ በቋንቋው ራሱንና አካባቢውን ይገልጽበታል፤ ልምዱንና ወጉን ያስጠብቅበታል፤ ሀዘን ደስታውንም ይገልጽበታል፡፡ የመግባቢያ ቋንቋው የማህበረሰቡን እውነታ ለመግለጽ ብቃት መኖር ብቻ ሳይሆን የፍልስፍናውንና የእምነቱን ዕሴት ለመሸከምም አቅም አለው፡፡የማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ጥንካሬ የተመሰረተው በቋንቋው ላይ ሲሆን የማህበረሰቡ መታወቂያና መለያ የሆኑት ባህሎች፣ ልማዶች፣ ወግና ስርዓቱንም ከቋንቋው ውጭ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡

፪. ቀጥሎ ከተሰጧችሁ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ሶስቱን የድርሰት ክፍሎች (መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ) የያዘ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ሀ. ኮሮና

ለ. ትምህርት ቤቱ

ሐ. በጎ ስነ-ምግባር

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### የቃላት አጠቃቀም

፩. በፅሑፋችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት አንባቢያችን ሀሳባችንን እንዲረዳልን ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም በአንድ ቋንቋ ውስጥ ተዘውታሪ /የተለመዱ/፣ ሙያዊ፣ የመሳሰሉትን ቃላት ልንጠቀም እንችላለን፡፡

- ተዘውታሪ ቃላት፡- ተዘውታሪ ቃላት የሚባሉት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በስፋት የሚታወቁና በዕለት ከዕለት የምንገለገልባቸው ቃላት ናቸው፡፡

  ምሳሌ፡- የሰላም ቃላት

- ሙያዊ ቃላት፡- የሚባሉት በተመሳሳይ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያውቋቸውና የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል በግልጽ

የማያውቃቸው ቃላት ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- የህክምና ቃላት

፪. ቃላትን እያዋቀርን ዓረፍተ ነገር በምንመሰርትበት ጊዜ የቃላት ድግግሞሽ፣ ድረታ፣ የተሰለቹ ቃላት፣ የተውሶ ቃላትና አገላለጽ መጠቀም የለብንም፡፡

አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ፡- አንድን ቃል ያለ ዓላማ በዓረፍተነገር ውስጥ መደጋገም ቃላትን እንደማባከን ይቆጠራል፤ሃሳብን ያደበዝዛል፤ ውበት ይቀንሳል፤ መልዕክቱ በቀጥታ እንዳይተላለፍ እንቅፋት ይሆናል፡፡

ምሳሌ፡- ‹‹ፍቅርን ያወቅሁት በእርሱ ነው፤ ህይወትን ያጣጣምኩት በእርሱ ነው፤ ተድላና ደስታዬን ያየሁት በእርሱ ነው፡፡›› በሚሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ አጽኦት ለመስጠት የተደጋገሙ ቃላት አሉ፡፡ ስለዚህ ድግግሞሹ ተገቢ ነው፡፡

የቃላት ድረታ፡- አንድ ቃል በራሱ የሚፈልገውን ትርጉም ማስተላለፍ እየተቻለ ሌላ ተጨማሪ ቃል ደርበን የምንጠቀምበት ከሆነ የቃላት ድረታ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- ራሴን አሞኝ ስለነበር ዲፐሮን መድሃኒት ውጬ ተኛሁ፡፡

በእስር ቤቱ ውስጥ ጽሁፎችን መጻፍ የሚያስቀጣ ነበር፡፡

በእነዚህ ምሳሌዎች እንደምንረዳው ዲፕሮንየሚለው ቃል የእንግሊዘኛ ቃል ቢሆንም …ዲፐሮን ውጬ ተኛሁ (…መድሃኒት ውጬ ተኛሁ፡፡) ማለት እየተቻለ ፤ ዓረፍተ ነገሮቹ ድረታን አስተናግደዋል፡፡ እንዲሁም … መጻፍ የሚያስቀጣ ነበር፡፡ ማለት እየተቻለ ጽሁፎችን መጻፍ የሚለው ድረታን ያመላክታል፡፡

የተሰለቹ ቃላት፡- ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የምንሰማቸው አገላለፆች ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት በአንድ ወቅት ማራኪነትን የተላበሱ አባባሎች የነበሩ፤ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ትኩስነታቸውንና ኃይላቸውን ያጡ ቃላት ወይም ሀረጋት ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-ውድ ወንድሜ የሰማይ ርቀቱን፣ የባህር ጥልቀቱን፣ የአሸዋ ብዛቱን፣ የከዋክብት ድምቀቱን ያህል እንደምን አለህ!

በቀረበው አገላለጽ በቀደመው ጊዜ ደብዳቤ ሲጻፍ የተለመደና ለዛ ያለው ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ አገላለጽ የተሰለቸ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

፩. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተደገሙ፣ የተሰለቹና የተደረቱ ቃላት ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በምሳሌው መሰረት ቃላትና ሃረጋቱን በሌሎች ቃላት በመተካት ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ

- በእግሩ ተራምዶ ደረሰብኝ፡፡
- ሲስተካል፡- ተራምዶ ደረሰብኝ፡፡
- አጉል ሱስን የመተውና እርግፍ አርጎ የመተው እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡
- ሲስተካከል፡- ሱስን እርግፍ አድርጎ የመተው እርምጃ ያስፈልጋል፡፡

1. በርዕሰ ከተማችን በአዲስ አበባ የመኖሪያ ቤት ችግር አለ፡፡
2. አርአያ መሆን ሲገባቸው አርኣያ አይሆኑም፡፡
3. በሀቅ ላይ የተመሰረተ እውነተኛ አባባል ነው፡፡
4. ስቃይ በርትቶብኝ እየተሰቃየሁ ቆየሁና ስቃዬን ልገልጽለት ፈልጌ አጎቴ ቤት በስንት ስቃይ ደረስኩ፡፡
5. የአባቴ እህት የሆነችው አክስቴ መጣች፡፡
6. ታላቁ ደራሲ በትናንትናው እለት ተቀብሮ ግብአተ መሬቱ ተፈጸመ፡፡
7. በአእምሮዬ የማስበውን ያወቀብኝ መስሎኝ ድንግጥ አልኩ፡፡

፪. በሚከተሉት ዓፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ሙያዊና ተዘውታሪ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ሀ. መሐመድ በቀዶ ጥገና ትናንት ተመረቀ፡፡

ለ. ቤቶች በሚገነቡበት ወቅት የውሃ ልካቸው ተጠብቆ መስራት አለባቸው፡፡

ሐ. ሰላምታ መለዋወጥ ከባህላችን አንዱ ነው፡፡

መ. መልካም ህይወት እንዲገጥማችሁ እመኝላችኋለሁ፡፡

፫. የሚከተለው አንቀጽ የተሟላ ሃሳብ ማስተላፍ አይችልም፡፡ የተሟላ ሀሳብ ማስተላለፍ የሚችለው ያሉት ክፍት ቦታዎች በተገቢ ቃላት ሲሟሉ ነው፡ ስለዚህ ከቃላቱ መካከል እየመረጣችሁ በክፍት ቦታዎች በማስገባት አንቀጹ የተሟላ ሃሳብ ማስተላለፍ እንዲችል አድርጉ፡፡ (ቃላቱ ለሚገቡበት ቦታ ተስማሚ

ቅርጽ እንዲይዙ ማድረጋችሁን አትዘንጉ።)

1. ቋጥኝ
2. ሜዳ፣ ፏፏቴ
3. አበባ
4. ሰማይና ምድሩ
5. ስኩየር
6. ምልክት

… ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ____________ (1) ቅርጽ እንደተዥጎረጎረ ብርድ ልብስ የተሸነሸነ አረንጓዴ ምድር ብቅ አለ፤ በአዝመራ የተንቆጠቆጠ ማሳ ____________ (2) የተሞሸረ ጋራ፣ በጅረት ጥበብ የተሰጣበት ____________ (3) የሚተፋ ቋጥኝ። የሀገሩ ሰማይ ለመሆኑ ሁሌም ማረጋገጫው ይሄ ነው፤ ከታች ያለውም የሀገሩ ምድር ለመሆኑ ሌላ ____________ (4) አላስፈለገውም የሀገሩ፣ ____________ (5) ከማንም ከሌላ ሀገር ሰማይና ምድር ጋር ተመሳስሎበት አያውቅም።

(ይስመዐከ ወርቁ፣ ዮቶድ፣ 2009:31)

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

የዓረፍተ ነገር ስልቶች የሚባሉትን በመዘርዘር ምሳሌ ስጡ።

የዓ.ነገር ስልቶች ዓረፍተ ነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር ጥያቄያዊ፣ ሀተታዊ፣ ትእዛዛዊና አጋናኝ ዓ.ነገር በመባል ይታወቃሉ።

ሀ. ሐተታዊ ዓ.ነገር፡- ስለ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት የሚያትትና መልዕክትን ማስተላለፍ ዓላማው አድርጎ የሚመሰረት ነው። ሐተታዊ ዓ.ነገር በውስጡ አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን ይይዛል።

አዎንታዊ ዓ.ነገር፡- በአዎንታ የሚነገር የዓረፍተ ነገር ስልት ነው።

ምሳሌ፡- ጓደኛዬ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት። እውቀት የማይሞት ሃብት ነው።

አሉታዊ ዓ.ነገር፡- በአሉታ ወይም በአፍራሽ የሚነገር የዓረፍተ ነገር ስልት ነው። በውስጡም አፍራሽ የሆኑ ቅጥያዎችን (አል-ም፣ አይ- ም፣ አን - ም) ወዘተ… ይይዛል።

ምሳሌ፡- ጎበዙ ተማሪ ዛሬ አልመጣም።
ጓደኛዬ የእግር ኳስ መጫወት አይወድም።

ለ. ጥያቄያዊ ዓ.ነገር፡- መጠይቃዊ ቃላትን ወይም የጥያቄ ምልክትን በመጠቀም

የሚመሰረት ሲሆን ምላሽ የሚያስፈልገው የዓ.ነገር ነው።

ምሳሌ፦ የኮሮና ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው የት ሀገር ነው?

ጓደኛሽ ነገ መምጣት ትችላለች?

ሐ. ትዕዛዛዊ ዓ.ነገር፦ አንድ ነገር እንዲከናወን ወይም እንዲፈጸም ሲባል በትዕዛዝ መልክ የሚቀርብ የዓ.ነገር ስልት ነው። ይህ ዓረፍተነገር በአራት ነጥብና በትዕምርተ አንክሮ ሊቀርብ ይችላል።

ምሳሌ፦ ነገ ሀገር ተረካቢ እንድትሆኑ በርትታችሁ ተማሩ!መልዕክቱን

በነገርኩሽ መሰረት አድርሽ!

መ. አጋናኝ ዓ.ነገር፦ ነገሮችን በማጋነን፣ በመገረም፣ በመደነቅ የሚያቀርብ ዓ.ነገር ሲሆን መደሰትን፣ መገረምን፣ መናደድና መሰል ስሜቶችን ያንፀባርቃል።

ምሳሌ፦ ዋው! ዛሬ ቀኑ ደስ ይላል።

እሰይ! እህቴ ነገ ከውጭ ሃገር ትመጣለች።

፩. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ሐተታዊ (አዎንታዊ፣ አሉታዊ)፣ ትእዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋናኝ እያላችሁ መልሷቸው።

ሀ. እኛ ሳናየው ጠላት ቀድሞ ገብቷል።

ለ. ዘምዘም ህይወቷን ሙሉ ለሃገሯ እየገበረች ነው።

ሐ. ትምህርት ለሃገር እድገት መሰረት ነው።

መ. የክብር እንግዳው ሳይመጣ ቀረ።

ሠ. መምህራችን መጽሐፍ ማምጣት እንዳለብን ነገሩን።

ረ. ከቢሮዬ በፍጥነት ውጣ!

ሰ. ኦ! ፈጣሪዬ ከዚህ ፈተና አውጣኝ።

ሸ. ወደ ኢትዮጵያ መቼ ትመለሳለህ?

፪. በሚከተሉት ቃላት ሐተታዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ጥያቄያዊና አጋናኝ ዓ.ነገሮችን መስርቱ።

ሀ. ፈለገ (ሐተታዊ)

ለ. ብሩህ (አጋናኝ)

ሠ. አመረቃ (ሐተታዊ)

ረ. ኩራት (አጋናኝ)

ሐ. ራእይ (ጥያቄያዊ) ሰ. ቆረጠ (ጥያቄያዊ)

መ. መሰረት (ትዕዛዛዊ) ሸ. አረንቋ (ሐተታዊ)

አዎንታዊ የሆኑ ሶስት ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ለውጧቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ‹‹ባህላዊ ጋብቻ›› በሚል ርዕስ ስለ ክርክር ምንነት፣ ዝግጅትና አቀራረብ ተምራችኋል፡፡ ስለሆነም ክርክር በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል በአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተለያየ አቋምን በማራመድ የሚደረግ የሃሳብ ሙግት ነው፡፡ የክርክር አዘገጃጀት እና አቀራረብ መመሪያ መሰረት አድርጋችሁም ክርክር አቅርባችኋል፡፡ የድርሰት ክፍሎችን ተምራችኋል፡፡ እነዚህም መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ሲሆኑ ክፍሎቹን ባካተተ መልኩ በተሰጣችሁ ርዕስ ድርሰት ጽፋችኋል፡፡

የቃላትን አውዳዊ ፍች በንግግርና በጽሁፍ ውስጥ ሰጥታችኋል፡፡ የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ ዘወትራዊና ሙያዊ ቃላትን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመለየት ጽፋችኋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰለቹ፣ የተደረቱና የተደጋገሙ ቃላትን በመለየት አስተካክላችሁ መጻፍ እንዳለባችሁ ተገንዝባችኋል፡፡ አንድን ቃል ያለ ዓላማ በዓረፍተነገር ውስጥ መደጋገም አስፈላጊ እንዳልሆነ፤ አንድ ቃል በራሱ የሚፈልገውን ትርጉም ማስተላለፍ እየተቻለ ሌላ ተጨማሪ ቃል ጨምረን መጠቀም እንደሌለባችሁና ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የምንሰማቸው አገላለጾች በሌላ ጊዜ ትኩስነታቸውን ስለሚያጡ ይህን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባጥ እንዳለባችሁ አይታችኋል፡፡ በመጨረሻም የዓረፍተ ነገር ስልቶችን በመለየት ሐተታዊ፣ ትእዛዛዊ፣ ጥያቄያዊና አጋናኝ ዓረፍተ ነገሮችን መስርታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ክርክር የሚያቀርብ ሰው ከሚተገብራቸው ነጥቦች መካከል አራቱን ጠቅሳችሁ አብራሩ፡፡

፪. በሚከተሉት የቃላት አጠቃቀሞች በራሳችሁ ሁለት ሁለት አረፍተ ነገሮችን ለእያንዳንዱ መስርቱ፡፡

ሀ. ሙያዊ ቃላት

ለ. ዘወትራዊ ቃላት

ሐ. አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ

መ. ድረታ

ሠ. የተሰለቹ ቃላት

፫. የሚከተሉትን የአረፍተ ነገር ስልቶች ተጠቅማችሁ ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ሀ. ጥዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

ለ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

ሐ. ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር

መ. አጋናኝ ዓረፍተ ነገር

፬. መግቢያ ፣ሀተታና መደምደሚያ ያለው ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አጭር ጽሁፉ ጻፉ፡፡

፭. በሚከተሉ ቃላት ዓረፍተ ነገር ከመሰረታችሁ በኋላ አውዳዊ ፊወቻቸውን ጻፉ፡፡

ሀ. ራደ

ለ. በላው

ሐ. አገደ

መ. ሰማ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ስለ ባህላዊ ጋብቻ የማውቃቸውን ለጓደኞቼ መናገር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ንግግሮችን በማዳመጥ ግብረ መልስ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን መሰረት በማድረግ በማንኛውም ርዕስ መከራከር እችላለሁ፡፡ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ። | | | |
| 5 | የጽሁፍን ሀሳብ አገናዝቤ አነባለሁ። | | | |
| 6 | የድርሰት ክፍሎችን መለየት እችላለሁ። | | | |
| 7. | የደርሰት ክፍሎች መሰረት አድርጌ በተሰጠኝ ርዕስ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ። | | | |
| 8 | በጽሁፍ ውስጥ ሙያዊና ዘወትራዊ ቃላትን መለየት እችላለሁ። | | | |
| 9. | የተሰለቹ ቃላት፣ የቃላት ድግግሞሽና ድረታ ለይቼ ማስተካከል እችላለሁ። | | | |
| ፲. | ዓረፍተ ነገር ስልቶችን በመለየት በተሰጡት ቃላት ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት (፫) ሴቶች እና እድገት

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሴቶች እና እድገት ዙሪያ የቀረቡ ሀሳቦችን አዳምጣችሁ የተናጋሪውን ሀሳብ ትገመግማላችሁ፡፡
- አንድን ምንባቡን አንብበው ተፈላጊውን ሀሳብ ታወጣላችሁ፡፡
- በሴቶችና እድገት ዙሪያ ቃለ መጠይቅ በማማድረግ ያገኛችሁትን ሀሳብ በቃል ታንጸባርቃላችሁ፡፡
- ለተሰጣችሁ ጽሁፍ በአንድ አንቀጽ ማጠቃለያ ትጽፋላችሁ፡፡
- ውስብስብ ዓርፍተ ነገሮችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በመመስረት ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

### ተመጣጣኝ ወግ ያላየው ወጋየሁ ንጋቱ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በሀገራችን ከምታውቋቸው ታዋቂ የጥበብ ሰዎች መካከል የተወሰኑትን ጥቀሱ፡፡

፪. ቀጥሎ መምህራችሁ ‹‹ተመጣጣኝ ወግ ያላየው ወጋየሁ ንጋቱ›› የሚል አንድ አጭር ጽሁፍ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡ ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት

ሀ. ከዚህ ርዕስ ምን ምን ነጥቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ግምታችሁን በየግላችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ወጋየሁ ንጋቱ የተባለውን ታላቅ ሰው በየትኛው ስራው ታስታውሱታላችሁ?

፫. መምህራችሁ ምንባቡን ሲያነቡላችሁ ማስታወሻ እየያዛችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በየግላችሁ ከሰራችሁ በኋላ በቡድን

ተወያዩባቸው፡፡ መልሳችሁንም ለመምህራችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

### አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. ወጋየሁ ንጋቱ ልጆች የሚከቡትና ዓይኖች የሚከተሉት ተወዳጅና ተፈቃሪ ልጅ የነበረው በምን ምክንያት ነበር?

ለ. ወጋየሁ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወነው ትያትር ምን የሚል ነበር?

ሐ. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ወጋየሁን በሙያው እንዲገፋበት ያበረታቱት የነበረው በምን ምክንያት ነው?

መ. ከወጋየሁ ታሪክ ምን እንደተማራችሁ በየግላችሁ አስረዱ፡፡

ሠ. ሴቶች በሀገር እድገት ላይ ስላበረከቷቸው የተለያዩ ተግባራት ከሚተላለፉ መገናኛ ብዙሃን (ቲቪ፣ ራዲዮ፣ ...ወዘተ.) በቤታችሁ ወይም ምቹ ሁኔታን በሚፈጥርላችሁ ቦታ ሆናችሁ አዳምጡ፡፡ ካዳመጣችሁ በኋላ

በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የተናጋሪዎቹን ሀሳብና አመለካከት በመገምገም በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. አጀንዳቸውን በሴቶች እድገት ላይ ያደረጉ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ ወ.ዘ.ተ) አዳምጡ፡፡ ስታዳምጡ የተናጋሪዎቹን መልዕክት፣ አመለካከትና ዝንባሌ በአግባቡ ከመረመራችሁ በኂላ የተረዳችሁትን በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፪. በአካባቢያችሁ ወደሚገኙ የህዝብ መገልገያ ተቋማት ቢሮ ኃላፊዎች በመሄድ ከታች የቀረበውን የቃለ መጠይቅ መመሪያ መሰረት አድርጋችሁ ቃለ መጠይቅ አድርጉ፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ እንድትችሉ የሚከተሉትን ነጥቦች ተግባር ላይ አውሉ፡፡

ሀ. አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት መረጃ ሊገኙባቸው የሚችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን አዘጋጁ (ጥያቄዎቻችሁ ስለመረጣችሁት ተቋም ጥሩ መረጃ የሚሰጡ መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡)

ለ. ስለተቋሙ መረጃ የሚሰጧችሁን ሶስት ሰዎች ምረጡ፡፡

ሐ. በጥያቄዎቻችሁ መሰረት የሰበሰባችኂቸውን መረጃዎች በጽሁፍ አዘጋጅታችሁ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለመምህራችሁና ለጓደኞቻሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**ቃለ-መጠይቅ**

ቃለ መጠይቅ ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ መረጃ የሚሰበሰብበት ሒደት ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ የተዋቀረ ወይም ያልተዋቀረ ሊሆን ይችላል፡፡ የተዋቀረ ቃለመጠይቅ በአቀራረብ ጊዜ የምንተገብራቸው ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### የቃለ መጠይቅ አቀራረብ

- ለቃለ መጠይቁ ዝግጁ በመሆናቸው ተጠያቂዎችን በቅድሚያ ማመስገንና ዓላማውን በአጭሩ ማስተዋወቅ፣
- የወዳጅነትና የመግባባት ስሜት መፍጠር፣

- ጥያቄዎችን በልበ ሙሉነት በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
- ትህትና ያልተለየው አቀራረብ ማሳየት (ግትርና ተሚጋች አለመሆን)
- አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ፣
- ዋና ዋና ሀሳቦችን እያዳመጡ ማስታዎሻ መያዝ፣
- በተጠያቂው ዘንድ ግልጽና ታማኝ ሆኖ መገኘት (የመዘገቡትን መረጃ ለተጠያቂው መልሶ ማሳየት)
- ሁኔታዎችን እዳስፈላጊነቱ ለመቀያየር ዝግጁነት ማሳየት
- ቃለ መጠይቁ ሲጠናቀቅ ተጠያቂውን ማመስገን የሚሉት በቃለ መጠይቅ፣ አቅርቦት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።

፫. ‹‹በአካባቢያችሁ በሚገኙ ማንኛውም ማህበራዊ መስተጋብሮች ላይ ሴቶችን ማሳተፍ ስላለው ጠቀሜታ ቃለ ምልልስ አድርጉ። ቃል ምልልሱን በክፍል ውስጥ ከማቅረባችሁ በፊት መለማመዳችሁንና ጠቃሚ ነጥቦችን ማንሳታችሁን አትዘንጉ።

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### እቴጌ ጣይቱ ብጡል

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የኢትዮጵያ ሴቶች ተሳትፎ በሀገር እድገት ላይ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ጥቀሱ።

ለ. በማንኛውም የሙያ መስክ ላይ ተሰማርተው አንቱታን ያተረፉ የሀገራችንን ሴቶች ተናገሩ።

ሐ. ቀጥሎ ‹‹እቴጌ ጣይቱ ብጡል›› በሚል የቀረበው ንባብ የሚያነሳቸው ነጥቦች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ንባባችሁን ስታነቡ እንግዳ የሆኑ ቃላት ካጋጠሟችሁ መዝግባችሁ በመያዝ ከንባብ በኋላ ተነጋገሩባቸው።



እቴጌ ጣይቱ ብጡል

እቴጌ ጣይቱ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፰፻፴፪ ዓ.ም. ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡል ኃ/ማሪያም እና ከእናታቸው ከወ/ሮ የውብዳር ደብረ ታቦር ከተማ ውስጥ ተወለዱ፡ አባታቸው የጎንደርና የወሎ፣ እናታቸው ደግሞ የጎጃም ተወላጅ ናቸው። ጣይቱ ለቤተሰባቸው ሶስተኛ ልጅ ናቸው። አባታቸው በጦርነት በመሞታቸው በ፲፫ ዓመታቸው ደብረ ታቦርን ለቀው ወደ እናታቸው ትውልድ ቦታ ወደ ጎጃም ሄዱ። ጎንደር እያሉ በማህደረ ማሪያም የጀመሩትን ትምህርታቸውን በጎጃም ደብረማዊ ደብር ቀጠሉበት። በዚህ ገዳም ውስጥ ንባብንና ጽሕፈትን፣ የግዕዝና የአማርኛ ቅኔ፣ በገና ድርደራንና የሰንጠረዥ ጨዋታን ተማሩ። ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በጥበብና በህይወት ፍልስፍና የላቀ ችሎታ እንዳላቸው እየታወቀ መጣ። ጣይቱ ደብረማዊ ገዳም እያሉም ወንድማቸው ራስ አሉላ ከሞቱ በኋላ ወደ ሸዋ መጡ።

አፄ ምኒልክ በ፲፰፻፸፬ ዓ.ም. የፋሲካን በዓል በባህር ዳር አቅራቢያ ሄደው

እንዳከበሩ በጣይቱ ብጡል እናት በወ/ሮ የውብዳር ቤት ውስጥ በአጋጣሚ ከጣይቱ ጋር ተጫጩ፡፡ በዚህም መሰረት ሚያዚያ ፳፭/፲፰፻፸፭ ዓ.ም. በአንኮበር ቤተ ክርስቲያን መድኃኒዓለም ተጋቡ፡፡ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓ.ም ጣይቱ ብጡል ‹‹እቴጌ›› ተብለው ተሰየሙ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስማቸው በመላው ሀገሪቱ ነገሠ፡፡ ከዚህ በኋላ እቴጌ ጣይቱ በፖለቲካ፣ በወታደራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና አጠቃላይ በሀገር ግንባታ ታላቅ ስራ የሰሩ የቆራጥነትና የአስተዋይነት ታሪክ ካላቸው ምርጥ ሴቶች መካከል አንዷ መሆን ቻሉ፡፡ አፄ ምኒልክ አዳዲስ ስልጣኔዎችንና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከውጪ ለማስገባት ቁርጠኛ አቋም ይዘው ሲሰሩ፣ ዋና አማካሪያቸውና አጋራቸው እቴጌ ጣይቱ ነበሩ፡፡

አፄ ምኒልክ ወደ ዘመቻ ሲንቀሳቀሱ የመንግስት አይንና ጆሮ ሆነው አገልግለዋል፡፤ ጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ኮራዶ ዞሊ ‹‹የዛሬይቱ ኢትዮጵያ›› በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ጣይቱ ሲጽፉ ‹‹ጣይቱ ቆንጆ ብቻ ሳይሆኑ ደስ የሚሉ ደማም እጅግ ብልህና ጀግና ናቸው፡፡›› ብሎ በአድናቆት ጽፏል፡፡ እቴጌ ጣይቱ ‹‹ብርሀን ዘ ኢትዮጵያ›› በሚል ቅጽል ስም መጠራት የጀመሩትም ከዚህ በኋላ ነው፡፡

ተማሪዎች! አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

እቴጌ ጣይቱ በፖለቲካው መስክ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ግንባር ቀደም በመሆን ውሳኔ በመስጠትና የአፄ ምኒልክ አማካሪ በመሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ አፄ ምኒልክ ጣይቱን ሳያማክሩ የሚወስኑት ምንም አይነት ውሳኔ አልነበረም፡፡ የፖለቲካ ህይወታቸው ይበልጥ ገኖ የወጣውም ሚያዚያ/፳፭ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. በአንቶኖሊና በምኒሊክ መካከል በተፈጠረው የውጫሌው ስምምነት ላይ ነበር፡፡ ስምምነቱ እንዳይፈረምና አገሪቱ አደጋ ውስጥ እንዳትገባ ብዙ ታግለዋል፡፡ ይህንን አስመልክቶ ለሕዝባቸው ሲናገሩ ‹‹እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም፤ ሆኖም ይህን ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ጥገኛ የሚያደርገውን ውል ከመቀበል ጦርነትን

እመርጣለሁ›› ብለው በምሬት ተናግረው ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት በራሳቸው የሚመራ ፴፻ እግረኛ ጦርና ፮፻ ፈረሰኛ አስከትለው ከባለቤታቸው ጎን በመሰለፍ የካቲት/፳፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ.ም አድዋ ላይ ጠላትን ድል አደረጉ፡ ከአድዋ ጦርነት በፊትም የኢጣሊያን ጋዜጠኞች ለእኚህ ጀግናና ሀይለኛ ሴት በዕትማቸው ያቀርቡ ነበር፡፡

ጣይቱ በአድዋ ጦርነት ጊዜም ብዙ ጀብድ ፈጽመዋል፡፡ ‹‹በባህር ከልሎ የሰጠንን አገራችንን የሚቀማ ጠላት መጥቶ እንዴት ዝም እንላለን›› በሚለው ወኔ ቀስቃሽ ንግግራቸው በሰራዊታቸው ተደግፈው እየተፎከረላቸውና እየተሞገሱ ወደ አድዋ ዘመቱ፡፡ ጦርነቱ ከመካሄዱ በፊትም በመቀሌና አካባቢው ሽምቆ የነበረውን የጠላት ሰራዊት ይጠቀምበት የነበረውን የውሃ ገንዳ በ፳፭ኪ.ሜ. ርቀት ላይ አስከብበው የጠላት ሰራዊት በውሃ ጥም እንዲሞትና በመጨረሻም ከምሽጉ ፈርጥጦ እንዲሸሽ ያደረጉትም እኝሁ ብልህ ሴት ናቸው፡፡ እንደተዋጊና የጦር መሪ ብቻ ሳይሆኑ የቆሰሉትን በማከም፣ የተራቡትን በመመገብ፣ የተጠሙትን በማጠጣትና የደከሙትን በማበረታታት ጦሩ በወኔ እንዲዋጋ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከጦርነቱ መልስም አባትና እናት የሌላቸውን ህጻናት በመንከባከብ፣ በማሳደግና በማስተማር ተግባር ላይ ተሰማርተው ነበር፡፡ ጣይቱ በመንፈሳዊ ህይወታቸውም በጣም ጠንካራና ለሌሎች አርዓያ የነበሩ ሴት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በስማቸው የመጀመሪያውን ሆቴል ጣይቱ ሆቴልን አሰርተዋል፡፡ ለአሁኗ አዲስ አበባ መቆርቆርና ስያሜ መሰረት ጥለውም አልፈዋል፡፡

እቴጌ ጣይቱ በመንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እያሉ የካቲት ፬/፲፱፻፲ ዓ.ም. በ፹፫ አመታቸው አረፉ፡፡ ከሞቱ ከ፶ ዓመት በኋላም ‹‹ታላቋ ንግስት›› በሚል የኢትዮጵያ ፖስታ ድርጅት በስማቸው ቴምብር አተመላቸው፡፡

(ብርሃኑ ለማ፣ ‹‹የታዋቂ የኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካና የፍቅር ታሪክ›› ከሚል

መጽሀፍ ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ፣ከገጽ114-130)

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጥንቃቄ በማንበብ ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. አፄ ምኒልክ ጣይቱን ሳያማክሩ የሚወስኑት ምንም አይነት ውሳኔ አልነበረም፡፡

ለ. እቴጌ ጣይቱ ንባብንና ጽሕፈትን እንዲሁም ቅኔን የተማሩት በደብረማዊ ገዳም ነው፡፡

ሐ. እቴጌ ጣይቱ በሀገር ግንባታ ላይ ታላቅ ስራ በመስራት የቆራጥነትና የአስተዋይነት ተምሳሌት መሆን የቻሉት አጼ ምኒሊክን ከማግባታቸው በፊት ጀምሮ ነው፡፡

መ. የኢጣሊያን ጋዜጠኞች ለእቴጌ ጣይቱ የተለያዩ ጥሁፎችን በዕትማቸው ያቀርቡ ነበር፡፡

ሠ. ጣይቱ ከአድዋ ጦርነት በኋላ አባትና እናት የሌላቸውን ህጻናት ይንከባከቡ ነበር፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ጣይቱ ወይዘሮ የውብዳር ወዳሉበት ጎጃም ውስጥ ደብረማዊ ወደምትባል ገዳም የሄዱት በምን ምክንያት ነበር?

ለ. የፖለቲካ ህይወታቸው ይበልጥ ገኖ የወጣው በምን ምክንያት ነው? አብራሩ፡፡

ሐ. በአድዋ ጦርነት ወቅት የኢጣሊያ ጦር ከምሽጉ ፈርጥጦ የሸሸው በምን ምክንያት ነው?

መ. እቴጌ ጣይቱ ‹‹ብርሀን ዘ ኢትዮጵያ›› በሚል ቅጽል ስም መጠራት የጀመሩት ከመቼ ጀምሮ ነው? ለምን?

ሠ. እቴጌ ጣይቱ ደብረ ታቦርን ለቀው ወደ እናታቸው ትውልድ ቦታ ወደ ጎጃም የሄዱት በምን ምክንያት ነው?

ረ. እቴጌ ጣይቱ ለሀገራቸው ካከናወኗቸው ጉልህ ተግባራት መካከል ሶስቱን ጥቀሱ፡፡

፫· ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ስለሆነም በንባቡ መሰረት ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ወግ | ረ. ጀብድ |
| ለ. ተጫጩ | ሰ. ሽምቆ |
| ሐ. ባጋጣሚ | ሸ. ተሰማርተው |
| መ. ደማም | ቀ. አርዓያ |
| ሠ. ውል | በ. አረፉ |

፬. በንባብ መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እንጠቀማለን፤ ስለሆነም የምታውቋቸውን የንባብ ስልቶች ጠቅሳችሁ ተወያዩባቸው፡፡

የንባብ ስልቶች

አንድ አንባቢ ጽሑፍን ሲያነብ ካለው ዓላማ ተነስቶ የሚከተሉት ስልቶች ሊጠቀም ይችላል፡፡

የአሰሳ ንባብ

ይህ የንባብ ስልት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በፍጥነት አንብቦ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ በአሰሳ ስናነብ መስመር በመስመር ማንበብ አይጠበቅብንም፡፡ ምክንያቱም ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ አንድ ተፈላጊ መረጃ ነጥሎ ለማውጣትና ለይቶ ለመረዳት በፍጥነት የሚከናወን የንባብ ስልት ስለሆነ ነው፡፡

የገረፍታ ንባብ

የገረፍታ ንባብ ከቀረበ አሃድ ውስጥ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ ቃላትን በአይናችን በመቃኘት ጠቅለል ያለ መረጃን ለማግኘት፣ የአንባቢውን በራስ የመተማመን ብቃት ለመገንባት ለፈተና ዝግጅት የተደረገ ንባብን ለማስታወስ ወዘተ የምንጠቀምበት የንባብ አይነት ነው፡፡

ጥልቅ ንባብ

በጽሁፍ ከቀረበ አሃድ ውስጥ እያንዳንዱን ዝርዝር ነገር በጥልቅ በመፈተሽ

የሚነበብበትና ከፍጥነት ይልቅ ጥልቀት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ስለሆነም ጥልቀት ያላቸው ጽሁፎችን ለማንበብ፤ የምርምር ጽሁፎችን ለመመርመርና ለመተንተን፣ የፈተና ጥያቄዎችን ለመመለስና ለመሳሰሉት ይረዳል፡፡

ሰፊ ንባብ

ሰፊ ንባብ ጥልቀት ሰጥተን የምናነባቸውን ጽሁፎች ረጅም ጊዜ ሰጥተን እንድናነብ የሚያግዘን ሲሆን እንደ ልብወለድ ያሉ ሰፊ ንባብ ያላቸው ጽሁፎች የሚነበቡበት ነው፡፡ የምናነበውም ለመዝናናት ወይም አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

፬. የሚከተለውን ጽሁፍ በአሰሳ ንባብ ስልት ካነበባችሁ በኋላ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

"አሰለፍ ሞት ሸቶኛል፤ ምን ይሻለኛል"

እርሱ ‹‹አሰለፍ›› የሚላት አሰለፈች ሴት ልጅ ወልዳ ሁለተኛውን ልጇን ነፍሰ ጡር ነበረች፡፡ አንድ ምሽት ወጣቷን ሚስቱን ‹‹አሰለፍ›› ብሎ ጠራት፡፡ እርሷም ‹‹አቤት ውዴ! አንተ ነህ ዘመዴ!›› ብላ የሚላትን ለመስማት አጠገቡ ቁጭ አለች፡ ጊዜው 1943 ዓ.ም ነው፡፡ ‹‹ዘንድሮ›› አላት ‹‹እንደምሞት ታውቆኛል፡፡ ያደኩት በችግር ስለሆነ ልጆቼ ቢቸገሩ እንዳታዝኝ፡፡ የምትወልጅው ልጅ ወንድ ሆኖ ከተወለደ ዓለም በቃኝ ብለሽ ስም አውጭለት›› ብሏት ከተቀመጠበት ብድግ ሲል አሰለፍ እጁን ይዛ ‹‹አለሜ! ለምን እንዲህ ትሆናለህ፤ ገና ብዙ ነገር ታያለህ›› ብላ ብትነግረውም ‹‹ከሞት ጋር ቀጠሮ አለኝ፣ ቢያልፈኝ ልከሰው፣ ቢተወኝ ልጠይቀው ቃል ተግባብተናል›› ብሎ ወደስራው አመራ፡፡ አሰለፍ ሀዘን ገባት፡፡ ‹‹ሜዳ ላይ ጥለኸኝ፤ እሞታለሁ ካልከኝ፤ ሌላ ምን ኑሮ አለኝ?›› ብላ ብትጠይቀውም ቃሉን ግን ሊያጥፍ አልቻለም፡፡ ይህንን ንግግር ለሚስቱ ከነገራት በኋላ ይበሳጫል፡፡ ብቻውን ያወራል፡፡ ተስፋ የቆረጠ ስሜት በፊቱ ላይ ይነበብበታል፡፡ የሚወደውን የስዕል ስራ ፈፅሞ ተወው፡፡

በሰላም ሸራውን ዘርግቶ፣ ቡሩሹን አንስቶ ‹‹ሀገሬ›› የሚለውን ቃል እየፃፈ ይተክዛል፡፡ ሁሌም በንግግሩ መሀል ሀገሬ ማለት ይቀነዋል፡፡ አሰለፍ የሚወደውን የስዕል ስራ እንዲሰራ በማለዳ ቡናውን አፍልታ፣ እጣኑን አጢሳ ጣፋጭ ምሳ

አዘጋጅታ ስራውን እየሰራ ቡና እንዲጠጣ ጋበዘችው፡፡ ደስ አለው፡፡ ብሩሹን ያዘ፡ ፡ ሸራው ላይ ብሩሹን ያውረገርገው ጀመረ፡፡ አቦል ቡናውን ጠጥቶ ስራውን እየሰራ ሳለ የቤቱ በር ተንኳኳ፡፡ አንድ ሰው ሰዓሊውን አስጠራው፡፡ ምሽት ቤተ መንግስት ስለምትፈለግ እንዳትቀር ተብሎ የቃል መልዕክት ተነገረው፡፡ አመሻሽ ላይ ‹‹አሰለፍ›› አላት ሚስቱን ‹‹ስዕሉን ስመለስ እጨርሰዋለሁ›› ብሏት ከቤት ወጣ፡፡ ከቤት ወጥቶ የት እንደሄደ ባይታወቅም ምሽት ላይ ግንፍሌ አካባቢ ሲሄድ በመኪና ተገጨ፡፡ መኪናው ገጭቶት ብቻ አላለፈም፡፡ እርሱን መሀል ላይ አጋድሞ እየደጋገመ ተመላለሰበት፡፡ ይህም ቢሆን የሰዓሊው ነፍስና ስጋው አልተላቀቁም ነበር፡፡ መኪናው ከገጨው በኋላ ጥሎት ሄደ፡፡ ፓሊሶቹም ወደ ቤተ ህክምና ወሰዱት፤ ሊተርፍ አልቻለም፡፡ እንዳለውም ሞተ፡፡ የጀመረውን ሥዕል ሣይጨርሰው አረፈ፡፡ ለሞቱ ምክንያት የሆነው የሚስላቸው ምፀታዊ ስዕሎች እንደነበሩ የሚያውቁት ይናገሩለታል፡፡ በተለይ ለሞት ያበቃው ሥዕል 12 አህያዎች የሚገኙበት ድርሰቱ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ ታሪክ በኢትዮጵያ የዘመናዊ አሳሳል ግንባር ቀደም ስም ያለው የሰዓሊ አገኘሁ ዕንግዳ አሟሟት ነበር፡፡ የሰዓሊ አገኘሁ ዕንግዳን አሟሟት ያቀረበው አዲስ 1879 ታሪኩን አቅርቦ ከድንገተኛ አደጋ ይሰውራችሁ፤ ከመኪና አደጋ ይጠብቃችሁ፤ ክፉውን ነገር ያርቅላችሁ ብሏል፡፡

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም የኢትዮጵያ ሴቶች በሃገር ዕድገት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያሳይ ሁለት አንቀጽ ጻፉ፡፡

፪. ከላይ ጣይቱ ብጡል በሚል ርዕስ የቀረበውን ሃሳብ በአንድ አንቀጽ አጠቃላችሁ ጻፉ፡፡

፫. ቀጥሎ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ቀርቦላችኋል፡፡ ሁለቱ ተጽፎላችኋል እናንተ ደግሞ እየመጨሻውን (ማጠቃለያ) አንቀጽ ጻፉ፡፡

በዚያ ለጋ ዘመኔ ወዜ ከፊቴ ላይ ሳይመጠጥ፣ ተንኮልና ነገር በልቤ ውስጥ ባልሰረፀበት ዕድሜ በከብት አጋጅነት ወላጆችን እረዳ ነበር፡፡ የዛሬን አያድርገውና

በዚያ ሙያ ከመጠን በላይ እደሰት እንደነበር ዛሬ ከተሜ ስለሆንኩ ልክድው አልችልም፡፡ ፀሀይ ፍንጥቅ ስትል ከብቶቼን ከበረት አውጥቼ፣ በቁልቁለቱና በአግድመቱ እያንጋጋው ወደማሰማሪያው መስክ ይገፍ ስሄድ አእምሮዬ ፍፁም ንፁህ በሆነ የደስታ ውሃ ይታጠብ ነበር፡፡

የደስታዬ ምንጮች ብዙ ነበሩ፡፡ የነፋሱ ፉጨት፣ የወፎቹ ዝማሬ፣ የወንዞቹ አወራረድና የአበቦቹ ሽታ በተፈጥሮ የሰጡኝ አስደሳች ባልንጀሮቼ ነበሩ፡፡ በቀትር ጊዜ የፀሃይ ሃይል በጣም አቃጣይ ሲሆን ከብቶችን በውሃ አረካቸው ነበር፡፡ በዛሬው መስታወት ወደ ኋላ ሳየው በጣሙን እገረማለሁ፡፡

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### መዝገበ ቃላዊና ዓውዳዊ ፍቺ

፩. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ቁንጮ ለ. አምበልጋ ሐ. መልቲ መ. ተቆራመደ ሠ. ዳረጎት

ረ. ቀልጣፋ ሰ . ደለዘ ሸ. ሲራክ ቀ. ረጃ በ. ሐጫ

፪. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

ሀ. ወጣቱ ትውልድ የአባቶቹን ታሪክ ያድሳል፡፡

ለ. ሰራተኛው በሰማው ነገር አዕምሮው ተረበሸ፡፡

ሐ. ደራሲው የአንባቢን ልብ የሚነካ ጽሁፍ አቀረበ፡፡

መ. ልጅቷ ከባለቤቷ ጋር በመጣላቷ ጎጆዋ ፈረሰ፡፡

ሠ. ሁልጊዜ ሰው በሚልህ ሳይሆን በራስህም መንገድ መጓዝ አለብህ፡፡

፫. ‹‹በላ›› የሚለውን ቃል ተጠቅማችሁ በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማስገባት ከአምስት በላይ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

፩. ዓረፍተ ነገሮች ከሰዋስዋዊ ቅርፃቸው አንጻር በስንት ይከፈላሉ? ምሳሌ በመጥቀስ አስረዱ፡፡

## የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች

ዓረፍተ ነገር ውስጣቸው ከሚይዙት ግስ አንጻር ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ በቀደመው የክፍል ደረጃ ተምራችኋል፡፡ ነጠላ ዓረፍተ ነገር በውስጡ አንድ ግስ የያዘ ነው፡፡

ምሳሌ፡- አረንጓዴ ሜዳ መንፈስን ያድሳል፡፡

ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ በውስጡ ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶችን ይይዛል፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር ሁለትና ከዚያ በላይ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አጣምሮ የሚይዝ የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ለማጠናከር የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እንመልከት፡፡

ለምሳሌ፡- ትናንት ከባህር ዳር የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰ፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ሁለት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡፡

እነርሱም፡- ልጁ ትናንት ከባርዳር መጣ፡፡

ልጁ ዛሬ ተመለሰ፡፡

፩. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ ዓረፍተ ነገር እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እያላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ቋንቋ በመልመድ እንጂ በመወለድ አይገኝም፡፡

ለ. ችግር ሲመጣ ድንገት ከተፍ ይላል እንጅ ነጋሪት አይጎስምም፡፡

ሐ. ኢትዮጵያውያን ኩሩና ጨዋ ህዝቦች ናቸው፡፡

መ. አለማየሁ ከክፍለ ሀገር ትናንት በመኪና መጣ፡፡

ሠ. በዓለም ላይ ጥቂት ሰነፎች ቢኖሩም አብዛኞቹ ግን ዓላማቸውን አይስቱም፡፡

፪. በሚከተሉት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አውጡ፡፡

ለምሳሌ፡- አለሚቱ በጧት ተነስታ፣ ቁርሷን ከበላች በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡

- አለሚቱ በጧት ተነሳች፡፡
- አለሚቱ ቁርሷን በላች፡፡
- አለሚቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡

ሀ. ዛፎችና ቅጠሎች ዳንኪራ እየረገጡ ይወዛወዛሉ።

ለ. ካፊያው መሬቱን ማራስ ስለጀመረ ትኩስ የአፈር ሽታ አፍንጫውን ወጋው።

ሐ. በምድር ላይ ርግቦች ቢኖሩም እባቦች ደግሞ በርካታ መሆናቸውን አትዘንጋ፡መ. እንደቦይ ውሃ ዝም ብሎ የሚፈስ ሰው፤ የህይወት እንቅፋት ነው፤ ሲሉ ታላላቆቻችን መክረውናል።

፫. በሚከተሉት ቃላት ሁለት ሁለት ነጠላዓረፍተ ነገር መስረቱና ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ቀይሯቸው።

ሀ. ጎሰመ    ለ. ሥራ    ሐ. ምርቃት

መ. ተሸፈነ    ሠ. ፍጥምጥም    ረ. ወላንሳ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሴቶችና እድገት መናገር በሚለው ክፍል ስለ ቃለ መጠይቅ ምንነት ተምረናል፡፡ ስለሆነም ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂው በአካል ተገናኝተው ተጠያቂው በቃል መልስ የሚሰጥበት ሒደት ነው፡ ፡ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ስናስብም በዝግጅትና አቀራረብ ጊዜ የምንተገብራቸው ነጥቦች እንዳሉ ተምረናል፡፡ ሴቶች ለሀገር እድገት በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ዙሪያ ቃለ ምልልስ በማድረግ ሀሳባችንን በቃል አቅርበናል፡፡

አንድን ንባብ አንብበን ተፈላጊውን ሀሳብ እንዴት ማውጣት እንዳለብንም አይተናል፡፡ ስናነብም እንደ ዓላማችን የተለያዩ ስልቶች ልንጠቀም እንችላለን፡፡ በዚህ ክፍልም የአሰሳ፣ የገረፍታ፣ ጥልቅና ሰፊ ንባብን አይተናል፡፡ የአሰሳ ንባብ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በፍጥነት አንብቦ ለማግኘት የሚጠቅም ንባብ እንደሆነም ተረድተናል፡፡
ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የማጠቃለያ ሃሳብ ጽፈናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች በመስጠት የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ተምረናል፡፡ በሌላ በኩል ስለ ነጠላና ውስብስብ ዓርፍተ ነገሮች ተረድተናል፡፡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጣቸው ከሚይዙት ግስ አንጻር ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉም አይተናል፡፡ ነጠላ ዓረፍተ ነገር አንድ ግስ ያለው ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶችን እንደሚይዝ ተመልክተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. አራት ግሶች (ሶስት ጥገኛ ዓ.ነገር) ያሉት ውስብስብ አረፍተ ነገር ከመሰረታችሁ በኋላ በውስጡ ያሉ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

፪. ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከሚዘጋጅ ሰው ተግባራት መካከል ሶስቱን ጠቅሳችሁ አብረሩ፡፡

፫. የአሰሳ ንባብ ከገረፍታ ንባብ በምን እንደሚለይ ከጻፋችሁ በኋላ

ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ።

፬. ለሚከተሉ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ከጻፋችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

ሀ. ዝባድ

ለ. ደራ

ሐ. ወርች

መ. አሜከላ

፭. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኝ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ምረጡና የሚመለከተውን አካል ከለያችሁ በኋላ የቃለ መጠይቅ መመሪያን መሰረት አድርጋችሁ ቃለ መጠይቅ አድርጉለት፤ የቃለመጠይቁን ውጤትም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሶስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሴቶች እና እድገት ዙሪያ የቀረቡ ሀሳቦችን በማዳመጥ መገምገም እችላለሁ። | | | |
| 2. | የቃለ መጠይቅ ምንነት፣ አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን ተከተየ ቃለ መጠይቅ ማቅረብ እችላለሁ። | | | |
| 3. | የንባብ ስልቶችን ለይቼ በአሰሳ ማንበብ እችላለሁ። | | | |
| 4. | አንድን ጽሁፍ አንብቤ ተፈላጊውን ሀሳብ ለይቼ ማውጣት እችላለሁ። | | | |
| 5. | ከአንድ ንባብ ውስጥ የማጠቃለያ ሃሳብ መጻፍ እችላለሁ። | | | |
| 6. | በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ቃለ ምልልስ ማድረግ እችላለሁ። | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7. | ከጽሁፍ ውስጥ አንድ አንቀጽ ማጠቃለያ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8. | ለቃላት ዓውዳዊ እና መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 9. | የአረፍተ ነነገር አይነቶችን እለያለሁ፡፡ | | | |
| 10 | ከውስብስብ ዓርፍተ ነገሮች ውስጥ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# አማርኛ ፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት (፬)
# በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የተለያዩ ተናጋሪዎችን ሃሳብ በማዳመጥ ትንተና ትሰጣላችሁ፡፡
- በማንበብ የቃላት ትርጉምን ትለያላችሁ፡፡
- ፈሊጣዊ አገላለጾችን በንግግራችሁ እና በጽሁፋችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- የቃላትን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺዎችን ትሰጣላችሁ፡፡
- አንቀፆችን ታብራራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

### ሽብርተኝነት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ሽብርተኝነት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ሽብርተኝነት በሀገር ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ዘርዝሩ?

ሐ. ሽበርተኝነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ወይም መፍትሔ የሚባሉትን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

መ. ቀጥሎ መምህራችሁ ሽብርተኝነት የሚል ምንባብ ሲያነቡላችሁ ማስታወሻ በመያዝ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቡድን እየተወያያችሁ ስሩ።

አዳምጦ መረዳት

፩. በአለማችን ላይ ስንት አይነት የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ዘርዝሩ፡ ፡

፪. የሽብር ወንጀል ወይም የሽብርተኝነት ድረጊቶች ከሚባሉት መካከል ሶስቱን ጥቀሱ።

፫. የሽብር ድርጊትን መከላከል የማን ኃላፊነት ነው መልሳችሁን በጸሁፍ ግለጹ።

፬. ሽብርተኝነት መነሻው ምንድን ነው ለሀገራችንና ለአለም ህዝብ ሰላምና ደህንነት ከፍተኛ ስጋት የሆነው ለምን እንደሆነ ግለጹ።

፭. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ሽብርተኝነት ከሚለው የማዳመጥ ምንባብ ውስጥ የወጡ ናቸው፤ ስለሆነም የቃላቱን ፍቺ ባዳመጣችሁት መሰረት ጻፉና ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

| | |
|---|---|
| ሀ. ርዕዮተ ዓለም | ሠ. መሰልጠን |
| ለ. ጽንፈኝነት | ረ. መዛት |

ሐ. እንዳይሰርጽባቸው ሰ. ዛቻ

መ. ጥቃት ሸ. ማገት

፯. ምንባቡ ሲነበብላችሁ ምን ምን ጉዳዮችን አዳመጣችሁ? በጥንድ ሆናችሁ ያዳመጣችሁትን በአጭር በአጭሩ በአስተዋፅኦ መልክ ዘርዝሩ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ከሰዎች፣ ከመጻሕፍት፣ ከመገናኛ ብዙሃን...) ስለመከባበር የሚያወሳ አጭር ጽሁፍ አዘጋጅታችሁ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ለጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

፪. ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ በክፍል ውስጥ ቃለ ምልልስ አቅርቡ፡፡

ሀ. የጥናት ተሞክሮ ሐ. የፈረቃ ትምህርት አሰጣጥ

ለ. ባህልና ቋንቋ መ. የሴቶች ልዩ ድጋፍ

፫ . ቀጥሎ የቀረበው ቃለ ምልልስ አደፍርስ ከተሰኘው ልቦለድ ውስጥ ተቀንጭቦ የቀረበ ነው፡፡ የገጸ-ባህርያት ቃለ ምልልስ በፈሊጣዊ ንግግር ያለባቸው ናቸው፡፡ እናንተ ደግሞ የገጸ- ባህርያቱን ንግግር በማጥናት ቃለ ምልልስ አድርጉ፡፡

አሁን ታዲያ የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለመበደር ነው አልክ.....?

‹‹ነበሩ እመየቴ ማስቸገሬ ባይሆን......

‹‹ለመግዛት ነው የምትፈልገው

‹‹ከየት እመየት ብሩ ከየት ተገኝቶ? በዚያው በዓይነቱ ለመክፈል ነው እንጂ በታሣሥ....

‹‹ነገር ማሞድሞድ ገንዘብ አይሆንም ይኸውልህ! ‹ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው ቀንዱ ይከለክለዋል!› ነው››

‹‹መቼምኮ የሚሉት ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም....

ብቻ እንዲያው ሰኔና ሰኞ..........

‹‹አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምርም ‹በሰም የተጣበቀ ጥርስ

ቢስቁበት አይደምቅ ቢበሉበት አያደቅ…!›

‹‹ታዲያ ምን ተሻለኝ ይመስለዎታል አሁን…?

‹‹መክልክሌ አይደለምኮ ‹ሰው ሆኖ የማይብስ እንጨት ሆኖ የማይጨስ!›

…‹ሰው ከስህተት ብረት ከዝገት..›

‹‹ታዲያ ያሉኝን ብለውኝ ብሄድ…

‹‹ ‹ብረት ካልፈላ አይላላ› እንዲህ ልክ ገባህ ይኸውልህ…

‹‹ድሮምኮ ቢሆን…እንዲያው ባንጣጣም ይሆናል…

‹‹ያለፈው አለፈ አሁን አንድ ልልህ የምፈልገው

ምን ነበር እቴ አዎ ለሁሉ እግዚአብሔርን..ማለቴ ከሆነ

ወዲያ ‹ደም ማልቀስ ድንጋይ መንከስ› አያስፈልግም…‹ወረቱን

እንደተቀማ

ነጋዴ ዋግ እንደመታው ስንዴ› መሚሰስ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም

ያሁኑ ወራት ስህተትህን ማረሚያ ነው፡፡ ‹ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ

መላጣ› መሻሉን መገንዘቢያህ…እንዲያ ተንዠባረህብኝ የነበረው ሰውዬ

ቢኖረኝ ነው የመጣኸው ‹… ተስካር ያዬ ተማሪ ሽቀጥ ያዬ አጣሪ…

‹‹የመሄጃ እጦት ነው እመየቴ…

‹‹ግርምቢጠኛነትህን ትንሽ አብረዶልሃል መቼስ ጨርሶም

ባይጠፋ፡፡ አዎ ለወደፊቱ መንገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊት ለፊቴ

ሽረር ብለህ መንገዱን ብትለቅልኝ ነውር የለውም…አንዳንዴ እንደሚ

ማልግ ነበር አንዳንዴ እየተፍረገረገ እንደሚለማመጥ ድመት መሆን

ያስተዛዝባል..አዎ ፊት ማጭገግ ወይም መሰንገጭም በኔ አይደለም

ከግምባርህ ትህትናን አታጥፋ

‹‹እመየቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም…

‹‹እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ..

‹‹ታዲያ ታዝኑ…

‹‹እንዴታ! በእርግጥ ታሳዝነኛለህ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ

ነው እንጂ ‹እህል ያለው ፈርዛዛ ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ› የተቻለ

ኝን ባደረግሁልህ…እንደምታውቀው ግን ዘንጋዳው ተወዷል

የሚሆንልህ ቢሆን ጥሬው ገንዘብ ይሻለኝ ነበር፡፡ ሳት ሆኗል ዘንጋዳ
እንደ ዘንድሮ ሆኖም አያውቅ ምን ይመስልሃል ታዲያ…? ደግሞስ
ደግሞስ
ሰማሆይ መረዳዳትን የመሰለ ምን ዓለም አለ? መረዳዳቱ አይከፋም ዛሬ
ባበድርህ
ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልል እመጣ ይሆናል…

፩. አንዳችሁ ጠያቂ ሌላኛችሁ ደግሞ ተጠያቂ በክፍል ውስጥ ጥንድ ጥንድ በመሆን የትምህርት የአጠና ተሞክሯችሁን ቃለ ምልልስ አድርጉ፡፡

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### ብዝኀነት

#### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል? ብዙኀነት ሲባል ምን ማለት ይስላችኋል፡፡

ለ. በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ስላለው ጠቀሜታ የተለያዩ የመገናኛ ብዙኀን ያዳመጣችሁት ክፍሉ ተማሪዎች በቃል አቅረቡ፡፡

ብዝኀነት

ሀገራችን የብዝኀ ባህል፣ ታሪክና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት ናት፡፡ ከትልቁ ራስ ዳሽን ተራራ እስከ ዝቅተኛው ዳሎል እና በመካከሉ ያለው የአየር ንብረት ክልል አቅፎ የያዘው የተፈጥሮ ሃብት ስብጥር በተፈጥሮ ከታደሉ ውስን ሀገራት አንዷ ያደርጋታል፡፡ በታሪካዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ወደር ያልተገኘላቸው የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር ፋሲለደስ ግንብ፣ የሀረር ጀጎል ግንብ እና ሌሎች ሃብቶች ዓለምን የሚያስደምሙ ክብሮቻችን ናቸው፡፡

የዚህ ሁሉ ሃብት ባለቤት ኢትዮጵያ ከ80 በላይ የራሳቸው የሆነ ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክና ወግ ያላቸውን ብሔሮችን አቅፉ የያዘች አንዲት ታላቅ ሀገር ናት፡፡ ልዩነታችንን እንደ ውበትና ድምቀት ቆጥረን ተከባብረንና ተዋደን የምንኖር ኩሩ

ህዝቦች ነን፡፡

በብዙኀነት ውስጥ ያለ አንድነትን አስተናግዳ የኖረችና የምትኖር ቅን ሃገር ለጠላቶቿ ደግሞ ሬት የሆነች ህብራዊ ሀገር ናት፡ ኅብር ስንል በአንድ በኩል እንደ ኅብረ ቀለማት የየራሳችን ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ያለን ነን፡፡ በሌላ በክል ደግሞ ‹ኅብር› ስንል አብረን፣ ተባብረን የኖርን፣ ኢትዮጵያ የምትባለውን የጋራ ሀገር የገነባን፤ መሆናችን ለማመልከት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ልዩነታችን ደግሞ የሰላማችን ምንጭ ነው፡፡ ሰላም ካለ ደግሞ እንኳን የሰው ልጅ አዕዋፍና አራዊትም ተከባብረው ይኖራሉ፡፡ አብሮነታችን የእኛ የሆኑትን መልካም ነገሮች ሁሉ የምናስጠብቅበት ኃይላችን ነው፡፡

አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ በቀረቡት አንቀጾችስ ምን ምን ነጥቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

በተለይ በሃይማኖቶች በኩል ያለው መቻቻል ሽብርተኝነትን የምንመክትበት ዕንቁ ባህላችን ነው፡፡ ‹‹ሃይማኖት የግል ነው፤ ሀገር የጋራ ነው!›› በማለት በአብሮነት የሚኮራ ህዝብ ባለቤት ነች፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን በገና፣ በጥምቀት፣ በኢድ-አልፈጥርና መውሊድ ወዘተ... ያለን መፈቃቀድና መተሳሰብ የመንፈስ እርካታን ይሰጣል፡፡ ከተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ተጋብቶ በመዋለድ አንድነቱን አጥብቆ ልዩነቱን አጥብቦ የሚኖር ህዝብ ነው፡፡ ለዚህ አይደል ዘፋኙ በስንኞቹ

አንቺም በሃይማኖትሽ እኔም በሃይማኖቴ

መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቴ፡፡ እንዲህ በማለት የገለጹት፡፡ የአንዱ እምነት ተቋም በሚሰራበት ሌላው ገንዘቡን እና ጉልበቱን አዋጥቶ ተሳታፊ ሲሆን መመልከት የተለመደ ነው፡፡ ስራዎቻችን ልዩነት ሳያስቸግረ አንድነትን ከፍ አድርገን በመተጋገዝ የሚሰራበት ሃገረ ኢትዮጵያ ዓለም የሚቀናባት፤ መንፈሳዊ ክብረ በዓሎቻችን ለዚህ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ይቺ ሀገርም በልዩነት ውስጥ አንድነት ነግሶ የሚታይባ ናት፡፡ በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት የሚያሳየን

አንዱ የውጪ ጠላት በመጣ ጊዜ ልዩነቶችን ወደ ጎን በማለት ለሀገር ሰላም አንድ ሃሳብ አንድ ልብ ሆነው ይዘምታሉ፡፡ ለዚህ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ቢቻልም በዋናነት ማሳያ የሚሆነን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ተምሳሌት የሆነ የአድዋ የድል ቀን ነው፡፡ ይህ የግለሰቦች ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ውጤት ነው፡፡ በልዩነት ውስጥ የሚታይ አንድነት ነው፡፡

አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት አድርጋችሁ ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልሱን በመምረጥ ማብራሪያ ስጡ፡፡

1 .ሀገራችን በተፈጥሮ ከታደሉ ውስን ሀገራት አንዷ ያደረጋት ምንምን ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሀ. ታሪክና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት

ለ. የአየር ንብረት ክልል አቅፎ የያዘው

ሐ.ከትልቁ ራስዳሽን ተራራ እስከ ዝቅተኛው ዳሎል መያዟ

መ. ሁሉም

2 . እንደ ውበትና ድምቀት ቆጥረን ተከባብረንና ተዋደን የምንኖረው በምንድን ነው፡፡

ሀ. ልዩነታችን ለ. የስራ ባህላችን

ሐ. የተለያየ ቀለም መ. አንድነታችን

3. ሽብርተኝነትን የምንመክትበት ዕንቁ የተባለው የትኛው ነው፡፡

ሀ. መቻቻል ለ. በሃይማኖቶች በኩል

ሐ. ከተለያየ ማህበረሰቦች መጋባት መ. ሀ እና ለ

4 .ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ተምሳሌት ያደረጋት ተግባር ምንድን ነው፡፡

ሀ. የአድዋ የድል ቀን ለ. በልዩነት ያለ አንድነታችን

ሐ. በቅርሶቻችን መ. ሁሉም

5 . ‹‹ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው፡፡›› ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ

ነው፡፡

ሀ. ተከባብሮ መኖርን

ለ. ተለያይቶ መኖርን

ሐ. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀልን

መ. ከእኔነት የእኛነት ሃሳብ ስላለው

፪. ቀጥሎ ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡ ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

ሀ. አንቺም በሃይማኖትሽ እኔም በሃይማኖቴ
መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቱ፡፡ ያለውን ግጥም ሃሳቡ ምን እንደሆነ ተወያይታችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. የሀገሪቱን አንድነት ተጠብቆና ልዩነቱን አጥብቦ የሚኖር በምንድን ነው?

ሐ. ሰላም ካለ እንኳን የሰው ልጅ አዕዋፍና አራዊትም ይኖራሉና ሲባል ምን ለማለት ነው?

መ. በብዙኀነት ውስጥ ያለ አንድነት አስተናግዳ የኖረች የምትኖር ቅን ሃገር ለጠላቶቿ ደግሞ ቅንቅን ምንነቷን ለመግለጽ የተሞከረ ሃሳብ ነው፡፡

ሠ. ሰው ሰራሽ የሚባሉ ቅርሶችን ለይታችሁ በማውጣት የት እንደሚገኝ ተወያይታችሁ ተናገሩ፡፡

፫. በጥንድ በመሆን ‹‹ብዝኀነት›› በሚለው ምንባብ ውስጥ በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት የሚለው ሃሳብ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

፬. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው በቡድን በመሆን ለቃላቱ ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ሬት

ለ. ስብጥር

ሐ. ዕንቁ

መ. ቅን

ሠ. መንፈሳዊ

ረ. ጥረት

## ክፍል አራት(፬)፡- ጽሕፈት

፩. ድርሰት ማለት ምን ማለት ነው? በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች የሚባሉት ምንምን ይመስላችኋል?

ማስታወሻ፡- ድርሰት

ድርሰት በአዕምሯችን የሚመላለስን ጉዳይ በጽሑፍ የማስተላለፍ /የማንጸባረቅ/ ስልት ነው። በውስጡም ፈጠራዊ እና ፈጠራዊ ያልሆኑ ገዳዮች እየተነሱ ሊብራሩና ትንታኔ ሊቀርብባቸው ይችላል። አጠቃላይ ድርሰት ልቦለዳዊ ወይም ኢልቦለዳዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ልቦለዳዊ ድርሰት የምንለው ፈጠራዊ ሥራን የሚያመለክት ሲሆን በውስጡም ኪናዊ ለዛ ያላቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ያካትታል።

ኢልቦለዳዊ ድርሰት ደግሞ እውነተኛ የሆኑ ኩነቶችን በጽሑፍ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው። ከተከሰተው ኩነት ዘርፋዘርፍ ሳንጨምር ማለትም ሳንከልስና ሳንበርዝ እንዳለ ማቅረብ ነው።

ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች

ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገባን (ሊያግዙን የሚችሉ) መርሆች አሉ። እነርሱም ድርሰት ከመጻፋችን በፊት እንዲሁም በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው ናቸው።

፩. ድርሰት ከመጻፋችን በፊት (ቅድመ ድርሰት ተግባር) ቀጥለን የምንዘረዝራቸው ተግባራት ድርሰት ከመጻፋችን በፊት የምንፈጽማቸው ናቸው።

1.1 ራሳችንን ድርሰት ለመጻፍ ማነሳሳት፡- በዚህ ተግባር ሥነ-ልቦናችሁን ዝግጁ የማድረግ ተግባር የሚፈጸምበት ነው።

1.2 ድርሰት የመጻፍ ዓላማ፡- ድርሰት የመጻፍ ዓላማ የምንለው ለማን፣ ለምን እንዴት እጽፋለሁ የሚለውን ቀድመን መመለስ የሚገባውን ጥያቄዎች የምንመልስበት ተግባር ነው።

1.3 ርዕስ መምረጥ፡- የሚመረጠው ርዕስ ሳቢ፣ ግልጽና አጭር መሆን አለበት፡፡

1.4 ርዕስ ማጥበብ/መወሰን/፡- የምንጽፈው ድርሰት ሊዳስስ የሚችላቸውን ነጥቦች የምንወስንበት ነው፡

1.5 አስተዋጽኦ /ቢጋር/ ማዘጋጀት፡- የምንጽፈው ድርሰት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍሰቱን ጠብቆ እንዲጻፍ የሚያግዘን ትልም ወይም መንገድ ቀያሽ ነው፡፡

1.6 መረጃ ማፈላለግ፡- በርዕሱ መሰረት ከሰዎች፣ ከመጻሕፍት ወይም ከመገናኛ ብዙሀን ልንፈልግ እንችላለን፡፡

1.7 መረጃዎችን መምረጥ/መለየት/፡- ከርዕሳችን ጋር የሚስማሙና ተመሳሳይነት ያላቸው ነጥቦች ብቻ የሚቀርቡበት ነው፡፡

1.8 የተደራሲ ዓውድ፡- የምንጽፈው ድርሰት በሰዎች ተቀባይነት እንዲያገኝ የምናደርግበት ነው፡፡

፪. ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ (የጽሕፈት ተግባር)

2.1 ረቂቅ መጻፍ፡- በተነደፈው ቢጋር መሰረት መጀመሪያውን የመጣልን ሀሳብን ማስፈር ነው፡፡

2.2 አርትኦት /እደታ/፡- የፊደል፣ የቃል ወይም የዓረፍተ ነገር ግድፈት እንዳይኖር ሙሉ ጥንቃቄ ተደርጎ የሚታረምበት ነው፡፡

2.3 የመጨረሻ ረቂቅ መጻፍ፡- ፀሀፊው ማድረግ የሚገባውን ሁሉ መፈፀሙን ባመነ ጊዜ ተከታዩ ተግባር በተፃፈበት ርዕስ ጉዳይ ላይ ሙያ ያላቸው ሰዎች አንብበው ተገቢ ማስተካከያ፤ አስተያየትና ምዘና እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

(ደረጀ ገብሬ፣ 2007 ዓ.ም.፣ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ)

፪. ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ድርሰት ጻፉ፡፡ ድርሰታችሁን ከመጻፋችሁ በፊት ከላይ ያለውን የድርሰት አጻጻፍ

መመሪያ መሰረት አድርጋችሁ፡-

ሀ. የመረጣችሁትን ርዕስ አጥብቡት/ወስኑት፤

ለ. ያጠበባችሁትን ርዕስ ከሶስት አንቀጽ በላይ ማጻፍ የሚያስችል ቢጋር ንደፉ፤

ሐ. ከላይ በነደፋችሁት ቢጋር መሰረት ግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድ ድረሰት ጻፉ፤

ርዕሶች፡-

ሀ. የከተሜነት መስፋፋት

ለ. ባህል

ሐ. መልካምነት

፫. የሚከተለውን ቢጋር ስለ መርካቶ የሚመለከት ነው፡፡ አስተዋጾውን መሰረት አድርጋችሁ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ፡፡

ርዕስ፡- መርካቶ

ሀ. የሁሉም ነገር መገኛ

1. ለማህበረሰቡ ሰፊ ግልጋሎት ይሰጣል
2. የተለያዩ ቁሳቁሶች ይከዘኑበታል
3. አዲስና ያገለገሉ የሚሸጥባት

ለ. የተጨናነቀች ከተማ

1. ኑዋሪዎቿ ሁሌ በመገፋፋት የሚኖሩባት
2. በሰውና በቁሳቁሶች የተሞላች
3. ሰውና መኪና የሚገፋፉባት

ሐ. ዋና የንግድ መስመር

1. ከተለያዩ ስፍራ እየመጡ የሚገበያዩባት
2. እቃዎችን በጅምላ የመታከፋፍል
3. ርካሽና ውድን የምታስተናግድ

## ክፍል አምስት (፭)፡- ቃላት

፩. በሚከተለው አጭር ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ፈሊጣዊ አንግግሮችን በመለየት በቡድን ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

“‹ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመት አይቆዩ› እንዲሉ ሰውየው ሰው ለየ፡፡ በዚያ ለዛ ቢስ ንግግሩ ቆሽቱ ያላረረ የለም፡፡ ‹መቼም ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት› እንደሚባለው እሱም እንደ ጻድቅ ድንግል መሬት ላይ አፈር ቀመሰ፡፡ ሙት ወቃሽ አያድርገኝና ግፉ ብዙ ነው፡፡ ታዲያ እንደ ጠዋት ጤዛ ለምትረግፍ እድሜ ሰው ነገር ሲቀምም ይውላል፡፡ይህ ነው ያልገባኝ የሃገሬ ሊቃውንት፤ አስረዱኝ ፡፡ እንደ ድርስ እርጉዝ ሆዱን አንገፍጦ፤ በሆድ እየታሰብ እንዴት ሀገር ልትበለፅግ ትችላለች?” አሉ፡፡ የስብሰባው መሪ ግንባራቸውን ሽብሽበው ታዳሚውን በቁረታ እየጠመለከቱ፡፡

፪. የሚከተሉትን ፈሊጣዊ ቃላት በ ‹‹ሀ›› የተዘረዘሩትን በ‹‹ለ›› ስር ካሉት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሀረግ መዘዘ | ሀ. እወደድ ባይ |
| 2. ዓይነ ልም | ለ. ድንገተኛ አጋጣሚ |
| 3. ሰማይ ጠቀስ | ሐ. ዘሩን ቆጠረ |
| 4. ሰኔና ሰኞ | መ. ተንኮለኛ |
| 5. ቅቤ አንጓች | ሠ. በጣም ረጅም |
| | ረ. ጅል፣ቂል |

፫. የሚከተሉትን ፈሊጣዊ አነጋሮች የሰውነት ክፍሎቻችን የሚመለከቱ ናቸው፡ ፡ እነዚህን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተጠቅማችሁ ‹‹ሰውነቴ›› በሚል ድርሰት ጻፉ፡፡፩ጉር ስንጠቃ የግንባር ስጋ ዓይነ አፋር ዓይነ ገመድ ሆደ ሰፊ እጅ አጠረው አፍ ለአፍ ዓይነ ልም እግረ እርጥብ እግረ ደረቅ እጅበእጅ እግር ብረት ወዘተ....

፬. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. መቋደሻ ሠ. ወርች

ለ. መናጆ ረ. ቅምጫና

ሐ. ህላዌ ሰ. ወሽከሬ

መ. ሽፍጥ ሸ. ድርሰት

፫. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻውን በመስጠት በቃሎቹ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ህልም ሠ. አደባባይ

ለ. ተባረከ ረ. ብርቅ

ሐ. ባላንጣ ሰ. ማክሰም

መ. የምስራች ሸ. ንቁ

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

ማስታወሻ፡- የቃል ክፍሎች

፩. የቃል ክፍሎች የሚባሉትን በመዘርዘር ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጡ፡፡

የቃል ክፍሎች በአምስት ይከፈላሉ፡፡ በአምስት ለመክፈል በመስፈርትነት የሚያገለግሉን ሶስት ነጥቦችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

እነርሱም:

ቅርፅ

አገባብና

ፍቺ/ትርጉም ናቸው፡፡

ቅርጽ፡- ቃላት በቅርጻቸው የሚወስዱትን ቅጥያ ምዕላድ አንጻር ነው፡፡

አገባብ፡- ቃላት በዓረፍተነገር መዋቅር ውስጥ የሚገቡበት ቦታ ይመለከታል፡፡

ፍቺ /ትርጉም/፡- ቃሉ የሚሸከመው መሰረታዊ ትርጉም ወይም ፍቺን የሚመለከት ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ በእነዚህ ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች መነሻ በማድረግ የቃል ክፍሎች በአምስት ይከፈላሉ፡፡

በዚህም መሠረት ስም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ ተውሳከ ግስና መስተዋድድ ናቸው፡፡

ሀ. ስም፡- የሰዎች፣ የእንስሳት፣ የእጽዋትና የማንኛውም ግኡዝና ረቂቅ ነገሮች መጠሪያ በመሆን የሚያገለግል ቃል ነው፡፡ ስሞች፡- ተውለወጠ፣ የተጸውኦ ወዘተ... ሁሉ ያጠቃልላሉ፡፡

በዓረፍተ ነገር ውስጥ መዋቅር የባለቤነት፣ የተሳቢነት እና የዘርፍነት ሙያ ይወጣሉ፡፡

እንደ /-ኦች/ እና /-ዎች/ የመሳሰሉትን አብዢ ምዕላድን ይወስዳሉ፡፡

መጠን፣ አይነትና ባህሪ የሚጠቁሙ ቃላትን ይወስዳሉ፡፡

ምሳሌ፡- ልጅ፣ ተራራ፣ ሰው፣ በግ፣ ውሃ፣ ቤት፣ አንበሳ ወዘተ

ለ. ቅፅል፡- ከስም በፊት እየገባ የስሙን ባህሪ፣ ቅርጽ፣ መጠን፣ ቀለም፣ ወገን ወዘተ የሚገልፅ ሲሆን የስም ገላጭ በመባልም ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ከስም በፊት የመጣ ቃል ሁሉ ቅጽል ሊሆን አይችልም፡፡ ቅጽሎች በጣም የሚለውን መግለጫ ቃል ተከትለው መግባት ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ደግ፣ ቸር፣ የዋህ፣ አዋቂ፣ ንፉግ፣ረጅም፣ ቀይ፣ ወፍራም ወዘተ...

ሐ. ግስ፡- በአገባቡ የዓረፍተ ነገር መቋጫ በመሆን ድርጊትን ወይም ሁነትን ያመለክታል፡፡ በቅርጹ ደግሞ የአረፍተ ነገር ባለቤት አመልካች ቅጥያዎችን ያስከትላል፡፡

ምሳሌ፡- መጣ፣ ናቸው፣ በላች፣ አመሰገነ፣ ገደለ ወዘተ...

መ. ተውሳከ ግስ፡- ማለት የግስ ጭማሪ ማለት ሲሆን ከግስ በፊት እየገባ ግሱን ከመጠን፣ ከሁኔታ፣ ከጊዜ፣ ከቦታ ወዘተ አንፃር የሚገልፅ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ግምኛ፣ ምንኛ፣ ጅልኛ፣ ክፉኛ፣ ቶሎና ገና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሠ. መስተዋድድ፡- ማለት ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ እና ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር ጋር የሚያዋድድ ወይም የሚያስማማ ማለት ነው፡፡ መስተዋድዶች የሚከተሉትን ባህሪያት የሚያሳዩ ቃላት ናቸው፡፡

ሀ. የራሳቸው የሆነ ፍች የላቸውም፡፡

ለ. እንደ ሌሎቹ ቃላት እርባታ የላቸውም፡፡

ምሳሌ፡- በ፣ ከ፣ ለ፣ ስለ፣ ወደ፣ እንደ...የመሳሰሉት ናቸው፡፡

(ጌታሁን አማረ፣ 2007)

፪. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍላቸውን ለዩ፡፡

ሀ. ልጁ በችኮላ ይነገራል፡፡

ለ. እኔ ጓደኛዬን በጣም እወደዋለሁ፡፡

ሐ. የጤና ጥበቃ ባለሙያዎች ዛሬ ተመረቁ፡፡

መ. መምህሩ የተሸለመውን ልጅ አደነቀው፡፡

ሠ. ሀይሉ ጠንክሮ ስላጠና ፈተናውን ደፈነው፡፡

ረ. የመስሪያ ቤታችን ጠንካራው ሰራተኛ ትናንት ተሸለመ፡፡

ሰ. ልጁ ሲሮጥ ክፉኛ ወደቀ፡፡

ቀ. ሀገራችን በእድገት ጎዳና ላይ እየገሰገሰች ነው፡፡

፫. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ከጻፋችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ቶሎ

ለ. ብርሃን

ሐ. እንደ

መ. መረመረ

ሠ. ጎበዝ

ረ. ፈጣን

ሰ. ኮሮና

ሸ. አሁን

፬. በክፍል ሶስት ‹‹ብዝኀነት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንድ አንቀጽ ከመረጣችሁ በኋላ በውስጡ ያሉትን እያንዳንዱን ቃላት ከቃል ክፍሎች መድቧቸው፡፡

ምሳሌ፡- ሀገራችን = ስም ታሪክ= ስም

ባህል = ስም ናት = ማሰሪያ አንቀጽ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት በሚል ርዕስ ድርሰት በተመለከተ በአዕምሯችን የሚመላለስን ጉዳይ በጽሑፍ የማስተላለፍ /የማንጸባረቅ/ ስልት እንደሆነና በውስጡም ፈጠራዊ እና ፈጠራዊ ያልሆኑ ገዳዮች እየተነሱ ሊብራሩና ትንታኔ ሊቀርብባቸው እንደሚችል ተገንዝባችኋል፡፡ ድርሰት ልቦለዳዊ ወይም ኢልቦለዳዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ልቦለዳዊ ድርሰት የምንለው ፈጠራዊ ሥራን የሚያመለክትና በውስጡም ኪናዊ ለዛ ያላቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ያካተተ ሲሆን ኢልቦለዳዊ ድርሰት ደግሞ እውነተኛ የሆኑ ኩነቶችን በጽሑፍ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡ በተጨማሪም ድርሰት በምንጽፍበት ጊዜ የምንከተላቸው መርሆች ተረድታችኋል፡፡ በተሰጣችሁ ርዕስ ቢጋር በመንደፍ እንዴት መጻፍ እንዳለባችሁ በመገንዘብ ድርሰት ጽፋችኋል፡፡ በመቀጠልም የፈሊጣዊ አነጋሮችን ሙያ በመለየት በድርሰታችሁና በንግግራችሁ ተጠቅማችኋል፡፡ በመጨረሻም የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርታችኋል፡፡ የቃል ክፍሎች ለመክፈል የሚያገለግል መስፈረቶችን ቅርጽ፣ አገባብና ፍቺን ለይታችሁ ቃላትን በየምድባቸው መድባችኋል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ሀገራችን ኢትዮጵያን እና በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት የሚለውን ሃሳቡ አንድነቱን በመወያየትና ምሳሌዎችን በማንሳት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

፪. የድርሰት አጻጻፈፍ መርሆችን ተከትላችሁ ከሚከተሉት ሁለት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ድርሰት ጻፉ፡፡

ሀ. ክብረ በዓላት

ለ. የወጣቶች መዝናኛ

፫. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቻውን በመስጠት ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. ወሽመጡ ተቆረጠ　　መ. ቅርሻ ቅርሻ አለ

ለ. ሱቅ በደረቴ　　ሠ. ወይን ረገጠ

ሐ. በጅ አለ　　ረ. በመላ ሄደ

፬. በሚከተሉት ቃላት የቃል ክፍላቸውን በመለየት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው፡፡

ሀ. እንስራ　　መ. አሸባሪ

ለ. ብዝኀነት　　ሠ. ለየ

ሐ. ከ　　ረ. ምንኛ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ረዘም ያለንግግሮችን በማዳመጥ፣ነጥቦችን በማውጣት ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 2. | አንድን ምንባብ በለሆሳስ በማንበብ ተገንዝበው የአንብቦ መረዳትን ጥያቄዎችን መመለስ እችላለሁ | | | |
| 3. | የቃላትን ዓውዳዊ ፍቺ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የቃላትን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺዎችን እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ፈሊጣዊ ንግግሮችን በፅሁፌቸውና በንግግራቸው ውስጥ በአግባቡ መጠቀም እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የተጻፉ የድርሰት አንቀፆችን ሃሳብ አብራራለሁ፡፡ | | | |
| 7. | በተሰጣቸው ርዕስ ላይ የተሟላ ፅሁፍ/መጣጥፍ/ ድርሰት እጽፋለሁ፡፡ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8. | ሁሉንም የንግግር ክፍልችን በመለየት በአግባቡ እና በትክክል መጠቀም እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት (፭) ቋንቋ ለዛ

## የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቋንቋ ለዛን ፅንሰ ሀሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘውጎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ አፈታሪኮችን ትለያላችሁ፡፡
- የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶችን ጭብጦች ትተነትናላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

**ተረትና አፈ-ታሪክ**

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩ .ያስነ ቃል አይነቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

፪ .ስለ ተረትና አፈታሪክ ያላቸውን አንድነትና ልዩነት በመዘርዘር አስረዱ፡፡

፫ .ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ የተረትና የአፈ-ታሪክ ምሳሌ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተ ደግሞ ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት ሃሳባችሁን በመሰብሰብ ለምታዳምጡት ነጥብ ትኩረት በመስጠትና ማስታወሻ በመያዝ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በየግላችሁ ስሩ፡፡

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. በተረቱ ውስጥ የተሳተፉት አካላት እነማን ናቸው?

ለ. ‹‹ጦጢት ጫማ መስራት ታውቃለች እንዴ?››በማለት የጠየቀው ማን ነው?

ሐ. ጦጣዋ ለጫማ መስሪያነት የሚያገለግለው ‹‹የጅብ ቆዳ፣ የዝንጀሮ ክስዳ ነው የሚሆነው፡፡›› ያለችው በምን ምክንያት ነው?

መ. ጦጣ አንበሳውን ውሃ ውስጥ ገብቶ እንዲሞት የደረገችው ምን ብልሃት በመፍጠር ነው?

ሠ. ከላይ ከተነበበላችሁ ተረት ምን ተማራችሁ?

ረ. ደባርቅ የተባለው ቦታ የሚገኘው በየትኛው የሀገራችን ክፍል ነው?

ሰ. ደባርቅ የተባለው ቦታ ስያሜውን እንዴት አገኘ?

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ምሰሌያዊ አነጋገር፣ የተረት የአፈ ታሪክ አንድነትና ልዩነት በቡድን እየተወያያችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በምሳሌ አስረዱ፡፡

፪. እነዚህ ስነቃሎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጥቅም እየተወያያችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## ተረት፣ አፈታሪክና እንቆቅልሽ

ተረት በእንስሳትና በተፈጥሮ ገፅታዎች እንዲሁም በሰዎችና ከእውኑ ዓለም ሰዎች ለየት ያለ መልክ፣ ባህሪና ችሎታ በተሰጣቸው የምናብ ዓለም ሰዎች አማካይነት የሰዎችን ሰናይና እኩይ ባህሪያት እንዲሁም የተለያዩ ድርጊቶች ያሳያል። ተረት የማህበረሰቡን ወግ፣ ልማድ፣ አጠቃላይ ማንነትና አመለካከት ሊያስተላልፍ ይችላል።

አፈታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው። የአፈታሪክ ዓላማ በታሪክ የተፈፀመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈፀም ቻለ? ለምን ተፈፀመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ መልስ ይሰጣል።

እንቆቅልሽ በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚደረግ የልጆችን አዕምሮ በማስላት፤ አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ፤ የአስተሳሰባቸውን አድማስ ለማስፋት፣ የሰውን፣ የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪና ቅርፅ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዳ የውድድር መንፈስ የሚታይበት የጥያቄና መልስ ስነቃል ነው።

(ዘሪሁን አስፋው፣ 2002፣ 28-41)

ለምሳሌ፡- ጠያቂ - ቀይ ዘንዶ ዋሻ ውስጥ ተጋድሞ

መላሽ - ምላስ

፬. የሚከተሉትን የምሳሌያዊ አነጋገር፣ አፈ ታሪክ እና እንቆቅልሽ ጥያቄዎች የያዙትን ሃሳብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አውድ በመፍጠር ማብራሪያ ስጡ።

ሀ. ምሳሌያዊ ንግግር

- ጨው ለራስ ስትል ጣፍጥ አለዚያ ድንገይ ነው ብለው ይወረውሩሃል።
- ስምከመቃብር በላይ ይውላል።
- ለጨለማ ጊዜ መብራት፤ ለመከራ ጊዜ ብልሃት

ለ. አፈታሪክ

በአዲስ አበባ‹‹እሪ በከንቱ›› የተባለው ሰፈር እንዴት ተሰየመ?

በአፄ ምኒልክ ዘመን የአራዳ ዘበኞች የአራዳን (የአሁኑን ፒያሳ) አካባቢ ብቻ ይጠብቁ በነበረበት ወቅት ይህ ሰፈር ጫካና በርከት ያሉ ጭፈራ ቤቶች ይኖሩበት ነበር፡፡ እነኝህ ብቻ ሳይሆኑ መሸት ሲል የዘረፋ ተግባር የሚያካሂዱ ማጅራት መቺዎች በጫካው ውስጥ ይገኙበት ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ወንድ አንዷ ቤት ገብቶ እረብሻ ቢያስነሳ አንዱዋ ዱላዋን፤ ሌላዋ ዘነዘነዋን የያዙትን ይዘው ይደበድቡታል፡፡ በተጨማሪም ማጅራት መቺዎችም አላፊ አግዳሚውን እየያዙ የአካል ጉዳት አድርሰው ገንዘብ ያለውን ገንዘቡን፤ የሌለውን ልብሱን ጫማውን ይዘርፉታል፡፡ ተጠቂው ክፍል ቢጮህ አንድም ሰው ዝር አይልም፡፡ ዝር ለማለት የሚቃጣው የአራዳ ዘበኛ ቢኖር በዚያው ይቀራል፡፡ በዚህ የተነሳ አካባቢው እሪ በከንቱ የሚል ስያሜ አገኘ፡፡

ሐ. እንቆቅልሽ

- እኔ ቢጠሩኝ አንቺ ምን አመጣሽ
- ሞቶ አይቀበር
  ወድቆ አይሰበር
  አባቴ የሰጠኝ ወንበር
- ባለ ግማሽ እምነት ባለአደራ
  ግማሹን አኑሮ ግማሹን የበላ

፫. ከቤተሰቦቻሁ በመጠየቅ ወይም ከመጽሐፍ በመፈለግ አራት አራት እንቆቅልሾቹን በማምጣት ጥንድ ጥንድ በመሆን በየተራ ተጠያየቁ፡፡ ስትጠያየቁ የእንቆቅልሽ የአጠያየቅ ስርዓቱን ተከትላችሁ መሆኑን አትዘንጉ፡፡

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የቋንቋ ለዛ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች የሚባሉትን ዘርዝራችሁ በምሳሌ አስረዱ፡፡

ሐ. የምንባቡን ርዕስ መሰረት በማድረግ ከምንባቡ የምትጠብቁትን በማስታወሻ ደብታረችሁ አስፍሩ፡፡

## የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች

ጽሁፋችን ወይም ንግግራችን በአንባቢ ወይም በአድማጭ ዘንድ ደርሶ ሳቢና ማራኪ እንዲሆን የተለያዩ ስልቶችን እንጠቀማለን፡፡ የምንጠቀማቸው ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች ግልጽ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከተለመደውና ዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀማችን በተጨማሪ የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘዴዎችን እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ስልቶች የቋንቋው ተጠቃሚው ሀሳቡን አጉልቶና አስውቦ እንዲያስተላልፍ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በርካታ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ቢኖሩም በዚህ ክፍል ፈሊጣዊ፣ ቅኔያዊ፣ ዘይቤያዊና ምሳሌያዊ አነጋገርን እናያለን፡፡

ከቋንቋ ለዛ መፍጠሪያ ስልቶች መካከል አንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ ይህ ዘዴ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉና ባለቤትነታቸው የማህበረሰቡ ሲሆን የእለት ተእለት ኑሮ፣ ገጠመኝና ምልከታ ማንጸባረቂያዎችና የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አገላለጾች በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሰረት የሚፈጠሩ፣ በቁጥብና ምርጥ ቃላት በአጭሩ የሚነገሩ የስነ ቃል አይነት ናቸው፡፡ በረጃጅም አረፍተ ነገሮችና ንግገሮች የሚብራራን ሃሳብ አሳጥረውና ጨምቀው የማቅረብ ሀይላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ባህሪያቸውም የማህበረሰቡን ማንነት፣ እምነት፣ ሀይማኖት፣ ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ የቋንቋ ቅመሞች ናቸው፡፡

ሰዎች በምሳሌያዊ ንግግሮች አዋዝተው ሃሳባቸውን ሲሰነዝሩ አድማጮችን ያዝናናሉ፤ የሚወዱትን ያሞግሳሉ፤ የሚጠሉትን ይነቅፋሉ፤ ተከራክረው ይረታሉ፤ ለሰዎች ተግሳጽ ይሰጣሉ፤ ባለጌ ከስህተቱ እንዲማር ያደርጋሉ፤ በአደባባይ ላይ ሲናገሩም አዋቂና አንደበተ ርቱዕ ይሰኙበታል፡፡

ባጠቃላይ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ነገሮችን በትኩረት እንድናያቸውና ካለፉ በኋላ መጸጸት እንደሌለብን፣ ለሁሉ ነገር መቸኮል ጥሩ እንዳልሆነ፣ ክፋት፣ ተንኮልና ሀሜት እንደማያስፈልግ፣ መረዳዳትና በታላላቆች ምርቃት ማግኘት ጥሩ እንደሆነ፣ አጉል ተስፋ ማድረግ እንደሌለብን ወዘተ የሚያሳዩ ናቸው።

ምሳሌ፡- ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም።

ለብልህ አይነግሩም ለአንበሳ አይመትሩም።

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለምናደርጋቸው ነገሮች ትኩረት እንድንሰጥና ጥንቃቄእንድናደርግ ይመክሩናል።

ሁለተኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ፈሊጣዊ አነጋገሮች እየቀላቀሉ መጠቀሙ ጥልቀትና ምጥቀት ያላቸው ሃሳቦችን ለማስተላለፍ ከማስቻላቸም በላይ የቋንቋ ችሎታንም ለማስገንዘብ አይነተኛ ማስረጃ ይሆናሉ፤ ሃሳብን በምሳሌ፣ በንጽጽር ወዘተ ትባት ባለው መልኩ ለማንጸባረቅ ያስችላሉ።

ፈሊጦች ቃላትን በማቀናጀት ወይም ለብቻቸው ከሚሰጡት ትርጉም በተለየ መንገድ ስንጠቀምባቸው ፈሊጦች ይሆናሉ። የአማርኛ ፈሊጦች ከሌሎች ቃላት የሚለዩባቸው ባህሪያት አሏቸው። ፈሊጣዊ ንግግሮቹ ከጥንድ ቃላት በትርጉማቸው ይለያሉ፤ ብዙ ጊዜ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ በቀጥታ አይተረጎሙም፤ ከቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ተነስቶ ፍች ለመስጠት ይከብዳል። እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀሞች ከሌሎች ቃላት በተለየ መልኩ ሃሳብን አጠናክረው የመግለጽ ሀይል አላቸው።

ምሳሌ፡- እግረ እርጥብ =እድለኛ

ሆደ ባህር = ቻይ፣ ትዕግስተኛ

መሬት ያዘ = ተመቻችቶ ተቀመጠ። በምሳሌዎቹ የተቀመጡት ፈሊጣዊ ንግግሮች በቀጥታ ፍቻቸውን ከመጠቀም የበለጠ ውበትና ለዛን ያስገኙልናል። የአማርኛ ፈሊጦች ለንግግራችን ለዛ፣ ለጽሁፋችን ደግሞ አጽንኦት ለመስጠት ያገለግላሉ። ሃሳብን በትክክልና በተዝናና መንገድ ማሸጋገር መቻልና ሌሎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መረዳት መቻል የቋንቋው ተቀዳሚ ተግባር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ገለጻን በሀይለቃል በማጠናከር ንግግርንም

ሆነ ጽሁፍን ይበልጥ ሃሳብ አስጨባጭነት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ የአማርኛ ፈሊጦች በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ወይም በማንኛውም ቃላት ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡

አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

ሶስተኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልት ዘይቤ ነው፡፡ ዘይቤ አንድን ሃሳብ ወይም ድርጊት ፣ የአንድን ነገር ቅርጽ፣ የሰውን ባህሪ ፣ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለተመልካችና ሰሚ ምናባዊ ፍስሃ በመስጠት የሚያቀርብ የአነጋገር ስልት ሲሆን በግጥምም ሆነ በዝርው ሊቀርብ ይችላል፡፡ ዘይቤ ነገሮች ንረውና ከረው፣ ብሩህና ጉልህ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያደርግ ሲሆን ከቋንቋ ለዛ መፍጠሪያ ስልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ለአነጋገር ትኩስነትና ጥንካሬ ለመስጠት፣ ሃሳብን ለየት ባለ መንገድ ለመግለጽና ረቂቅ የሆኑ ነገሮችን አጉልቶ ለማሳየት ሲባል ከመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ሆን ብሎ ማፈንገጥ ዘይቤ ይባላል፡፡ ዘይቤ ረቂቅ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ወትሯዊ የሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮችንም አግዝፎ ለስሜት በማቅረብ የሚባለው ነገር በአእምሮ ውስጥ እንደ ስዕል እንዲታይ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ዘይቤ የአድማጭን ወይም የአንባቢን ስሜት ለመሳብ፣ ሃሳብን ግልጽ፣ ጥልቅና ስሜት ነኪ ለማድረግ መልዕክትን በተቀባዩ አእምሮ ውስጥ ምስል ከሳች በሆነ መንገድ ለማስተላለፍና ትውስታን ለመፍጠር ወዘተ ያገለግላል፡፡

ዘይቤዎችን ማፍለቅ የሚቻለውም አንዱን ካንዱ ጋር በማነጻጸር ፣ አንዱን ከአንዱ ጋር በማመሳሰል ፣ አንዱን በሌላው በመወከል፣ ያንዱን ባህሪ ለሌላው በመስጠት፣ ግዑዙ ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ፣ ደብዛዛውን ብሩህ በማድረግ፣ ረቂቁን በማግዘፍ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡- ‹‹ዘሪሁን እንደንብ ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡›› በሚለው ዓረፍ ነገር ውስጥ የዘሪሁንን ታታሪነት ከንብ ጋር በማነጻጸር መልዕክቱ የበለጠ ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሌላኛው የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ዘዴ ቅኔ ነው፡፡ ቅኔ ረጅም ታሪክ ያለው በግጥም ወይም በዝርው ሊቀርብ የሚችልና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ረቂቅ እውቀት የታከለበት የህዝብ ሀብት ነው፡፡ ቅኔ በንግግርም ሆነ በጽህፈት ሊከሰት የሚችል፣ በውስጡ ስውር መልዕክትን ይዞ፣ ያ ስውር መልዕክት እንዳይታወቅ ሌላ ግልጽ የሆነ መልዕክት በመጨመር ሀሳብ የሚተላለፍበት ያገላለጽ ለዛ ነው፡፡

ቅኔ የሚፈጠረው በቃላትና ሀረጋት የእርስ በርስ ቅንጅት ነው፡፡ ሲመሰረትም ቀጥተኛውንና ሚስጥራዊውን መልዕክት ባንድ አዋህዶ የሚይዝ ቃል ወይም ሀረግ በገለጻው ውስጥ የሚኖር ሲሆን እሱም ህብረቃል ይባላል፡፡ ህብረ-ቃል የቅኔውን ግልጽና ስውር ፍች የያዘ ቃል ወይም ሀረግ ነው፡፡ ህብረቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚገኘው በቅኔው በስተመጨረሻ ሲሆን በውስጡም ሁለት ነገሮችን አጣምሮ ይይዛል፡፡ እነሱም ሰም እና ወርቅ ናቸው፡፡ የቅኔው ግልጽ ፍች ሰም ሲሆን ስውር(ድብቅ) ፍችው ደግሞ ወርቅ ይባላል፡፡ ሰም ቅኔውን በመጀመሪያ ስናነብ በአእምሯችን የሚመጣው ትርጉምና ቅኔ የሚቀኘው ሰው በትክክል ለማስተላለፍ የፈለገውን ሚስጥራዊ መልዕክት እንደመሸፈኛ የሚጠቀምበት ነው፡፡ ወርቅ ደግሞ ጸሀፊው ወይም ተናጋሪው ቅኔውን የተቀኘበት ምክንያት መልስ የሚያገኝበት ነው፡፡

ቅኔ ታሪክን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ለምስጋና፣ ለደስታና ለፍቅር መግለጫ፣ ለወኔ መቀስቀሻና ወዘተ ይጠቅመናል፡፡ ይህን ስናደርግ የምናስተላልፈው መልዕክት ለዛና ውበት ያለው እነዲሆን ይረዳናል፡፡

ለምሳሌ፡- ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ የሚወዷቸውና ታላቅ ደጋፊያቸው የነበሩት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች የሞቱባቸው ጊዜ

‹‹ እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ፣
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ፡፡

እጅግ ሙያ አዋቂ ዛሬ ተቀበረች፣

መዳኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች፡፡›› በማለት አስለቀሱ፡፡ ይህ የሚያሳየን ቅኔ በመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ብቻ ከመግባባት ይልቅ በዚህ መልኩ መልዕክት ብናስተላልፍ ውበት የተላበሰ አቀራረብ እንደሚሆን ነው፡፡

(መንግስቱ ታደሰ፣ 2012 ዓ.ም፣ ሜጋ የአማርኛ ሰዋሰው አጋዥ መጽሀፍ፤ ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ)

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ ካለው ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ በንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. የፈሊጣዊ ንግግሮች ፍች በቃላት ተናጠላዊ ትርጉም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ለ. ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ በጽሁፍ የሚተላለፉ የህዝብ የጋራ ሀብት ናቸው፡፡

ሐ. ቅኔ በግጥም ወይም በዝርው ሊቀርብ የሚችል ቃላዊ የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ነው፡፡

መ. በዘይቤ የሚነገረው ወይም የሚጻፈው ነገር በአእምሮ ውስጥ ምስል ከሳች እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሠ. ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች በአቀራረባቸው ተመሳሳይ የሆኑ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ናቸው፡፡

ረ. የቅኔን ግልጽና ስውር ፍች የያዘ ቃል ወይም ሀረግ ወርቅ ይባላል፡፡

፪ .ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ፈሊጦች ከሌሎች ቃላት በምን ይለያሉ? አብራሩ፡፡

ለ. ዘይቤን ከዘወተሩ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ሐ. ‹‹ምሳሌያዊ ንግግሮች በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሰረት የሚፈጠሩ ናቸው›› ሲል ምን ማለቱ ነው? በምሳሌ አብራሩ፡፡

መ. ለዛውን የጠበቀ ንግግር እንዴት ማቅረብ ይቻላል? በምሳሌ አስረዱ።

ሠ. ቅኔ ምንድን ነው? የቋንቋ ለዛንስ እንዴት ያስገኛል?

፫. የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን በጽሁፍ መልሱ።

| | |
|---|---|
| ሀ. በአደባባይ | ረ. አግዝፎ |
| ለ. ተግሳጽ | ሰ. ወትሯዊ |
| ሐ. አንደበተ ርቱዕ | ሸ. ማፈንገጥ |
| መ. ጨምቀው | ቀ. ፍስሃ |
| ሠ. ምስል ከሳች | በ. አጽንኦት |

፬. ‹‹ በ “ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በ “ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩት አቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.ሹርባ ልትሰራ ሄዳ ፀጉሯን ተላጭታ መጣች | ሀ. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ |
| 2.ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ | ለ. ደህና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ |
| 3. አህያ ቢሰባ ምን ረባ | ሐ. ሞኝ ለጠበቃው ምስጢር ይሸሽጋል |
| 4. ኃሜተኛ ያፍራል ሀሰተኛ ይረታል | መ. ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ |
| 5. ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ነው | ሠ. የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች |
| | ረ. ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ነው |
| | ሰ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች |

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሰረት ለተሰጧችሁ ርዕሶች በሃሳብ የሚስማሙ ከአራት በላይ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ተንኮል ጥሩ እንዳልሆነ ለማሳየት

- ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን፤
- ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ወዳጁን ይነቅል፤
- ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው፤
- በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም፤
- እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው፤

ሀ. ጠንክሮ መስራት

ለ. የመማር ጠቀሜታ

ሐ. የጊዜ ክቡርነት

መ. ምስጢር መጠበቅ

ሠ. በህብረት መስራት

ረ. ከመጥፎ ነገር መጠንቀቅ

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡ የቅኔ ጥያቄዎች ህብረ ቃላቸውን ከለያችሁ በኋላ የሰምና ወርቅ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ዝናቡ ዘነበ ይሞላል ውሃው

አወይ ይህን ጊዜ ለተሻገረው፡፡

ህብረ ቃል፡- ይህን ጊዜ ለተሻገረው

ሰም፡- ውሃው ሳይሞላ መሻገር ነው

ወርቅ፡- ይህን መጥፎ ዘመን እንደምንም ማለፍ መታደል ነው፡፡

ሀ. ሙሰኛው ሲበላ ይስቃል፡፡

ለ. በጣም አደነቅሁ ተመልክቼ፣

የሰው እንስራ አይቼ፡፡

ሐ. ድኀ ጸመ ድኀ ተሰቅሎ ከቤቴ፣

እኔን የሚቆጨኝ ሳልማር መቅረቴ፡፡

መ. ወተት በጨለማ ታበላሻላችሁ፣

ቀን እንዲህ ይገፋል እኔ ላሳያችሁ፡፡

ሠ. እሬት በመታቀፍ አለቀ ሸማዬ፣

በቃ አድርገህ ስጠኝ እባክህ ጌታየ፡፡

**ቅኔን ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎች**

- ቃላትን በማጥበቅና በማላላት የቅኔውን ፍቺ ማውጣት ይቻላል፡፡
- ታሪክን በማወቅ የቅኔ ትርጉሞች ይፈታሉ፡፡
- አንድን ቃል ወይም ሃረግ ሁለት ቦታ ላይ በመክፈል የተለያየ ትርጉም የሚኖራቸውን ቃላት በመፍጠር ዋናውን መልዕክት ማግኘት ይቻላል፡፡
- ሁለት ቃላትን ወይም ሃረጋትን በማገኛኘትና ወዘተ… የቅኔውን ምስጢር ማግኘት ይቻላል፡፡

፫. የሚከተሉትን ቅኔዎች ህብረ ቃላቸውን ከለያችሁ በኃላ የሰምና ወርቅ ፍቻቸውን በመጻፍ የቅኔዎቹን አፈታት ዘዴ ግለጹ፡፡

ሀ. ውሀ ክፍቱን አድሮ እንዳናጣ ጤና፣

ከዳድኜ እንደሆን ልየው እንደገና፡፡

ህብረቃል______________________________

ሰም ______________________________

ወርቅ______________________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ __________________

ለ. አስራ ሁለት ውሻ ታስሮ ከደጅሽ፣

አስፈትቼ ገባሁ እኔ ወዳጅሽ፡፡

ህብረቃል______________________________

ሰም ______________________________

ወርቅ______________________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ __________________

ሐ. ሚስቴ በየዓይነቱ ቁርሴን ስትሰጠኝ፣

ቅንጨዋ ናት በጣም የምትጣፍጠኝ፡፡

ህብረቃል_______________________

ሰም _______________________

ወርቅ_______________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ _____________

መ. አዳራሹ ሰፊ በሩ አልጠበባችሁ፣

በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ፡፡

ህብረቃል_______________________

ሰም _______________________

ወርቅ_______________________

ቅኔው የተፈታበት ዘዴ _____________

፬. የሚከተሉትን ግጥሞች በማንበብ ግጥሞቹ የተገነቡበትን ዘይቤዎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ስለዘይቤዎቹ አጭር ማብራሪያ ስጡ፡፡

ሀ. ለወትሮው ዳመና ፊቱ እየጠቆረ

ይዘንብ ነበረ...

የዘንድሮ ሰማይ

እየሳቀ ገዳይ

ፈጋግ ሰማያዊ መልኩን አሳምሮ፣

ስንቱን ፈጀ በላ ከራብ ተመሳጥሮ፡፡

(ነብይ መኮንን)

ለ. አካሄድሽ ይምጣ አረማመድሽ፣

ጥርስ አገላለጥሽ ከከንፈሮችሽ፣

ትህትናሽ አታላይ ከቅንነትሽ፣

አንገትሽ ብርሌ ወይኒቱ ማር ነሽ፡፡

(መንግስቱ ለማ )

ሐ. ፈላስፋው ሲመክር አደራ ብሏል፣

በምትሰራው ስራ ቀስ

ብለህ ቸኩል፡፡

(ከበደ ሚካኤል)

መ. አዕዋፍ በጠዋቱ ተነሳ እምትሉኝ ለምን ይሆን ከተቶ፣

ባማረ ድምጻችሁ መስኮቴ ተንኳኩቶ።

በሉ እኔስ ተነሳሁ ነቃሁኝ ታግየ፣

አዎ! በእርግጥ ነግቷል የሰው እግር ታየ።

ግን ልጠይቃችሁ አዕዋፍ በያይነቱ፣

ነጋ ጠባ ባዮች ሰርክ በየጠዋቱ።

ያነጋችሁት ቀን ባማረ ዜማችሁ፣

ለማን እንደጠባ ግን ታውቅታላችሁ?

( አያልነህ ሙላቱ)

ሠ. አስደንጋጭ

አልማዝ ያስነጠፈች

ወርቅ ያስጎዘጎዘች

በቫነር በዲዩር ሽቱ የታጠበች

በጌጥ ተብረቅርቃ

ጌጥ ሆና ጌጥ ይዛ

ጨረቃ ታፍራለች

ፀሀይ ትጠፋለች

ፀዳል፣ ብርሃን፣ ንጋት ሁሉን ታስንቃለች።

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

ረ. ብቸኝነት ጥምቡሳሱ፣

የፍርሀት ግሳንግሱ።

እንዳልተገራ ፈረስ ሲያደባየኝ፣

እንደ ደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ።

እንደተጋለጠ ሐሜት ሲሰብረኝ፣

አለ! በርታ ጠና በል የሚለኝ።

(ደበበ ሰይፉ፡ "አለ ‹ጠና በል› የሚለኝ")

፫. የሚከተሉትን ጅምር ስንኞች ቅኔያዊ አነጋገር በማድረግ የመጨረሻቸውን ስንኝ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ያው እዚያ ማዶ ፍሪዳ ተጥሏል፣

__________________________ ፡፡

ለ. ከተራራው ቆሞ የሚጣራው ማነው፣

__________________________ ፡፡

ሐ. እጠጣው አይደለም ጠጅ አምጡ ማለቴ፣

__________________________ ፡፡

መ. መድሃኒት ፈልጉ ሰዎች ባካችሁ፣

__________________________ ፡፡

፬. ከሚከተሉት የግጥም ርዕሶች ሁለቱን በመምረጥ ባለ አምስት ስንኝ ዘይቤያዊ ግጥም ጻፉ፡፡

ሀ. እያየሁ አላይም
ለ. ጨረቃ
ሐ. እንደሰው
መ. አዲስ አበባ

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

የቃላት መዝገበ ቃላዊ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ

፩. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. አጉረጠረጠ
ለ. በለዘ
ሐ. ቦረቦረ
መ. መረቅ
ሠ. ተቀናጀ
ረ. ዘመዘመ

፪. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. መልካም
ለ. እድገት
ሐ. ሆነ
መ. ክፉ
ሠ. ማርጀት
ረ. ወጠነ

፫. በሚከተሉት ጥንድ ጥምድ ቃላት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ዓረፍ ነገር በመስራት አስረዱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ለገሰ | ለ. አጫ | ሐ. ሽምግልና | መ. ረከሰ |
| ነፈገ | ጥላት | ወጣትነት | ተወደደ |

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

፩. የቋንቋ ለዛ ማስገኛዎች በሚለው ምንባብ አንቀጽ አንድ ውስጥ የሚገኙ ስሞችና ግሶችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

፪ .የለያችኋቸውን ስሞች ከምንባቡ ከያዙት ፍቺ ውጪ በራሳችሁ አምስት ቃላትን በመምረጥ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱባቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች ተምራችኋል፡፡ ማዳመጥና መናገር በሚለው ክፍል ከስነ ቃል ዘውጎች መካከል ተረት፣ አፈታሪክና የእንቆቅልሽን ምንነት ተገንዝባችኋል፡፡ ተረት በእንስሳትና በተፈጥሮ ልዩ ልዩ ገፅታዎች እንዲሁም በሰዎችና ከእውኑ ዓለም ሰዎች ለየት ያለ መልክና ባህሪ በተሰጣቸው የምናብ ዓለም ሰዎች አማካይነት የሰዎችን ሰናይና እኩይ ባህሪያት ሲያሳይ አፈታሪክ በአንድ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ እንቆቅልሽ ደግሞ በጠያቂና ተጠያቂ መካከል የሚደረግና ልጆች አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ፤ የሰውን፣ የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪና ቅርፅ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዳ የውድድር መንፈስ የሚታይበት በጥያቄና መልስ የሚቀርብ ስነቃል እንደሆነ ተረድታችኋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ቃላዊ ስነጽሁፎች በአግባቡ መጠቀም ችላችኋል፡፡

በመቀጠል ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ፣ ቅኔያዊና የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ምንነትና በንግግራችን ወይም በጽሁፋችን እንዴት ለዛን እንደሚያስገኙ አይታችኋል፡፡ የምንጠቀማቸው ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች ሳቢና ግልጽ እንዲሆኑ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ከተለመደውና ዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀማችን ለየት ባለ መልኩ ሀሳቡን አጉልቶና አስውቦ እንዲያስተላልፍ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ለዛ ማስገኛ ዘዴዎች ተጠቅመን የተለያዩ ቅኔዎችን መፍታት ችላችኋል፤ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮችን በጽሁፋችንና በንግግራችን ውስጥ ለምንና እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ ለይታችኋል፤ ዘይቤያዊ ግጥሞችን መጻፍ ችላችኋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለቃላት ቀጥተኛ፣ ተቃራኒና አውዳዊ ፍች ሰጥታችኋል፡፡ የቃል ክፍሎች በተለይም ስሞችና ግሶችን ከጽሁፍ ውስጥ ለይታችሁ አውጥታችኋል፡፡ በቃላቱም ዓረፍተ ነገር መመስረት ችላችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. የቋንቋ ለዛ ማስገኛ ስልቶች የሚባሉትን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ምሳሌዎችን በመጥቀስ በቃል አስረዱ።

፪. የሚከተሉትን ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ።

ሀ. ከአፍ የወጣ ቃል ከእጅ ______________________________ ።

ለ. ክርና መርፌ፤ስንደዶና ______________________________።

ሐ. ከመምህሩ ______________________________ ።

መ. ያለ ፍቅር ሰላም ______________________________ ።

ሠ. ከሮከረ ይሻላል ______________________________ ።

ረ. ያለ አቻ ጋብቻ ______________________________ ።

፫. በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በእንቆቅልሽ፣ በተረትና እና በአፈታሪክ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በጽሁፍ አቅርቡ።

፬. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. አንገተ ወፍራም

ለ. የቀለም ቀንድ

ሐ. ሰምና ፈትል

መ. ወንር ዘረጋ

፭. ለአፈታሪክ ምሳሌ የሚሆኑ ታሪኮች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመፈለግ በክፍል ውስጥ ለጓኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።

፮. ለሚከተሉት ቅኔዎች ህብረቃል፣ ሰምና ወርቃቸውን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ቁጠባ ሳናደርግ ተሻምተን በልተን፣
እነኛ ወጣጡ እኛ እንጀራ አጣን።

ለ. አለ ትለኛለች ሞኝ መስያት እኔ፣
ቅቤው በፊት አልቆ እያየሁት ባይኔ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የቋንቋ ለዛን ፅንሰ ሀሳብ ተረድቼ ዘውጎችን መዘርዘር እችላለሁ። | | | |
| 2. | ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅሎሾችን፣ አፈታሪኮችንና ተረቶችን ምንነት በመረዳት ፋይዳቸውን ለይቻለሁ። | | | |
| 3. | ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን በጽሁፍና በንግግር በመጠቀም መልዕክታቸውን ማስረዳት እችላለሁ። | | | |
| 4. | የስነቃል ዘውጎችን የምንጠቀምበትን ማህበራዊ አውድ ማስረዳት እችላለሁ። | | | |
| 5. | ዘይቤዎችን ከግጥም ውስጥ መለየት እችላለሁ። | | | |
| 6. | የቅኔ አፈታት ዘዴዎችን ለይቼ ቅኔችን መፍታት እችላለሁ። | | | |
| 7. | የተለያዩ የቋንቋ ለዛ ጭብጦችን መተንተን እችላለሁ። | | | |
| 8. | ለቃላት ዓውዳዊ፣ ተመሳሳይና፣ ተቃራኒ ፍቺ መስጠት እችላለሁ። | | | |
| 9. | ከማንኛውም ጽሁፍ ውስጥ ስሞችንና ግሶችን መለየት እችላለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት (፮) የታላላቆች ሚና

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በማድመጥ የፅሁፋን ዋና ሀሳብ ትተነትናላችሁ ፡፡
- በክርክር በመሳተፍ ምክንያታዊ ዳኝነት ትሰጣላችሁ፡፡
- በማንበብ እንደገና ጭምቃችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ ትፅፋላችሁ ፡፡
- ቃላትን በመገጣጠም ለቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- ተሻጋሪ ግሶችን በመለየት ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ(፩) ማዳመጥ

### ሀገር ማለት የኔ ልጅ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታላላቅ ሰዎች ሚና ምን እንደሆነ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

፪. የሚከተሉት ቃላት ‹‹ሀገር ማለት የኔ ልጅ›› በሚል ግጥም ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቃሎቹን በቡድን ተወያይታችሁ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱባቸው፡፡

ሀ. ሀገር
ለ. ዥረት
ሐ. ባዳ
መ. ጥሪት
ሠ. ሽቅጦ
ረ. ፍንትው
ሰ. የላቡን
ሸ. ፅጌ
ቀ. የሚለማ
በ. ደጃፍ

### የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎች

፪. መምህራችሁ ‹‹ሀገር ማለት የኔ ልጅ›› በሚል ርዕስ አንድ ግጥም ያነቡላችኋል፡፡ ግጥሙ ሲነበብ በጥሞና እያዳመጣችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎችን እንዲሟሉ አድርጓቸው፡፡

ሀ. __________ የተቀበረበት፣ ቀድመሽ የተነፈሽው አየር ብቻ እዳይመስልሽ፡፡

ለ. ሀገር ________________ ነው ቃሉ፡፡

ሐ. ሀገር ማለት ቋንቋ ነው፤________________ አይናገሩት በጆሮ አያዳምጡት፡፡

መ. ________________ ጥሪት ________________ ብርሃንሽ፡፡

ሠ. ________________ ባዳ ነው፤ ላለማው የሚለማ፡፡

የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ቀጥሎ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኂል፤ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ መልሱ

ሀ. ከግጥሙ የተረዳችሁትን የሃገር ብያኔ መነሻ በማድረግ ሀገር ማለትን በአጭሩ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

ለ. ባዳመጣችሁት ግጥም ላይ ጎልተው የታዩ ሃሳቦችን በማንሳት ተወያዩባቸው፡ ፡

ሐ. የግጥሙን ሃሳብ በራሳችሁ አገላለጽ ከአንድ አንቀጽ ባልበለጠ ዝርው ጽሁፍ ጻፉ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ በቡድን በመሆን ምክንያታዊ ሃሳብ በማመንጨት በማድረግ ሃሳባችሁን ለጓደኞቻሁ አጋሩ፡፡

- እርስ በእርስ የመከባበር ጉዳይ
- ከታላላቆቻችን የተቀበልነውን በአግባቡ እየተወጣን ነው? ወይስ አልተወጣንም?

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### የሰፈሩ አድባር

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ‹‹መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን›› የሚባለው አባባል ምን ማለት ይመስላችኂል፡

ለ. የሰፈር አድባር ሲባል ምን ለማመልከት ታስቦ ነው፡፡

ሐ. ለሚከተሉት ቃላት በቡድን እየተወያያችሁ ፍቺ ስጧቸው

| | |
|---|---|
| ሀ. የተኮለኮሉ | ሐ. ዘገባ |
| ለ. ማንቆርቆር | መ. ምክር |



## የሰፈሩ አድባር

የሰፈሩ ታላቅ ሰው ተማሪዎችን ሰብስበው ምሽት ላይ ምክር ይለግሳሉ፡፡ ተማሪዎች ቀናቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ይጠይቋቸዋል፡፡ ተማሪዎችም የተለመደ ምክራቸውን ለመስማት የጠሀይን ማዘቅዘቅ ይጠባበቃሉ፡፡ ከሾላ ዛፍ ስር ተቀምጠው ዙሪያውን ለተኮለኮሉ ህጻናትና ወጣቶች እንደማር የሚጣፍጠውን ንግግራቸው ያንቆረቁሩላቸዋል፡፡ ረጅም የእጅ ጭራቸውን እያወዛወዙ ሲናገሩና ሲያዳምጡ ወደር የላቸውም፡፡ በዚህ ተግባራቸውም የአካባቢው ሰው ሁሉ ይወዷቸዋል፡፡ የእምነትና ቋንቋ ልዩነት ያላቸውና የሌላቸው ብለው አይመርጡም፡፡t

አንድ በሰውነቱ ሙልት ያለ የአስረኛ ክፍል ተማሪ የገጠመውን መሰረት በማድረግ ፊቱን አኮሳትሮና ምላሽ እንደሚሰጡት በመተማገን ከከሌላ ተማሪ ጋር ስለገጠመው የውሎ ዘገባ በጥያቄ አቀረበና ‹‹እኔን ተማሪዎች ይጠሉኛል፤ ለምንድን ነው?›› ሲል የሰፈሩን አድባር ጠየቃቸው፡፡ የሰፈሩ አድባር ነገርን በምሳሌ ማስረዳት ከልጅነታቸው ጀምሮ የተካኑበት በመሆኑ የዚያን ወጣት ተማሪ ጥያቄ ከአንድ ታሪክ ጋር አገናኝተው ሊያስረዱት በመዘጋጀት ‹‹ልጆቼ

አንድ ታሪክ እነግራችኋለሁ፤ እንደተለመደው በጥሞና አዳምጡኝ›› በማለት ታሪካቸውን እያዋዙ መናገር ጀመሩ፡፡

አንድ ቀን ዝንብና ንብ አያወሩ በወሪያቸው መሃል ዝንብ ንብን እንዲህ ስትል ጠየቀቻት ‹‹ንብ ሆይ ለምንድን ነው የሰው ልጅ እኔን የሚጠላኝ? ለምንስ ነው የሚፀየፉኝ? ቤታቸው ስገባ ያባርሩኛል ይገድሉኛል፡፡ ከሚጠጡት ነገር ላይ ከተገኘሁ ይደፉታል የሚበሉት ነገር ላይ ካረፍኩ ያረፍኩበትን ቦታ ያለውን እህል ቆርሰው ይጥሉታል፡፡ አንቺን ግን እንደኔ አይፀየፉሽም፡፡ እንዲያውም ቤታቸው ስትገቢ ይንከባከቡሻል›› አለቻት፡፡ ንግግሯን በመቀጠልም ‹‹ደግሞም መልካም ነገርን ተስፋ አድርገው ቤት መግባትሽን በደስታ ይቀበሉታል፡፡ ለምንድን ነው?›› ስትል ለንብ ጥያቄዋን በብስጭት አቀረበች፡፡ በዚህ ጊዜ ንብ ክንፎቿን እያርገፈገፈች ‹‹ውሎሽ የት ነው?›› አለቻት፡፡ ይህን ከተናገረች በኋላም ወደ አበባዋ (ስራዋ) ሄደች፡፡

ተማሪዎች! አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

እንግዲህ እዚህ ጋር ቆም እንበል እናስብ፣ ሰው ጠላን፣ ገፋን፣ ናቀን እያልን እንደ ዝንቧ ጥያቄን አዝለን ከምንጓዝ ውሏችንን በደንብ እንይ፡፡ የሚገርመው ንቧ የምታወራው ከማን ጋር እንደነበር እረስታ መቼም ‹‹ከዝንብ ማር አይጠበቅም፡፡ ›› ልትል ፈልጋ ከእሷ ጋር እያወራች መሆኑን ስታስታውስ ዝም አለች፡፡ ታዲያ ወዲያው ‹‹መቼም ማንም በጤፍ ማሳ ላይ ስንዴ አይጠብቅም በማለት ተካችው›› አሉ ታላቁ ሰው፡፡ ቀጥለውም ‹‹ስለዚህ ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ፡፡ ምክንያቱም ሀሳባችን ስራችንን፣ ስራችን ውጤታችንን፣ ውጤታችን እኛነታችንን ይገልፅልናልና›› ብለው ትንፋሻቸውን በረጅሙ ተንፍሰው ሃሳባቸው ቋጩ፡፡

የሰፈሩን አድባር ንግግር በተመስጦ ሲያዳምጡ የነበሩት ልጆችም ተነስተው

ጉልበታቸውን ሳሙ። የሰፈሩ አድባር ቀጥለውም ‹‹እስኪ የተራዳችሁትን በአጭሩ የሚነግረኝ ማነው?›› በማለት ለልጆቹ ጥያቄ አቀረቡ። በክፍል ጓደኞቹ የተነቀፈው ተማሪ ከሰፈሩ አድባርና ከጓድኞቹ መሃል ፈጠን ብሎ ቆመና ‹‹ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ... ምን ... ተምራ መጣች ነው›› የሚሉት አባቴ። ‹‹አዋዋሌ ጥሩ ስላልነበር የክፍል ጓደኞቼ በመልካም ሊመለከቱኝ አልቻለሉም። በዝንቧ እና በንቧ መስለው ያስተማሩኝ ከመጥፎ መካሪ ጓደኛ መራቅ እንዳለብን ተገንዝቤያለሁ›› አለ። የልቡን ጥያቄ መልስ በሚያገኝበት ቦታ በመጠየቅና አንጀት የሚያርስ ምላሽ በማግኘቱ ልቡ በሀሴት ሞልቶ። ለጥያቄ መልስ ሲያገኙለት የማይደሰት ማን አለ ሲል ውስጡን እየጠየቀ። በመጨረሻ የሰፈሩ አድባር ትምህርታቸውን በምርቃት ቋጩ።

አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባቡ መሠረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም ለጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ።

1. ንብ ለዝንብ የሰጠቻት ምላሽ ምን ነበር?

ሀ. ውሎሽ የት ነው ለ. ሰው አይጠላሽም

ሐ. ለጥያቄዋ የጥያቄ መልስ መ. ሀ እና ለ

2. በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ብዛት ...............ናቸው

ሀ. ፬ ለ. ፫ ሐ. ፪ መ. ፩

3. ምንባቡ የተጻፈበት የዘይቤ አይነት --------------- ነው?

ሀ. እንቶኔ ለ. ሰውኛ ሐ. ግነት መ. ተለዋጭ

4. ብዙ ጊዜ ሰው ጠላን፣ ገፋን፣ ናቀን የምንለው ለምንድን ነው?

ሀ. ውሏችንን በደንብ ስለማናይ ለ. ውሏችንን በደንብ ስለምናይ

ሐ. ውሏችንን ከመልካም ጓደኛ ጋር ስለምናሳልፍ መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ስህተት የሆነው የትኛው ነው።

ሀ. እንደ ዝንቧ ጥያቄ አዝለን ከምጓዝ ውሏችንን መመርመር

ለ. እንደ ዝንቧ ጥያቄ አዝለን ከመጓዝ ለጓደኞቻችን ጥያቄአችንን ማቅረብ።

ሐ. ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት

ውሏችንን እንቃኝ

መ. ሁሉም

6. የምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ

ለ. አንቺን ግን እንደኔ አይፀየፉሽም፡፡ እንዴውም ቤታቸው ስትገቢ ይንከባከቡሻል፡፡

ሐ. ‹‹ንብ ሆይ ለምንድን ነው የሰው ልጅ እኔን የሚጠላኝ?

መ. ሁሉም

፪. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ንብ በሃገራችን የምትመሰለው በታታሪነት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ከምንባቡ በየትኛው አንቀጽ ላይ ቀርቧል በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. የሰፈሩ አድባር ምክራቸውን የዝንብና የንብን ታሪክ በመጥቀስ ያቀረቡት በምን ምክንያት ነው? አብራሩ፡፡

ሐ. በክፍል ጓደኞቹ የተነቀፈው ተማሪ የሽማግሌውን ምክር ለማብራት የተነሳከሰፈሩ ፈጠኖ የተነሳው ለምድን ነው? አብራሩ

መ. ‹‹ምንግዜም ውድቀታችንን ለማረምም ይሁን ብርታታችንን ለማብዛት ውሏችንን እንቃኝ፡፡›› ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

ሠ. ከምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ፈሊጣዊ አነጋሮችን ለይታችሁ በማውጣት ፍቺ ስጡ፡፡

፫. የምንባቡን ሃሳብ በራሳችሁ አገላለፅ ከመቶ ባልበለጠ ቃላት እንደገና ጻፉ፡፡

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

ሀ. ደብዳቤ ማለት ምንድን ነው?

ለ. የደብዳቤ አይነቶች የሚባሉት እነማን ናቸው? እሲኪ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ደብዳቤ

ደብዳቤ ሰዎች ሃሳባቸውን በተሳካ መልኩ በጽሁፍ የሚለዋወጡበት ዘዴ ነው፡፡ ደብዳቤ የሰላምታ/የግል/የወዳጅ ዘመድ/ እና የስራ/ የመስሪያ ቤት/ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

ሀ. የግል ደብዳቤ፡- ይህ የደብዳቤ አይነት ግለሰብ ለግለሰብ፣ ግለሰብ ለቤተሰብ፣ ቤተሰብ ለቤተሰብ ወይም ቤተሰብ ለግለሰብ የሚጽፉት ሲሆን ዓላማውም ማህበራዊ ህይወታቸውንና መስተጋብራቸውን (ሰላምታ ለመለዋወጥ፣ ለምስጋና፣ ለይቅርታ፣ ለወቀሳ፣ ለማጽናኛ፣ ለፍቅር፣ ለደስታ መግለጫና ለተለያዩ ፕሮግራሞች ጥሪ ለማድረግ) ማጠናከር ስሊሆን ይችላል፡፡ የግል ደብዳቤ የራሱ የሆነ ቅርጽ ሌለውና ቅርጹና ይዘቱም በጸሀፊው ፍላጎት የሚወሰን ነው፡፡

ለ. የስራ/የመስሪያ ቤት ደብዳቤ፡- የራሱ ቅርጽ ያለው ሲሆን ግለሰብ ለድርጅት፣ ድርጅት ለግለሰብ ወይም ድርጅት ለድርጅት የሚጽፉት የደብዳቤ አይነት ነው፡፡ የደብዳቤው ዓላማም ስራ ለመቀጠር፣ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ዋጋ ለመጠየቅ፣ ለማንኛውም ህጋዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠትና ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ የስራ ደብዳቤ ሲጻፍም የሚከተሉትን ነጥቦች አካቶ ይይዛል፡፡

ሀ. ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ያስፈልጋል፡፡

ለ. በድረጅት የሚጻፍ ማንኛውም ደብዳቤ የሚመዘገብበት ልዩ ቁጥር ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን ግለሰብ ለድርጅት በሚጽፈው ደብዳቤ ውስጥ ቁጥር አይኖርም፡፡

ሐ. የተቀባይ አድራሻ፡- መልዕክቱ የሚላክለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ስምና አድራሻ በትክክል መጻፍ አለበት፡፡

መ. የላኪ ስም፣ ፊርማና ኃላፊነት፡- ደብዳቤውን የጻፈው ግለሰብ ወይም ያጸደቀው ድርጅት ሙሉ ስም፣ ፊርማና ኃላፊነት በግልጽ ይሰፈራል፡፡

ሠ. ጉዳዩ በሚል ርዕሱ በአጭሩ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ረ. የደብዳቤው ሀተታ ወይም መልዕክት በግልጽ ቋንቋ ይጻፋል፡፡

ሰ. የመልካም ምኞት መግለጫ፡- ደብዳቤውን ለምንጽፍለት አካል ዓላማውን በጠበቀ መልኩ፣ በአጭርና ግልጽ ቃላት የመልካም ምኞት መግለጫ(‹‹ከሰላምታ ጋር!››) የምንጽፍበት ነው፡፡

ሸ. ማህተም፡- ደብዳቤውን የጻፈው ድርጅት ከሆነ የራስጌና የግርጌ ማህተም ያስፈልገዋል፡፡ የራስጌ ማህተም በአራት ማዕዘን ቅረጽ (የተቋሙ ልዩ ምልክት) ከደብዳቤው ራሰጌ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን የግርጌ ማህተም ክብ ቅርጽ ኖሮት በደብደቤያችን ግረጌ ላይ ይገኛል፡፡

ቀ. ግልባጭ፡- ግልባጭ የሚጻፈው ደብዳቤው ከተጻፈለት በተጨማሪ ሌላ አካል እንዲያውቅልን ወይም እንዲደርሳቸው ከፈለግን ነው፡፡

፩ የሚከተለውን የመስራ ቤት ደብዳቤ በመመልከት ከላይ ከቀረበው ማስታወሻ ጋር በማገናኘት ዋና ዋና ነጥቦች በማንሳት በቡድን ተወያዩበት፡፡



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

Biiroo Barnoota Bulchiinsa Magaalaa Finfinnee

City Government of Addis Ababa Education Bureau

ቁጥር [illegible]

ቀን 04/01/2014

ለ------------------ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፦ የ2014ዓ.ም የትምህርት ካላንደር ማሳወቅን ይመለከታል፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ2014ዓ.ም ትምህርት የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት የበጀት አመቱን የትምህርት ካላንደርን ለቅድመ አንደኛ፣ ለአንደኛ ደረጃ እና ለሁለተኛ ደረጃ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም የትምህርት ካላንደሩን ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር 2 ገጽ አባሪ በማድረግ የላክን ሲሆን ክፍለ ከተማው ይህንን አውቆ በተቀመጠው መሰረት ትምህርት ቤቶች እንዲያከናውኑ እና እንዲፈጽሙ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አድማሱ ደቻሳ ቶና
ምክትል ቢሮ ኃላፊ
Admasu Dechasa Tona
Deputy Bureau Head

ግልባጭ

- ለትምህርት ቢሮ ሃላፊ ጽ/ቤት
- ለቢ/ት/ም/ቢ/ሃላፊ
- ለመም/ል/ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለት/ም/ቴክ/ ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለቢ/ት/ዝ/ትግበራ ዳይሬክቶሬት
- ለአፋን ኦሮሞ አጠ/ት/ም/ሉ/ዳይሬክቶሬት ት.ቢሮ

ምሳሌ ሁለት

ቀን……………………ዓ.ም

ለአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጻፍልኝ ስለመጠየቅ

ከላይ በርዕሱ እንደተገለጸው እኔ ተማሪ ሰሚራ አወል የአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ፲ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆንኩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ባወጣው የተማሪዎች የሥነጽሑፍ ውድድር ትምህርት ቤቱን ወክዬ ስለምወዳደር ት/ቤቱ ከአሁን በፊት የተለያዩ ክበባት ላይ የሰራኋቸውን የክበባት እንቅስቃሴዎች ተጠቅሶ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጽፍልኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር!



ተማሪ ሰሚራ አወል

፪. አንድ ተቋም ውስጥ አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ማመልከቻ እንድትጽፉ የታዘዛችሁ እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ የመስሪያ ቤት ደብዳቤ (የስራ ማመልከቻ) ጻፉ።

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### ቃላትን መመስረት

፩.በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኙ ቅጥያ ምዕላዶችን ከስራቸው ከሚገኙ ቃላት ጋር በማገጣጠም ከመጀመሪያው ትርጉም ተጨማሪ ፍች ያላቸው ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፡- ኢትዮጵያዊነቱን = ኢትዮጵያ-ኣዊ-ነት-ኡ-ን

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| -ኣቸው | -ኡ | -ዎች | -ን | -ም |
| አስ- | -ኣችን | -ኦች | -ኣማ | -ኧኛ |
| -ነት | -ኣዊ | ተ- | አል- | -ኣችሁ |

ሀ. ኢትዮጵያ

ለ. ልጅ

ሐ. ስራ

መ. ነገር

ሠ. ወደደ

ረ. ተማሪ

ሰ. ቤት

ሸ. መንፈስ

፪. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ቃላት በስርዓት ያልተዋቀሩ ናቸው። በመሆኑም የቃሎቹን ሰዋስዋዊ አወቃቀር በማስተካከል ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካላችሁ ጻፉ።

ሀ. ደስ ይለኛል ቀይ በግ

ለ. ባህል አንዱ የሃገር ሽምግልና መገለጫ ነው።

ሐ. የእናት መድረስ ትልቅ ወግ ላይ ማዕረግ ነው።

መ. ለሃገር ከፍተኛ እድገት ንፁህ ጥቅም አእምሮ አለው።

ሠ. የማያበላሸው ሃብት እውቀት ብል ነው።

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

፩. የድርጊ ግሶች የሚባሉት እነማን ናቸው ? በምሳሌ አስተረዱ።ሽብርተኝነት

የድርጊት ግስ

የድርጊት ግሶች የሚባሉት አንድ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፁ ናቸው። ገደለ፣ ፈለጠ፣ ቆረጠ፣ ተኛ፣ ተነሳ ወዘተ የድርጊት ግስ ምሳሌዎች ናቸው። የድርጊት ግሶች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም:- ሳቢና ኢሳቢ ግሶች ይባላሉ።

ሀ. ሳቢ ግስ /ተሻጋሪ ግስ/:- ሳቢ የሚባሉት ከተሳቢ ስም ጋር እየተዋቀሩ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርቱ ግሶች ናቸው። ተሳቢው ስም ከግሱ በፊት ይገኛል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

1. እንጀራ በላ።
2. ሻይ ጠጣ።

ሁለቱም ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። በላ እና ጠጣ የሚሉት ሳቢ ግሶች ስለሆኑ እንጀራ እና ሻይ የሚሉትን ስሞች በተሳቢነት ወስደው ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል።

ለ. ኢ-ሳቢ ግስ /ኢ-ተሻጋሪ ግስ/:- ኢ-ሳቢ ግሶች ተሳቢ ስም አያስፈልጋቸውም፡ ሀረግ የሚመሰርቱት ከተውሳከ ግስ ጋር በመጣመር ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

1. ክፉኛ ወደቀ።
2. በጣም ሮጠ።

ወደቀ ኢ-ሳቢ ግስ ነው። የሚገልፀው የመውደቅን ድርጊት ብቻ ነው። ድርጊቱ የሚፈፀመው በወዳቂ ሰው ነው። አወዳደቁ ከባድ/ቀላል/ ሊሆን ይችላል። ይህም የሚገለፀው በተውሳከ ግሶች አማካይነት ነው። ተውሳከ ግሶቹ ከግሱ ቀድመው ገብተዋል።

( ባየ ይማም2010:183)

፪. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ተሻጋሪና ኢ-ተሻጋሪ ግሶችን የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን ለዩ፡፡

ሀ. መምህሩ ከተማሪዎቹ ሃሳብ ተቀበለ፡፡

ለ. ይህ አመለካከቷ ከጓደኞቿ ጋር አጣላት፡፡

ሐ. ህጻኗ አምርራ አለቀሰች፡፡

ሠ. ህይወቷን ለልጆቿ አሳልፋ ሰጠች፡፡

ረ. ቢራራ ተንሸራቶ ወደቀ፡፡

ሰ. ወላጆች በልጆቻቸው ስኬት ይደሰታሉ፡፡

፫. የሚከተሉትን ቃላት ተሻጋሪና ኢ-ተሻጋሪ ግሶች መሆናቸውን በመለየት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ተኛ

ለ. ፈነጨ

ሐ. ነቃች

መ. ደበደበ

ሠ. ዘመረች

ረ. ነቀፈች

ሰ. ዓፈ

ሸ. ሞተ

ቀ. ላከ

በ. ወደደ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ‹‹የታላላቆች ሚና›› በሚል ስለደብዳቤ ምንነትና አይነቶች ተረድታችኋል፡፡ በመሆኑም ደብዳቤ ሰዎች ሃሳባቸውን በተሳካ መልኩ በጽሁፍ የሚለዋወጡበት ሲሆን የግል ወይም የሰላምታ እና የስራ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ በመባል በሁለት እንደሚከፈል አይታችኋል፡፡ የስራ ደብዳቤ የራሱ ቅርጽ እነዳለው በምሳሌ አስደግፋችሁ ካያችሁ በኋላም ለማንኛውም ጉደይ ማስፈጸሚያ የሚሆን የስራ ደብዳቤ መጻፍ መቻል እንዳለባችሁ አይታችኋል፡፡

ቃላትን ከጥገኛ ምዕላዶች ጋር በማቀናጀት ትርጉም ያላቸው ቃላት መጻፍ ችላችኋል፡፡ በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሰዋስዋዊ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ የሚገኙ ቃላትን በማስተካከል የተቃና ዓረፍተ ነገር መስርታችኋ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተሻጋሪና ኢተሸጋሪ ግሶችን ምንነት ተምራችኋል፡፡ ተሸጋሪ ግሶች ከተሳቢ ስም ጋር እየተዋቀሩ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርቱ ግሶች ሲሆኑ ኢተሸጋሪ ግሶች ተሳቢ ስም እንደማያስፈልጋቸው ተምራችኋል፡፡ እነዚህን ግሶች ከአረፍተ ነገር ውስጥ መለየት ችላችኋል፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

፩. በአካባቢያችሁ ከምትቀርቧቸው ታላላቆቻችሁ መካከል ከአንድ ሰው ጋር በመሄድ በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሃሳብ እንዲሰጧችሁ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፪. በትምህርት ቤታችሁ የተመለከታችሁትን አንድ ጉዳይ የሚመለከተው አካል እንዲፈታለችሁ በማሰብ የስራ ደብዳቤ ፃፉ፡፡

፫. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ሳቢ ወይም ኢሳቢ በማለት ፃፉ፡፡

ሀ. ነቃ

ለ. ሰረቀ

ሐ. ገዛ

መ. በላ

ሠ. ተደሰተ

፬. በስራ ደብዳቤ ጊዜ አይቀሬ የሆኑ ነጥቦችን ዘርዝራችሁ አብራሩ።

፭. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ከአምስት ያላነሱ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አለሚቱ | ወደ | ወጣ | ራቢያ | አጠና | ከ |
| ትናንት | መጽሐፍ | ሽለሙት | ሰማች | ክፉኛ | ሄደች |
| ጎበዝ | ጠንካራ | አንደኛ | ቤቷ | ዘሪሁን | ረበሸ |
| ቶሎ | ልጁ | ስለ | መጣች | ወላጆቹ | ደፈነ |
| ትምህርት ቤት | እንደ | ተባረረ | አህመድ | ተዝናና | ተደሰተች |

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁየምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ንግግርን በማድመጥ የፅሁፉን ዋና ሀሳብ መተንተን እችላለሁ ። | | | |
| 2. | በክርክር በመሳተፍ ስርዓቱን የጠበቀ ክርክር ማቅረብና ምክንያታዊ ዳኝነት መስጠት እችላለሁ። | | | |
| 3. | ጽሁፍን በማንበብ ጭምቅ ሃሳቡን እንደገና መፃፍ እችላለሁ። | | | |
| 4. | የስራ ደብዳቤ ማካተት ያለበትን ነጥቦች | | | |
| 5. | አውቃያለሁ።ማመልከቻ ወይም የስራ ደብዳቤ እጽፋለሁ። | | | |
| 6. | ቃላትን በመገጣጠም ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ። | | | |
| 7. | ተሸጋሪና ኢተሸጋሪ ግሶችን መለየት እችላለሁ። | | | |
| 8. | ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ በመጨመር ትርጉም ያለው ቃል መመስረት እችላለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋች ሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።።

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት (፯) ረጅም ልቦለድ

የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የልቦለድ ዋና ሀሳብን ዘርዝር አድርገው ታብራራላችሁ፡፡
- የልቦለድ ክፍሎችን ታብራራላችሁ፡፡
- የልቦለድ ባህሪያትን ትለያላችሁ፡፡
- በልቦለድ ውስጥ የሚገኝ አንድ የተወሰነ ክፍልን ለይታችሁ እንደገና ትጽፋላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

## የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ረጅም ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ ያነበባችሁትን ልቦለድ ውስጥ የምታስታውሷቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

፪. በልቦለዶቹ ውስጥ ምስል ከሳች ስልትን ቃላት በመጠቀም ሃሳብ ሲያሰፍረሩ አይረሴ የሆነባችሁን ተናገሩ

፫. መምህራችሁ አንድ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ ያነቡላችኋል፡፡ ከዚያ በፊት ግን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጥሞና አንብቧቸው፤ ጥያቄዎቹን ካነበባችሁ በኋላ ጽሁፉ ሲነበብላችሁ እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ፤ በመቀጠል ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. በዝናቡ ውስጥ የሚፈነጩት ህፃናት የባለጊታሩን ትኩረት የሳቡት በምን ምክንያት ነው?

ለ. በወጀብና ውሽንፍር በታጀበው ዶፍ ዝናብ ውስጥ ባህር ዳር ከተማ አውራ ጎዳና የታየው ምን አይነት ሰው ነው?

ሐ. ዶክተር ሚራዥ ለህፃናቱ ሰላምታ ሰጥቷቸው በጭብጨባ ከተሰናበቱት በኋላ ጉዞውን ያደረገው ወደ የት ነው?

መ. ዶክተር ሚራዥ የጎጃምና ጎንደር ኩታ መጋጠሚያ ቦታ ላይ መሆኑን ያወቀው በምን ምክንያት ነው?

# ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ልቦለድ ምንድን ነው? ስለምንነቱ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ፈልጋችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ በቡድን ተወያዩበት፡፡ የደረሳችሁበትን ድምዳሜም ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፪. ልቦለድ በውስጡ የሚዛቸውን ፍሬ ሃሳቦች በጥንድ ከተወያያችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ በቃል አስረዱ።

፫. የልቦለድ ባህሪያትን ዘርዝራችሁ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡ።

፬. የሚከተለውን አጭር ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን የልቦለድ አለባውያን ለይታችሁ በማውጣት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩባቸው።

ከባድ ዝናብ ያረገዘው የሀምሌ ሰማይ አጣዳፊ ምጥ ይዞት በጣር ያጉረመርማል። አዲስ አበባ ጥቁር የጉም ብርድ ልብስ ለብሳለች። በጥፊ የሚማታ ቀዝቃዛ፤ስለታም ንፋስ እያፏጭ የሽምጥ ክንፍ አውጥቶ ይበራል። ዛፎችና ቅጠሎች የዛር ዳንኪራ እየረገጡ ይወዛወዛሉ።

ጠብ ያለህ በዳቦ እያለ ሲፎክር ከመጣው፤ አህያ ከማይችለው ዝናብ ለማምለጥ እግረኞች ወደየቤታቸው ወይም መጠለያ ካለው ሱቅ ለመጠጋት ይሮጣሉ፤ ወፎች ጫጫታቸውንና እልልታቸውን ትተው ወደየጎጇቸው ይበራሉ። ሁሉም ወደሰማይ እያየ ሲሮጥ፤ ሽብር የመጣ ይመስል ነበር።

ያለርህራሄ በጥፊ የሚማታው ንፋስ አቧራ አንስቶ ሰው ዓይን ውስጥ እየሞጀረ፤ የሴቶችን ቀሚስ ወደላይ እየገለበና ጃንጥላቸውን ከእጃቸው ለመንጥቅ እየታገለ መንገደኞችን ይተናኮላል። ንፋሱ ከራሱ ላይ የነጠቀውን ባርኔጣ የሚያባርር አንድ መላጣ ሰው አይቶ አበራ ፈገግ አለ። ከታች የሚመጣ አንድ ሰው ባርኔጣውን ባይዝለት ኖሮ ሰውየው መቆሚያ አልነበረውም።

(በአሉ ግርማ ፤ከአድማስ ባሻገር፣2010፣109)

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

## ልቦለድ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ልቦለድን ከኢልቦድ የሚለይበትን ባህርይ በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. የልቦለድ አይነቶች ምን ምን ይባላሉ? ልዩነታቸውን አጭሩ አስረዱ፡፡

ሐ. የልቦለድ አላባውያን ውስጥ ታሪክና የትም ምንነታቸው ምንድን ነው?

ልቦለድ

ልቦለድ ከተፈጸመና ሊፈጸም ከሚችል የግለሰብና የማህበረሰብ የህይወት ገጠመኝ ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚንጸባረቁበት፣ በቃላት አማካኝነት የሚቀርብ ምናባዊ የሆነ የፈጠራ ስራ ነው፡፡ ይህ የስነ ጽሁፍ ዘርፍ በእውኑ አለም የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች አጠቃላይ ሰዋዊ ባህሪያትና ክንዋኔዎች እውነት አስመስሎ በገጸባህሪያት አማካኝነት የሚያቀርብ ነው፡፡ ስለዚህ የሰውን አጠቃላይ የህይወት መልኮች (ሀዘንና ደስታ፣ ምኞትና ፍላጎት፣ እድገትና ውድቀት ወዘተ.) በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የስነጽሁፍ አይነት ነው፡፡ በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገጸባህሪያት ህይወት በእውኑ አለም በእርግጥ የተፈጸመ ወይም ታሪኩ በሚያቅፈው ዘመንና ቦት እንዳለ የታየ አይደለም ማለት ነው፡፡ ደራሲው በልቦለዱ ውስጥ ግን የዘመኑን ባህል፣ ማህበረሰባዊ እውነታና ቋንቋ በግልጽ ያሳየናል፡፡

ልቦለድ የገሀዱን አለም እውነት ውበት ባለው ፈጠራዊ መንገድ በማቅረቡ ከሌሎች ጽሁፎች ይለያል፡፡ ሕይወት፣እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ መቅረቡ ጽሁፉን ተነባቢና ሳቢ ያደርገዋል፡፡ በልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ የህይወት ገጠመኞች በገሀዱ አለም ላይ የተከሰቱ ወይም ይከሰታሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው፡፡ ገጸ ባህሪያቱም የገሃዱን አለም ሰዎች አጠቃላይ ሰዋዊ ማንነት ንጸባርቃሉ፡፡ ደራሲው ሲጽፍም ከእውነታው አያፈነግጥም ፤ ለማፈንገጥ ሞክር እንኳ በሰዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት አናሳ ይሆናል፡፡ ሌላው ጉዳይ ደራሲው ምናባዊ አስተውሎቱን ተጠቅሞ ሲጽፍ ቃላቱን በአግባቡ መርጦና ሳቢ የሃሳብ ፍሰትን ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

አንድ ልቦለድ የተዋጣለት እንዲሆን ሁሉንም የልቦለድ አላባዊያን ወይም ፍሬ ነገሮች መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ አላባውያኑም ታሪክ፣ ትልም፣ ግጭት፣ ገጸባህርያት፣ መቼት፣ ጭብጥና አንጻር ናቸው፡፡

ታሪክ በጊዜና ድርጊት ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶች ትረካና የልቦለዱ መሠረት ወይም ቀዳሚ ነገር ነው። ታሪክ ምን ምን ሆነ? ምን ምን ተረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው። የልቦለድ ታሪክ ሰው ምን አነበብክ ተብሎ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ወይም ለሌላ ሰው የሚያካፍለው ትረካ ነው። ስለሆነም የድረጊቶች አነሳስ፣ አፈጻጸምና የመጨረሻ ውጤት ተዓማኒነትና አንጊነት እንዲኖረው ከሰው ልጅ እውነተኛ ገጠመን የተቀዳ መሆን ይጠበቅበታል።

ትልም (ሴራ) የልቦለድ መዋቅር ግንባታ ሲሆን የልቦለድ ቁልፍ ነገር ወይም አፅም በመባል ይታወቃል። ትልም በልቦለድ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች በምክንያትና ውጤት መተሳሰራቸውን የሚያሳይ አላባ ሲሆን ምን ለምን ሆነ /ተደረገ/ ብለን በመጠየቅ የምናገኘው ምላሽ ነው። ትልም እንደ ታሪክ በጊዜና ድርጊት ቅደም ተከተል የተከናወኑ ሁነቶች ትረካ ቢሆንም ድርጊቱ ምክንያታዊ ነው። የአንድ ልቦለድ ልብ አንጠልጣይነት የሚመዘነውም በሴራው ነው። ትልቁን የልቦለድ ታሪክ የፈጠሩት በርካታ ሁነቶች አንዳቸው ከአንዳቸው እየተንሰላሰሉ ግጭት ይፈጥራሉ፤ ግጭቱም ሌላ ግጭት ሊያስከትል ይችላል። ሴራ ወይም አጽመ ታሪክ (ምሰሶ) በመባልም ይታወቃል። ሴራው ልል ወይም ጥብቅ፣ ነጠላ ወይም ድርብ ሊሆን ይችላል።

መቼት ገጸባህሪያት የሚንቀሳቀሱትና ታሪካቸውን የሚፈጽሙት ደራሲው በመረጠው የተወሰነ አካባቢና ወቅት ሲሆን የሚኖሩበትና ታሪካቸውን የሚፈጽሙበት ጊዜና ቦታ ያስፈልጋቸዋል። መቼት አገርን፣ ሀይማኖትን፣ ፖለቲካን፣ ባህላዊና መንፈሳዊ አኗኗርን፣ትምህርትን፣ ተዝናኖትን፣ የኑሮ ደረጃንና የመሳሰሉትን ሁሉ ይይዛል። ስለዚህ መቼት ታሪኩ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜ ከነጓዙ ሲሆን ደራሲው ይህን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት። ጊዜ ገጸባህርያት የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሲሆን ጓዞቹም ወቅት፣ ዘመንና ሰዓት ሊሆኑ ይችላሉ። ቦታ ደግሞ ታሪኩ የሚፈጸምበት ወይም ገጸባህርያት የሚመላለሱበት መልክዓ ምድር ወይም አካባቢ ነው። ከመልክዓ ምድር ባሻገር ተጠቃሽ የቦታ ጓዞች መገልገያ ቁሳቁስ፣ አለባስ፣ ባህልና ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

ግጭት በገጸባህሪያት ዓላማና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት ወይም አለመስማማት ነው፡፡ ግጭት ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ድረስ የሚያልፍባቸው ደረጃዎች ተመጣጣኝ ተጻራሪ ኃይላት፣ ሰበበ ግጭት፣ ፍልሚያ፣ ጡዘት፣ ልቀትና ለውጥ ናቸው፡፡ ግጭት በባህሪው በበቂ መንስኤ ላይ የተመሰረተ፣ ተኣማኒ የሆነ፣ ልብ ሰቀላ ያለውና ታሪኩን ወደፊት የሚያራምድ መሆን አለበት፡፡

ግጭትየልቦለድ ታሪኩ የጀርባ አጥንት ሲሆን የግጭት ዓይነቶችም አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ገጸባህሪ ከራሱ ጋር- ኅሊናዊ/ስነልቦናዊ/ ግጭት ፣ ገጸባህሪ ከሰው (ሌላ ገጸባህሪ) ወይም ከማህበረሰቡ ጋር ፣ገጸባህሪ ከፈጣሪው ጋርና ገጸባህሪ ከተረጥሮ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ጋር ጋር(እንስሳትና አራዊት፣ ከአየር ጠባይ፣ እጽዋት፣ የውሀ አካላት...) ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው! ስንት የልቦለድ አላባውያንን ተገነዘባችሁ፡፡ቀጥሎ በቀረቡት አንቀጾችስ ምን ምን ነጥቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

ገጸባህርይ ደራሲው በቀነበበላቸው የልቦለድ ዓለም ውስጥ ስጋ ለብሰው፣ ባህሪ ተጎናጽፈውና መጠሪያ ተሰጥቷቸው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው የሚንቀሳቀሱ፣ የሚራቡ፣ የሚጠሙ፣ የሚፋቀሩ፣ የሚጣሉ፣ የሚሞቱ፣ የሚደሰቱ፣ የሚያዝኑና የዕውኑ ዓለም ሰዎች የሚፈጽሙትና አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አምሳለ ሰብዕ ናቸው፡፡ ገጸባህሪያት ልቦለዱ ከተቀነበበበት ቦታና ዘመን ካሉ ሰዎች የፈለቁ ወኪሎች ሲሆኑ በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ፣ ባህልና ማህበራዊ ልማድ፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ፡፡ ስለዚህ ገጸባህሪያት ደራሲው በህይወት ገጠመኙ ካያቸውና ካወቃቸው የተለያዩ ሰዎች የቃረማቸውን ባህሪያት የሚያስቀምጥበት ምናባዊ ፍጡር ነው፡፡

ጭብጥ የማህበረሰቡ የአኗኗር ስርዓትና ደረጃ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ነጸብራቅ ነው፡፡ ስለሆነም ጭብጥ ደራሲው በድርሰቱ ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ወይም ይዞት የሚቀርበው ቁምነገር ነው፡፡ ጭብጥ የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት በማንጸባረቅ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ልቦለድ በተለይም ረጅም ልቦለድ በውስጡ በርካታ ጭብጦችን ወይም ርእሰ ጉዳዮችን ይዞ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ጭብጥን ለማግኘትም ገጸባህርያት የሚገቡበትን ኩነትና ንግግር መፈተሽ፣ የገጸባህርያትን መቼት መዳሰስ፣ የደራሲውን ገለጻ መመርመርና ገጸባህርያት የሚገቡበትን ግጭት መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

የትረካ አንጻር በልቦለድ ውስጥ ታሪኩ የሚቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው፡፡ ታሪኩን የሚተርከው ማን ነው፣ ከታሪኩ ጋርስ ያለው ግንኙነት ምንድን ነው፣ የተተረከውስ ከማን አኳያ ነው ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ አንጻሩ ሦስተኛ መደብ (ሁሉን አወቅ ወይም ውስን ሁሉን አወቅ)፣ አንደኛ መደብ የትረካ አንጻር ወይም ተውኔታዊ የትረካ አንጻር / ተራኪው በገጸባህሪያቱ ድርጊትም ሆነ ሆነቶች ምንም አይነት አስተያየት የማይሰጥበትና ገጸባህሪያቱ ራሳቸው የሚያቀርቧቸው/ ሊሆን ይችላል፡፡

ልቦለድ አጭርና ረጅም በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ አጭር ልቦለድ አንድ የትኩረት ነጥብ ያለው፣ የታመቀና ጥብቅ ትስስር ያለው አጭር የፈጠራ ስራ ነው፡፡ ረጅም ልቦለድ ደግሞ ከቅርጽና ይዘት አንጻር ሰፊና በርካታ ክልሎችንና ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ መጠነ ርዕዩ ሰፊ በመሆኑ የሕይወትን ልዩ ልዩ መልኮች በጥልቀት ለአንባቢያን ያቀርባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁሉንም የልቦለድ አላባውያን ሰፊ በሆነ መልኩ የማቅረብ እድል ያለው የፈጠራ ስራ ነው፡፡

አጭርና ረጅም ልቦለድ ሁለቱም ዝርዋዊ የፈጠራዊ ድርሰቶች በመሆናቸው፣ የልቦለድን ፍሬ ነገሮችን /አላባዊያን/ እና ዘዴዎችን በመያዛቸው እንዲሁም የሕይወት መልኮችን በማንጸባረቃቸው ይመሳሰላሉ፡፡ ነገር ግን አጭር ልቦለድ ጥቂት ገጸባህርያት፣ አንድና ነጠላ ጭብጥ፣ ውስንና ጠባብ መቼት፣ ነጠላና

ያልተውሰበሰበ ታሪክ፣ ትልምና ግጭት አለው፤ ጥድፊያ የጠበቀ አንድነትና በመጠኑ አጭርነት ይታይበታል፡፡ ረጅም ልቦለድ አንድ ወይም ሁለት አብይ ጭብጥና በርካታ ንኡሳን ጭብጦችን ያቀርባል፤ በርካታ ገጸባህሪያት ስላሉት ውስብስብና የገጸባህርያቱን ሕይወት ከልደት እስከሞት ቀስብሎ እየተረከ የሚያቀርብ ረጅም ታሪክ አለው፤ አንድ ወይም ሁለት አብይ ገጸባህሪና በርካታ ንኡሳን ገጸባህርያትን በውስጡ ይይዛል፤ ሰፊ የጊዜና የቦታ ገለጻ ያቀርባል፤ በርካታና ውስብስብ የገጸባህሪያት ግጭት የታይበታል፤ትልሙም ውስብስብ ነው፡፡

(ዘሪሁን አስፋው፣ 2002፣ 152-204)

አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ ካለው ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ በንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. በልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ የህይወት ገጠመኞች በገሀዱ አለም ላይ የተከሰቱ ብቻ ናቸው፡፡

ለ. የልቦለድ ታሪክ ተዓማኒነትና አኅጊነት እንዲኖረው ከሰው ልጅ እውነተኛ ገጠመኝ የተቀዳ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ሐ. ልቦለድ ተጨባጭ እውቀትን ለማስተላለፍ የሚጻፍ ዝርዋዊ ስራ ነው፡፡

መ. አጭርና ረጅም ልቦለድ ተመሳሳይ የልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡

ሠ. አንድን ልቦለድ አንብበን በመልዕክትነት የምንወስደው የልቦለድ አላባ ጭብጥ ነው፡፡

ረ. የልቦለድ ታሪክ በምክንያትና ውጤት መተሳሰሩን የሚያሳይ አላባ መቼት ይባላል፡፡

፪. ቀጥሎ ከላይ ካለው ንባብ የወጡ የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል። ንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ስለ ልቦለድ ገጸባህሪያት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ገጸባህሪያት በደራሲዎች የሚፈጠሩ የምናብ ሰዎች ናቸው።
   ለ. በልቦለድ ውስጥ የሚቀርበው ታሪክ የገጸባህሪያቱ ነው።
   ሐ. ገጸባህሪያትን በገሀዱ አለም ላይ ብንፈልጋቸው ልናገኛቸው እንችላለን።
   መ. በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ፣ ባህል እንዲሁም መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ።
2. በልቦለድ ውስጥ መቼት ________________ ነው።
   ሀ. የልቦለዱ ታሪክ የሚፈጽምበት ስፍሪያ ሐ. ልቦለዱ የሚተረክበት ግንባር
   ለ. የልቦለዱ ታሪክ የሚጠነጠንበት ቁምነገር መ. በልቦለድ ውስጥ ያለ ግጭት
3. ረጅም ልቦለድን የማይመለከተው አማራጭ የትኛው ነው?
   ሀ. አንድ ወይም ሁለት ዋና እና በርካታ ንኡሳን ጭብጦችን ያቀርባል።
   ለ. የገጸባህርያቱን ሕይወት ከልደት እስከሞት ቀስ ብሎ እየተረከ ያቀርባል።
   ሐ. በውስን መቼት ላይ የሚንቀሳቀሱ ውስን ገጸባህሪያትይኖሩታል።
   መ. በርካታና ውስብስብ የገጸባህሪያት ግጭት የታይበታል።
4. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ልቦለድ ጽሁፍን በትክክል የሚገጸው የትኛው ነው?
   ሀ. እውነተኛዎቹን የሰው ልጅ የህይወት ፈርጆች በጽፍ ቀርፆ ያሳያል።
   ለ. የገጸባህሪያቱ ህይወት በዕውኑ አለም ላይ በእርግጥ የተፈጸመ ነው።
   ሐ. ታሪኩ በሚያቅፈው ዘመንና ቦታ በእውን የታየና የተከሰተ ነው።
   መ. የሰውን ልጅ ህይወት ልዩ ልዩ መስኮች በተመሳስሎ ቀርፆ ያሳያል።

5. የልቦለድ አጽም ወይም ምሰሶ በመባል የሚታወቀው የልቦለድ አላባ የትኛው ነው?

ሀ. ታሪክ ለ. ትልም ሐ. ግጭት መ. ገፀባህሪ

፫. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ‹‹ልቦለድ በቁሙ እውነት ያልሆነ የስነጽሁፍ አይነት ነው›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. ረጅም ልቦለድ ከአጭር ልቦለድ የሚለይባቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ፡፡

ሐ. የልቦለድን ጭብጥ እንዴት ማግኘት እንደምንችል ምሳሌ በመጥቀስ አስረዱ፡፡

መ.‹‹በልቦለድ ሕይወት፣ እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ ይቀርባል›› የሚለውን ሀሳብ አብራሩ፡፡

ሠ. ግጭት የልቦለድ የጀርባ አጥንት የተባለው ልምንድን ነው? አስረዱ፡፡

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. አንድ የታተመ ልቦለድ ቤታችሁ በማንበብ እያንዳንዱን የልቦለድ አላባውያን አውጥታችሁ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

፪. ከአነበባችሁት ልቦለድ ውስጥ ዋና ገጸባህሪውን/ዋን/ ለይታችሁ በኋላ ዋና ያላችሁበትን በምክንያት በቃል አቅርቡ፡፡

### የልቦለድ ዘዴዎች

ሀ. ስታነቡ ከገጠማችሁ የልቦለድ አጻጻፍ ዘዴ በመነሳት የልቦለድ ዘዴች የሚባሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

በልቦለድ ጽሁፍ ውስጥ አራት ዋና ዋና የአተራረክ ዘዴዎች ቴክኒኮች አሉ፡፡ እነሱም፡- ምልልስ፣ ምልሰት፣ ገለጻና ንግር ናቸው፡፡

ሀ. ምልልስ

በእውኑ ዓለም በልቦለድ ገጸባህሪያት መካከል የሚደረግ የሃሳብ ወይም የንግግር መለዋወጥ ምልልስ በመባል ይታወቃል። ምልልስ የገፀባህሪያቱን ማንነት፣ ችግር፣ ስሜት፣ ዓላማና ስነልቦናዊ መልክ ማሳያ ነው። ምልልስ ግልፅ፣ ማራኪ እንዲሁም ከታሪኩ ትልም ጋር ከተቀናጀ ለረጅም ልቦለድ ለዛ ከሚያጎናፅፉት ውስጥ አንዱ ይሆናል።

ለ. ገለጻ

ስለ ገጸባህሪያቱ ቁመና፣ መልክ፣ አለባበስ፣ ስሜት፣ አካባቢያቸው፣ ስለሚፈፅሟቸው ድርጊቶች ወዘተ ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት ሲሆን ተደራሲያን ገፀባህሪያቱን በጥልቀት እንዲያውቁ ይረዳል። ከታሪኩና ከገጸባህሪያቱ ጋር የተያያዘ ዓላማ ያለውና የሚፈለገውን ነገር በግልፅ የሚያሳይ እንዲሁም የተመረጠና ከሌሎቹ የአተራረክ ዘዴዎች ጋር በውል ተጣምሮ ይቀርባል ።

ሐ. ምልሰት

የገጸባህሪያቱን ገጠመኝ፣ አስተሳሰብ፣ ማንነት፣ና የቀደመ ስሜት ወደኋላ በመመለስ ቀንጭቦ በማምጣት የአሁኑን የስብዕና መሰረታቸውን ለማሳየት የሚረዳ የአተራረክ ዘዴ ነው። በምልሰት በሚተረክበት ጊዜ ያለፈው ታሪክና አሁን የሚተረከው በጠበቀ ሁኔታ ተሳስረው ይቀርቡበታል።

መ. ንግር፡-

ወደፊት ስለሚፈጸም አንዳች ድርጊት ጥቆማ በመስጠት አንባቢያን ታሪኩን በጉጉት እንዲያነቡት የሚያደርግ ነው። ንግር ጥበባዊ በሆነ መንገድ ስለትልሙ አካሄድ፣ ስለግጭቱ ሁኔታ፣ ስለገፀባህሪያቱ ማንነትና በታሪኩ ውስጥ ስለሚገጥማቸው አቢይ ነገር አስቀድሞ ለአንባቢ ፍንጭ ይሰጣል።

፫. አንድ ልቦለድ በማንበብ የልቦለድ የአጻጻፍ ዘዴውን ለይታሁ በማውጣት በምሳሌ አስደግፋችሁ አስዱ።

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### የቃላት መጥበቅና መላላት

አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ ከቃላቱ ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍች ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ድምፆች በቃሉ መካከል ወይም መጨረሻ ላይ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የቃል መጀመሪያ ድምጽ ጠብቆ አይነበብም፡፡ እንደ እነዚህ አይነት ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት የፍቺ ልዩነት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ሁኔታውን በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ አስገብተን እንመልከት፡፡

አባይ፡- ሀ. በአፍሪካ ረጅሙ ወንዝ አባይ ነው፡፡

ለ. ዓባይ እናቷ ስለታመመች ዛሬ ትምህርት ቤት አልመጣችም፡፡

ሐ. ልጁ አባይ መሆኑ ሰዎች ይጠሉታል፡፡

በምሳሌ ሀ እና ለ የወንዝ እና የተጸውኦ ስም ሲሆን ይህም ጠብቀው የሚነበቡ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ምሳሌ ሐ ላልቶ ስለሚነበብ ዋሾ የሚል ፍቺ እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

፩. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ በሚያስገኙት ፍቺ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | ቃል | ሲላላ | ሲጠብቅ |
| | ጥሬ | ያልበሰለ | ለፍቼ |

- ለምለም ያልበሰለ በቆሎ እሸት ገዝታ መጣች፡፡
- ይህንን ገንዘብ ያገኘሁት ለፍቼ ነው፡፡

ሀ. የሚያርሰው

ለ. በራ

ሐ. ሽፍታ

መ. ከዳኝ

ሠ. ይጣላል

፬. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመሩባቸውን ቃላት የገቡበት ዓውድ በመጥበቅና ወይም በመላላት መሆኑን ጻፉ፡፡

ሀ. ጎበዟ ተማሪ የሰው ችግር በቀላሉ ይገባታል፡፡

ለ. ሰነፉ ተማሪ በሰው ውጤት ቀና፡፡

ሐ. ከፋ ከቡና መገኛ ቦታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

መ. ተማሪዋን በስስት አያት፡፡

ሠ. የበዛብህ አማት ፊታውራሪ መሸሻ ቁጡ ናቸው፡፡

፭. ልቦለድ በሚለው ምንባብ ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍቺ ልዩነት የሚያስከትሉ አምስት ቃላትን በመፈለግ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

ሀ. ሰዋስዋዊ ስህተት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ሰውስዋዊ ስህተቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ አለመስማማት፣ የተሳቢ አመልካች ካለቦታዋ መግባት ወይም መቅረት፣ የእምር አመልች መቅረት ወይም ያለቦታዋ መግባት፣ እንዲሁም የሀረግ አለመጣጣም ወዘተ... የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ስህተቶችን አስተካለን እና ተጠንቅቀን ካልጻፍናቸው መልዕክቱ ሊፋለስ ወይም ሊደበዝዝ ይችላለል፡፡

ለምሳሌ፡- ትናንትና የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰች፡፡

በዚህ ዓረፍት ነገር ውስጥ የታየው ሰዋስዋዊ ችግር የጾታ አለመመጣጠን ነው፡፡ በመሆኑም በሁለት መንገድ ሊስተካከል ይችላል፡፡ በወንድ ወይም በሴት አንቀጽ ማስተካል እንችላለን፡፡

ትናንትና የመጣው ልጅ ዛሬ ተመለሰ፡፡

ትናንት የመጣችው ልጅ ዛሬ ተመለሰች፡፡

፩. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሰዋስው ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ችግሮችን (የመደብ የጾታ፣ የቁጥር፣ እምር አመልካች እንዲሁም የተሳቢ አመልካች ያለቦተዋ መግባት ወይም መቅረት) እያላችሁ በመለየት ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ገበሬው በሬው ሸጠ፡

ለ. ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃሉ፡፡

ሐ. ኢትዮጵያ የተለያዩ የአትክልት አይነቶችን ያመርታል፡፡

መ. አካባቢን ማጽዳት ተላላፊ በሽታ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

ሠ. ሯጭ ልጅ በፍጥነት እየሮጠ መጣ፡፡

፪. በሚገተለው አጭር ጽሁፍ ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ስህተት እንደገና አስተካላችሁ ጻፉ፡፡

መረን ለቀቅ ቋንቋ አጠቃቀመም ከማህበራዊ ገጽታ አንጻር ሲታይ አሉታዊ መልክ ጎልቶ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ተግባትን ባያደናቅፍም ማሻከሩ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ የቋንቋ አጠቃቀማ ላይ ሊስተካል የሚገባ ነው፡፡ ወጣት አክብሮ ሰውን መጥራት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃኑን ታላላቅ ለመልካም ቅርርባችን አንተ/ አንቺ እያለ መጥራት በቅድሚ ይመርጣል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ረጅም ልቦለድ ተምራችኋል፡፡ ስለሆነም የልቦለድ ምንነት፣ አላባውያን፣ አይነቶችና ዘዴዎች ተረድታችኋል፡፡ ልቦለድ የገሀዱን አለም አጠቃላይ እንቅስቃሴ በገፀባህሪያት አማካኝነት የሚያቀርብ የፈጠራ ስራ እንደሆነም ተምራችኋል፡፡ በመሆኑን ልቦለድ ታሪክ፣ ገፀባህሪያት፣ ግጭት፣ መቼት፣ ጭብጥ፣ ትልምና የትረካ አንፃር የተባሉ ፍሬ ነገሮችን ሲይዝ ማቅረቢያ ዘዴዎቹ ደግሞ ገለፃ፣ ምልሰት፣ንግርና ምልልስ ነቸው፡፡ በዚህ መሰረትም የልቦለድ አላባዊያንና ዘዴዎችን በማስረጃ በማስደገፍ መግለጽ ችላችኋል፤ ከልቦለድ ውስጥ ሁሉንም የልቦለድ አላባውያን ለይታችሁ አሳይታችኋል፡፡

ልቦለድ የገሀዱን አለም እውነት ውበት ባለው ፈጠራዊ መንገድ በማቅረቡ ከሌሎች ጽሁፎች ይለያል፡፡ ሕይወት፣እውነትና ውበት በተቀናጀ መልኩ መቅረቡ ጽሁፉን ተነባቢና ሳቢ እንደሚያደርገውም በማስረጃ በማስደገፍ አይታችኋል፡፡ ልቦለድ ረጅምና አጭር በመባል በሁለት እነደሚከፈልም ተምራችኋል፡፡ ስለሆነም በሁለቱ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መጥቀስ ችላችኋል፡፡ አጭር ልቦለድ በሁሉም አላባዎቹ ቁጥብነት የሚታይበት ሲሆን ረጅም ልቦለድ ግን የገፀባህሪያቱን ህይወት ከልደት እስከ ሞት የሚተርክበት ረጅም ጊዜ ስላለው አላባውያኑም በሰፊው ይቀርባሉ፡፡ በተማራችሁት መሰረትም ለረጅምና አጭር ልበለድ የተለያዩ ምሳሌዎች መስጠት ችላችኋል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ በቃልም ሆነ በአረፍተ ነገር ደረጃ የትርጉም ለውጥ ሊያመጡ እንደሚችሉም ተምራችኋል፡፡ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶች (የቁጥር፤ የጾታ፣ የመደብ አለመስማማት፣ የተሳቢ አመልካች ካለቦታዋ መግባት ወይም መቅረት፣ የእምር አመልች መቅረት ወይም ያለቦታዋ መግባት፣ እንዲሁም የሀረግ አለመጣጣም ... ) እንደሚያጋጥሙም አይታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ከልቦለድ አላባውያን መካከል ትልምና ግጭት ለአንድ ልቦለድ መዋቅር ያላቸውን ጠቀሜታ በጽሁፍ አብራሩ፡፡

፪. ጠብቀውና ላልተው በመነበብ የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ አምስት ቃላትን (መማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ ከተጠቀሱ ቃላት ውጪ) በመፃፍ በዓረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ፡፡

፫. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያለውን ሰዋስዋዊ ስህተት በመለየት ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ጓደኛዬ የገዛችው ቀሚስ መልኩ አልወደድኩትም፡፡

ለ. ጎበዙ ልጅ ፈተና አለፈች፡፡

ሐ. ህፃን ልጅ ቃላቶችን አቀላጥፎ መናገር ችሏል፡፡

መ. ልጆች በእረፍት ሰዓታቸው መጫወት ያስፈልጋል፡፡

፬. ‹‹የልቦለድ ጭብጥ የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት በማንጸባረቅ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ መሆን ይጠበቅበታል›› የሚለውን ሀሳብ ምሳሌ በመጥቀስ አብራሩ፡፡

፭. ከልቦለድ ዘዴዎች መካከል ገለፃ ምን እንደሆነ አብራርታችሁ ፃፉና ከአንድ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ገለፃን የሚያሳይ ምሳሌ ቀንጭባችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

የግንዛቤ ማስተካከያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የልቦለድ ምንነትን ማብራራት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የልቦለድ አላባዊያንና ዘዴዎችን ምንነት በማስረጃ በማስደገፍ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የልቦለድ ባህሪያትን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ አንድነትና ልዩነት መጥቀስ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ለረጅምና አጭር ልበለድ የተለያዩ ምሳሌዎችን መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6. | በልቦለድ ውስጥ የሚገኙ አላባውያንን መለየትና ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7. | ሁሉንም የልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎች ተጠቅሜ ልቦለድ መፃፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8. | የልቦለድ ጭብጥን መተንተን እችላለሁ፡፡ | | | |
| 9. | በመጥበቅና በመላላት የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ቃላትን መለየት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 10. | በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን መለየት እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት (፰)
# ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- በቃል የተላለፍን መልዕክት በጥሞና በማዳመጥ የማጠቃለያ ሀሳብ ትሰጣላችሁ፡፡
- የተሰጣቸውን ንግግር አዳምጣችሁ ምክረ ሀሳብ (አስተያየት) ትሰጣላችሁ፡፡
- የፅሁፉን ዋና ፍሬ ሃሳብ በማንበብ ትለያላችሁ፡፡
- ምክንያታዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ መልኩ አከራካሪ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- የፅሁፍን ዓውድ በመጠበቅ ተመሳሳይና ተቃራኒ ትርጉሞችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- ጊዜ ገላጭ ግሶችን በትክክል ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

### የተውልድ ቅብብሎሽ

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በአንድ ሀገር ውስጥ ከሚኖሩ ህዝቦች መካከል የበለጠ ተቀባይነት ያላቸው በየትኛው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ዜጎች ናቸው?

፪. ሀገራችን እንደተጠበቀች ለተተኪው ትውልድ እንድትደርስ ማድረግ ያለበት የትኛው የህብረተሰብ ክፍል ነው? ለምን?

፫. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት የሚሰጡትን ፍች በቡድን በመወያየት ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ወይፈን | መ. ሐረግ |
| ለ. አጣማጅ | ሠ. ሰንሰለት |
| ሐ. መቀናጀ | ረ. ጨልሌ |

፬. መምህራችሁ ‹‹የትውልድ ቅብብሎሽ›› የሚል አንድ አጭር ጽሁፍ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡ ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት በምንባቡ የሚነሱ ነጥቦች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምታችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡ ምንባቡ ሲነበብላችሁ ማስታወሻ በመያዝ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ለመስራት ተዘጋጁ፡፡

#### አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. ‹‹ወይፈኖች የሚገሩት በበሬ ነው›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. በአዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት አጣማጅ የሚለው ቃል የሚወክለው ምንን ነው?

ሐ. ‹‹የዛሬዎቹ እንደ ትናንትናዎቹ እንሆናለን፤ በዛሬዎቹም ላይ የነገዎቹ አሉ›› የሚለውን ሃሳብ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

መ. ‹‹የእኛ ተባብሮ አለመስራት ለአንዳንድ ጨልሌዎች ያመች ይሆናል›› ሲል ምን ማለቱ ነው? እኛ የተባሉትስ እነማን ናቸው? አብራሩ፡፡

ሠ. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምን እንደሆነ በአጭሩ ጻፉ፡፡

## ክፍል ሁለት (፪) መናገር

፩. ቀጥሎ ከቀረቡላችሁ የመከራከሪያ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ፤ መምህራችሁ በሚመሰርቱላችሁ ቡድን መሠረት ዳኛ መርጣችሁ ምክንያታዊ ሃሳብ በማመንጨት ክርክር አድርጉ፡፡

ሀ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከጥቅሙና ከጉዳት የትኛው ያመዝናል?

ለ. ስልጣኔ በባህል ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ምንድን ነው? (አዎንታዊው ወይስ አሉታዊው )

ሐ. ምስጢራዊ ሃሳቦችን ለማስተላለፍ ከንግግር እና ከጽሁፍ የትኛው የተሻለ ነው?

፪. በማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን የቀረበን የስፖርት ዜና በማዳመጥ መደምደሚያ/ ማጠቃለያ ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡ በምትጽፉበት ጊዜ ጠቃሚውን ብቻ መምረጥ እንዳለባችሁ አትዘንጉ፡፡

፫. ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከመጻሕፍት ወዘተ.) ስለመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ያዳመጣችሁትን /የምታውቁትን/ መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፬. የሀገራችን የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ከእውነተኛ ህይወታችሁ ጋር በማዛመድ አስተያየት /ሂስ/ በማድረግ ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### መገናኛ ብዙኀን

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

፩. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ማለት ምን ማለት ነው? የሚባሉት እነማን ናቸው፡፡

፬. በመገናኛ ብዙኀን እና በማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

፫. ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

### መገናኛ ብዙኀን

መገናኛ ብዙኀን መልዕክትን በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ አንባቢያን፣ አድማጮች ወይም ተመልካቾች የማሰራጫ መሳሪያ ነው። ዘዴው በዋነኛነት ህብረተሰብን ተደራሽ ያደረጉ መረጃዎች በተደራጀና በተቀናጀ አሰራር በተለያዩ የግንኙነት አግባቦች የሚደርሱበት ተግባቦታዊ ሂደት ነው።

የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች ሶስት ናቸው። እነሱም፡- የህትመት የመገናኛ ብዙኀን፣ የብሮድካስት /ኤሌክትሮኒክስ/ መገናኛ ብዙኀንና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ናቸው። የህትመት የመገናኛ ብዙኀን ጥንታዊው /ቀዳሚው/ ሲሆን በቃላትና በስዕል ወይም በዕይታ አማካኝነት መልዕክትን ያስተላልፋል። ይህ የመገናኛ ዘዴ መማርን የሚጠይቅና እያየን ለማንበብ የሚያስችል ነው። በ፲፰፻፺፩ ዓ.ም በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት አዕምሮ በተሰኘ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጋዜጣ ጥቅም ላይ መዋል ጀምሮ በአሁኑ ወቅት በሰፊው እያገለገለ ያለ የመገናኛ ብዙኀን አይነት ነው። ጋዜጣ፣ መጽሄት፣ በራሪ ወረቀትና የመሳሰሉት ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

የብሮድካስት መገናኛ ብዙኀን በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ሲሆኑ ዜና አስተላላፊው እየተናገረ ወደ ተመልካቹ በጆሮ እና በአይን አማካኝነት መልዕክትን የሚያደርሱ ናቸው። እነዚህ ዘዴዎች በተንቀሳቃሽና በማይንቀሳቀሱ ፎቶ ግራፎችና ስዕሎች አማካኝነት በጥምረት ወይም በተናጠል ታግዘው መቅረብ የሚችሉ ሲሆኑ ቴሌቭዥንና ሬዲዮን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል።

ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉት ደግሞ እንደ ህትመት መገናኛ ብዙኀን

መማርን የሚጠይቁ፣ እያየን ለማንበብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም የማየት ወይም የማንበብ የመገናኛ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰሩ ሲሆን በህትመትም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መተላለፍ የሚችሉትን ጽሁፎች፣ ንግግሮች እንዲሁም ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ፎቶግራፎችና ስዕሎችን አንድ ላይ አቀነባብረው ወይም ለያይተው ማቅረብ የሚችሉ ናቸው፡፡ እንደኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እያዳመጥን ወይም እያየን መልዕክት የምንቀበልባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን ከህትመት መገናኛ ብዙኀንም ሆነ ከኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኀን የሚወስዱት የጋራ ባህርይ አለ፡፡ እንደ ፌስቡክ፣ ዋትስአፕ፣ ኢሜል፣ ቲዊተር፣ ቴሌግራም፣ ኢሞ፣ ኢንስታግራም፣ ዩቲዩብ፣ ቫይበር፣ ሜሴንጀር፣ ቲክቶክና ወዘተ. በማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡

ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን በመላው ዓለም በተለይም በወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ በጣም ተንሰራፍቶ ይገኛል፡፡ ዓላማቸው ሰዎችን እርስ በእርስ ማገናኘትና ማግባባት ነው፡፡ አንዳንድ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ተመሳሳይ ፍላጎቶች ያላቸውን ሰዎች እንዲያገናኙ ወይም ሃሳብ እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም ሰው ይጠቀምበታል ማለት አይደለም፡፡

አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና ከላይ ካነበባችሁት ጽሁፍ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት አንቀጾችስ ምን ላይ ያተኩራሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ፡፡

መገናኛ ብዙኀን የሚሰጧቸው ጠቀሜታዎች የሚባሉት ወቅታዊ ዜናዎችንና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማድረስ፤ የሀገር መልካም ገጽታ እንደ ባህል፣ ታሪክ፣ እድገት ወዘተ.. ለሌላው ዓለም ለማጋራት፤ የተለያዩ የንግድ ተቋማትንና ድርጅቶችን ማስተዋወቅ፤ ወዳጅነትን ለመፍጠር በተጨማሪም ለመዝናኛነትና ለግለሰቦች መተዳደሪያ ወይም የገቢ ምንጭ ሆኖ ወዘተ... ያገለግላል፡፡

በማህበራዊ በይነ መረብ ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር እንድገናኝ

ይረዱናል፤ ተጠቃሚዎች ለጓደኞቻቸው የሚያጋሯቸውን ነገሮች ሁሉ በቅጽበት እንዲመለከቱ ያስችላቸዋል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከጓደኞቻቸው፣ ከሚያስደስቷቸው ዝነኞች እና ከሚከተሏቸው ሰዎች ጋር የሚያገናኙ ብቻ አይደሉም፤ የሚያዝናኑ ጨዋታዎችም ብቻ አይደሉም፤ ብዙዎቹ የተለመዱ ማህበራዊ መገናኛ መድረኮች ብዙ ችግሮች አሉባቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የማይፈለግ መረጃ፣ ራስን ማመቻች (ለራስ ማተኮር)፣ የሀሰት ዜና፣ ከመጠን በላይ መጫን፣ የግላዊ ምስጢር ብክነት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ጥሩ ያልሆኑ ይዘቶችን በመጥለፍ ለአይፈለጌ መልእክተኞች በቀላሉ ይደርሳሉ፡፡ ይህም ሲባል የሚሰራጩ መረጃዎች ሁሉን ያማከሉ ባለመሆናቸው የአንዱን ሃሳብ በሌላው ላይ መጫን ስለሚሆን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ከመጠን በላይ መረጃዎች ከተለያየ ምንጪ ስለሚሰራጩና አዲስ ድረ ገጾችን አስመስሎ የመለጠፍና ከሌላ በመውሰድ የሐሰት የዜና ዘገባዎችን ያራምዳሉ፡፡ መጀመሪያ ላይ የውሸት መረጃዎች መሆናቸውን ሳያጣሩ የተዛባ መረጃ ተቀብለው ለሌሎች በማስተላለፍ ችግር ይፈጠራል፡፡

የመረጃ ተዓማኒነት የጎደላቸው ሃሳቦች በቀላሉ ይደርሳሉ፤ በጣም ብዙ የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጓደኞሞች በማፍራት ያልተፈለገ ህይወትን መምራትና ከመብዛታቸው የተነሳ ለመከታተል መቸገር፤ የሚያስተላልፏቸው የራሳቸውን ዒላማ ከግብ ለማድረስም ምስል በመጫን በዚህ ዘዴ ላይ ማሰራጨት ይፈልጋሉ፡፡

ሌላው ብዙ የደህንነት መጠበቂያ እርምጃዎች ቢኖሩም ማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ይጠለፋሉ፡፡ ለምሳሌ የግል መረጃቸውን በሚፈልጉት መልኩ እንዲጠብቁ የሚፈልጓቸውን የግል አማራጮች ሁሉ አያቀርቡም፡፡ ሁላችንም በሞባይል መሳሪያዎቻችንና በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ላይ መስተጋብር ፈጥረን እንገናኛለን፡፡ ይህ ደግሞ ሁልጊዜ ውጤታ ማስለማይሆን የግለሰቦች መረጃ ምስጢራዊነቱን ያጣል፡፡ ሁልጊዜ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ወቅቱን የጠበቀ ዜናዎችንና መረጃዎችን

ለህብረተሰቡ ማድረስ፣ የሀገርን እድገት፣ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ ለሌሎች ማስተዋወቅ፤ የሀገርን ደህንነትና ሰላም ማስጠበቅ፤ የተለያዩ የንግድ ተቋማትንና ድርጅቶችን ማስተዋወቅ የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገል ወዘተ የሚባሉት የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ ሲሆኑ ጉዳቱ ደግሞ የባህል መበረዝን ያስከትላል፤ በህብረተሰቡ ላይ ሽብርን ይፈጥራል፤ የገበያ አለመረጋጋትን ያስከትላል፤ የወገናዊነት ስሜት ይንጸባረቅባቸዋል፤ የአንድን ሀገር ሰላም የሚያደፈርሱ እና ከእውነታ የራቁ ዜናዎችን ያሰራጫሉ። ስለሆነም እኛ የአሁኑ ዘመን ትውልዶች የሚጠቅሙንንና ለራሳችን ብሎም ለአገር እድገት ፋይዳ ያላቸውን የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን መርጠን የመጠቀም ትልቅ ኃላፊነት አለብን።

አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባብ የወጡ ናቸው። ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ።

ሀ. የህትመት መገናኛ ብዙኀንና ማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉት መማርን የሚጠይቁ ናቸው።

ለ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን እንደኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እያዳመጥን ወይም እያየን መልዕክት የምንቀበልባቸው ናቸው።

ሐ. በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት አዕምሮ የመጀመሪያው ጋዜጣ ከማህበራዊ የመገናኛ ብዙኀን መካከል የሚጠቀስ ነው።

መ. ማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከሚተችባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ወቅቱን የጠበቀ ዜናዎችንና መረጃዎችን ለህብረተሰቡ አለማድረሱ ነው።

ሠ. መገናኛ ብዙኀን በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ አንባቢያንና አድማጮች የማሰራጨት አቅማቸው ከፍተኛ ነው።

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት አድርጋችሁ ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልሱን በመምረጥ ማብራሪያ ስጡ።

1. በተንቀሳቃሽና በማይንቀሳቀሱ ፎቶ ግራፎችና ስዕሎች አማካኝነት በጥምረት ወይም በተናጠል ታግዘው መቅረብ የሚችል የትኛው ነው።

   ሀ. ሬዲዮ ሐ. መጽሔት

   ለ. ቴሌብዥን መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት አንዱ ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ትክክል ነው።

   ሀ. ወቅቱን የጠበቀ ዜናዎችን ማድረሳቸው

   ለ. የገበያ አለመረጋጋትን ለመከላከል አሉታዊ አስተዋጽኦ አለው፤

   ሐ. የወገናዊነት ስሜት ስለማይንጸባረቅባቸው ለአንድነት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው፡

   መ. የሀገርን እድገት፣ ባህል፣ ታሪክ አለማስተዋወቁ

3. ከማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ስር የማይካተተው የመገናኛ ብዙኀን አይነት የትነኛው ነው።

   ሀ. ፌስቡክ ለ. ቲክቶክ

   ሐ. ኢሜል መ. መልስ የለም

4. ከሚከተሉት አንዱ መገናኛ ብዙኀን በተመለከተ ስህተት ነው።

   ሀ. በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኀን የተጀመረው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መስግስት ይሁን እንጂ ከዚያ በፊትም ኢመደበኛ በሆነ መልኩ ነበረ።

   ለ. እንደ ምንባቡ ሞባይል በሁላችንም እጅ ይገኛል።

   ሐ. በአሁኑ ወቅት በሰፊው እያገለገለ ያለ የመገናኛ ብዙኀን አይነት አንዱ ጋዜጣ ነው።

   መ. የግለሰቦችን ምስጢር ቢያባክንም በቡድኖች መካከል መስተጋብር ለመፍጠር አዎንታዊ አስተዋጽኦ አለው።

5. የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን በርካታ ጓደኞች በማፍራት <u>ያልተፈለገ ህይወትን መምራት</u> ሲል ምን ማለቱ ነው።

ሀ. የተቀራረቡት ለመጥፎ ተግባር መሆኑን

ለ. በችግር ውስጥ መኖርን

ሐ. የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ዓላማ መሳትን

መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡

፫. በጥንድ በመሆን ‹‹መገናኛ ብዙኀን›› በሚለው ምንባብ ውስጥ ስለ መገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

፬. ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ከዚህ በፊት የምታውቁትን በምንባቡ ውስጥ ከአገኛችሁት ሃሳብ ጋር በማነጻጸር በጽሁፍ አስተያየት/ሂስ/ ስጡበት፡፡

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. ድርሰት ምንድን ነው? ከአሁን በፊት የተማራችሁትን በማስታወስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፪. የድርሰት አይነቶችን በመዘርዘር ልዩነታቸውን በጽሁፍ አስረዱ፡፡

**የድርሰት አይነቶች**

ድርሰት በስርዓት የተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮች ወይም አንቀጾች ሊመሰርቱት የሚችሉ ጽሁፍ ነው፡፡ ከድርሰት ዓይነቶች ውስጥ አመዛዛኝና ገላጭ ድርሰትን እንመልከት፡፡

ሀ. ገላጭ ድርሰት

የአንድን ነገር ምንነት፣ አሰራር፣ ቅርፅ፣ መጠን ወዘተ. በግልፅ የሚያሳይ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመለክት ወይም የሚመራ ድርሰት ገላጭ ድርሰት ይባላል፡፡ ገላጭ ድርሰትን ለመገንዘብ ይረዳን ዘንድ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

ምሳሌ፡- ነፋስ በአይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ሲነፍስ ስሜቱ ለፍጥረት ሁሉ የሚሰማ ነው፡፡ ይህ በራሪ አየር ተለይተው ከታወቁት አየሮች ከኩሬና በሀይቅ፣ ከባህርና ከፈሳሾች በፀሀይ ሀይል ተነስቶ በአየር ውስጥ ከሚዛወረው እንፋሎት፣ ከአትክልት ርግፍጋፊ፣ ከአቧራ በአየር ውስጥ ከሚገኙት ከጥቃቅን ነገሮችና ከትናንሽ ተባዮች ይመሰረታል፡፡

ለ. አመዛዛኝ ድርሰት

አከራካሪ ስለሆኑ ጉደዮች የሚጽፍ፣ አድማጩን(አንባቢውን) የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሀሰትነት ለማሳመን የሚጥር የድርሰት ዓይነት ነው። ስለሆነም ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን ክፉም ሆነ ደግ የትኛው እንደሚበልጥ ወይም እንደሚሻል ወዘተ የሚያሳይ ነው። አንባቢን ይዞት ከነበረው አቋም የሚመልስ በመሆኑ ሰባኪ ድርሰት ነው።

ምሳሌ፡- መድሀኒት ቀማሚና ደራሲ የሚለያዩበት ነጥብ አለ። ቀማሚ በአይን የሚታዩትንና በእጅ የሚዳሰሱትን ነገሮች እያሰባሰበና በእጁ እየገለበጠ ስለሚቀምማቸው ነው። ደራሲ ግን በአእምሮ እየሰበሰበና እየቀረፀ ይፅፋል እንጂ እንደቀማሚ በእጁ አይዳስሳቸውም ባይኑም አያያቸውም። ከተጠቀሱት ምክንያቶች በስተቀር እየሰበሰቡ ቀምሞና አዘጋጅቶ ለህዝብ በመስጠት ግን ሁለቱም አንድ ናቸው።

፫. የሚከተሉት አንቀጾች በየትኛው ድርሰት አይነት እንደሚመደቡ በየግላችሁ ከሰራችሁ በኃላ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ ምክንያታችሁን በጽሁፍ አስፍሩ።

ሀ. እውነት ጦቢያ እጅግ ያማረች፣ እጅግ የጠተበች እጅግ የተደነቀች ላያት ሁሉ የምታነሆልል የምታዘናጋ ነበረች። ዓይኗን አስቀድሞ የብር አሎሎ መስሎ ካጥቢ ኮከብ የተፎካከረ ነበር። በዚህ ላይ ግማሽ ሽፋሽፍቷ እንደ በልግ ሳር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስል ነበር። አፍንጫዋ ቀጥ ያለ፣ ከንፈሯ መፈንዳት የጀመረ የማለዳ ፅጌረዳ ይመስል ነበር። እንደ ወንድ የተቆረጠችው ጠጉርዋ እንደ ሰኔ ቡቃያ  ወይም እንዳዲስ መሬት ጤፍ እየጋሸበ የሀር ነዶ መሰለ። በፀሐይና በውርጪ የተጎሳቆለውና የጠቆረው ፊቷ እያሸለተ ሀጫ በረዶ ከመሰለው ጥርሷ ጋር ገና ከርቁ እየጠቀሰ ከተሸሸገበት ሴትነቷን ያሳጣባት ጀመር።

(አፍወርቅ ገብረየሱስ 1958፡64)

ለ. በሀረር አካባቢ የተወለዱት አቶ መንግስቱ ለማ በልጅነታቸው የዜማና የቅኔ ትምህርት ቀስመዋል፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሀረር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ ተከታትለዋል፤ ከዚያም ወደ ውጪ ሀገር በመሄድ ከፍተኛ ትምህርት የተከታተሉ ሲሆን ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በልዩ ልዩ መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል።

ሐ. ማንጠግቦሽ በዚህ ሙያዋ ሳውቃት ጥቂት ወራት አልፈውኛል። የድምጧ ቅላጼዋ የምታወርደው ግጥም ዘወትር ይማርከኛል። ያን ትንሽ ጠጅ ቤትም ማዘውተር የጀመርኩት ለእርሷ ስል ነው። ከድምጧ በተጨማሪ ሰው አክባሪነቷ እና ትህትናዋ በእንደኔ ያለ ሰው ተወዳጅ አድርጓታል።

መ. ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት የሚበጃት ዜጎች በራሳቸው መፍትሔ ሲፈልጉ ነው። ባዕድ በቀየሰው መንገድ መጓዝ ሀገሪቱን ፈጹም አይጠቅማትም፤ ህዝቡ የራሱን እደ ጥበብና ፈጠራ እንዲሁም የስራ ፍቅር ማሳደግ አለበት። ይህ ከሆነ ኢትዮጵያ ከድህነት ልትላቀቅ ትችላለች። በእርግጥ ኢትዮጵያ ከኃላቀርነት ለመውጣት የተሻለ አማራጭ የሚሆናት ከውጭ ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት መመስረትና ጥሩ ብድርና እርዳታ የምታገኝበትን መንገድ መቀየስ ነው። ሌሎች ሀገራት ያለቸውን ያህል የተቀበረ ማዕድን የሌላት ሀገር ድህነትን በራሷ ተፍጨርጭራ ታሸንፋለች ማለት ዘበት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ይህ አስተሳሰብ በራሱ ኋላቀር አስተሳሰብ ነው።

የጥገኝነት አስሳሰብ ሰዎች በራሳቸው መተማን እንዳይኖራቸው ኋላፊነትን የሚቀበሉና የሚወጡ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ነው። ሰዎች የችገራቸውንና የጎደላቸውን ከሌሎች መቀባለቸው ያለ ቢሆንም የጠባቂነትና የተረጅነትን መንፈስን የሚዳብር በመሆኑ ፍጹም የሚደገፍ አይደለም። ጉዳዩን ወደሀገር ሰፋ አድርገን ስንመለከተውም ተመሳሳይ መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን። ደሀ የሚባሉ ሀገራት ከድህነት ለመውጣት ብቸኛ አማራጫቸው በራሳቸው ሀብትና ህዝብ መጠቀም ነው።

፬. ከሚከተሉት ርዕሶች ሁለቱን በመምረጥ ከላይ የቀረበውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ አመዛዛኝና ገላጭ ድርሰት ጻፉ፤ የጻፋችሁትንም ለክፍል ጓደኞቻሁ አንቡቡላቸው ፡፡

ሀ. አትክልትንና ስጋ መመገብ

ለ. ከዛሬ ነገ ይበልጣል

ሐ. የደሮ ወጥ አሰራር

መ. አዲስ አበባ ቤቴ

፭ .በጣም የምትወዱትን ሰው ወይም አካባቢ መርጣችሁ ርዕስ በመሰየም ባለሶስት

አንቀጽ ገላጭ ድርሰት ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

፮ .የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን አጠቃቀምን በተመለከተ (ገጠመኛችሁን ወይም ያዳመጣችሁትን) ምክንያታዊ ቅደም ተከትልን በጠበቀ መልኩ የተሟላ አከራካሪ ድርሰት ጻፉ፡፡

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

ሀ. እማሬያዊ ፍች፡- ግልፅና ቀጥተኛ እንዲሁም የቃሉ የመጀመሪያ ፍቺ /ትርጉም/ የያዘ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ሀ. ተኩላ የሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺው የዱር እንስሳ የሚል ነው፡፡

ለ. ባህር እማሬያዊ ፍቺ የተኛ ውሃ የሚል ነው፡፡

ለ. ፍካሬያዊ ፍች፡- ከቀጥተኛ ፍቻቸው በተጨማሪ በተደራቢነት የሚይዙት ምስጢራዊ ወይም ስውር ፍች ነው፡፡ ለምሳሌ ተኩላ የሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺው ነጣቂ የሚል ሲሆን ከእማሬያዊ ትርጉሙ በተደራቢነት ሲይዝ በ‹‹ለ›› ላይ የቀረበው ባህር የሚለው ፍካሬያዊ ፍቹ ሰፊ የሚል ትርጉም ይዟል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u> ሁሉም ቃላት እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍቺ ይኖራቸዋል ማለት አይደለም፡፡

፩. የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍቾቻቸውን በሰንጠረዡ በቀረበው ምሳሌው መሰረት ሙሉ።

| ተ.ቁ | ቃል | እማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| | እፉኝት | የእባብ ዝርያ | መርዘኛ |
| | ወርቅ | ውድ ማዕድን | ሸጋ፣ቆንጆ |
| 1. | ሳር | | |
| 2. | ዱባ | | |
| 3. | አንበሳ | | |
| 4. | ንብ | | |
| 5. | እስስት | | |
| 6. | ቋንጣ | | |

፪ .እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸው አምስት ቃላትን ሰብስባችሁ በሚከተለው ሰንጠረዥ አስፍሩ።

| ተ.ቁ | ቃል | እማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |
| 4. | | | |
| 5. | | | |

ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት በተሰጣቸው ፍቺ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡- ቃሪያ ( እማሬያዊ) = ቃሪያ አዘውትሮ መመገብ ለጤና ተስማሚ ነው።

መሬት (ፍካሬያዊ) = ኃላፊው መሬት ነው።

ሀ. ድንች (ፍካሬያዊ)

ለ. ኩራዝ (እማሬያዊ)

ሐ. ቁልፍ (ፍካሬያዊ)

መ. እንቁ (እማሬያዊ)

ሠ. ኤሊ (ፍካሬያዊ)

ረ. በግ (እማሬያዊ)

፫. ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ስጡና ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ሊቅ = ተመሳሳይ ፍቺ = የተማረ፣ምሁር-

ሀገራችን የብዙ ምሁር መፍለቂያ ናት፡፡

ሀ. ልጨኛ

ለ. መግነጢስ

ሐ. ነዳይ

መ. ሁዳድ

ሠ. ባይተዋር

ረ. መርህ

ሰ. ጓጓ

ሸ. ነቂስ

፬. ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቆፈን = ተቃራኒ ፍቺ = ሙቀት

የዓለም ሙቀት መጨመር ብዙ ሀገራትን እያስጨነቀ ነው፡፡

ሀ. ምርት

ለ. ቀልባም

ሐ. በሳል

መ. ብልጥ

ሠ. ጨዋ

ረ. አልፋ

ሰ. ባዝራ

ሸ. ለም

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

፩. የግስ ጊዜ ስባል ምን ማለት ይመስላችኋል? የግስ ጊዜ የሚባሉት በመዘርዘር በምሳሌ አስረዱ፡፡

የግስ ጊዜ

ጊዜ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈፀም የሚገልፅ የግስ ባህሪ ነው፡፡ ጊዜ በሶስት ሊከፈል ይችላል፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የአሁን ጊዜ

ለ. ሀላፊ ጊዜ

ሐ. የትንቢት ጊዜ

ሀ. የአሁን ጊዜ

አንድ በአሁኑ ጊዜ የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁነትን የሚገልፅ የጊዜ ዓይነት ነው፡፡ የአሁን ጊዜ የሆነ ግስ "እየ- " የሚል ምዕላድ ሲያስቀድምና "--ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ትህትና ቁርስ እየ-ሰራች ነው፡፡

ለ. መሸሻ እራቱን እየ-በላ ነው፡፡

ሐ. ዮሀንስ አስ-ተማሪ ነው፡፡

ለ. የኃላፊ ጊዜ

አንድ ድርጊት ከአሁን በፊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን የሚገልፅ የጊዜ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ሀሊማ ትናንት ሁለት በግ ሸጠች፡፡

ለ. ዘርትሁን አንድ ፎቅ ሰራች፡፡

ሐ. የትንቢት ጊዜ

አንድ ድርጊት ገና ያልተፈፀመና ወደፊት የሚፈፀም መሆኑን ይገልፃል፡፡ የሚገለፀውም በጊዜ ተውሳከ ግስና ‹‹ -አል›› በሚለው ረዳት ግስ አማካኝነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. በልዩ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች፡፡(ትሄድ-አለች)

ለ. ገዛኸኝ ነገ ወደ ጎንደር ይሄዳል፡፡(ይሄድ-አል)

፪. በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ግሶች የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ጊዜያት መሆናቸውን እየተወያያችሁ በምሳሌ እያስደገፋችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

ሀ. ይመጣል

ለ. ፈራ

ሐ. ሰብስቧል

መ. ነበር

ሠ. ደረሰች

ረ. አለፈ

ሰ. ይሸፍን

ሸ. እየጸዳ ነው

፫. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶችን የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ጊዜ መሆናቸውን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ሀ. ኤደን እየሮጠች መጣች፡፡

ለ. የዳመናውን መጥቆር ለተመለከተው ዛሬ ይዘንባል፡፡

ሐ. መምህራችን የቤት ስራ ሰጥተውን ነበር፡፡

መ. ጎበዙ ተማሪ በሰራው ስራ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ተደስቷል፡፡

ሠ. ቃሉን ጠብቆ እየኖረ ነው፡፡

፬. ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በቡድን በመሆን ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ቅጥያዎችን በመጨመር የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ግሶችን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የኃላፊ ጊዜ | የአሁን ጊዜ | የትንቢት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| | አመሰገነ | እያመሰገነ ነው | ያመስግናል |
| 1. | | እየተኛ ነው | |
| 2. | ጻፈች | | |
| 3. | | | ይዘፍናል |
| 4. | | እየሰበረ ነው | |
| 5. | ገሰጸ | | |
| 6. | | | ይገኛል |

አንዳንድ ግሶች የኃላፊ እና የአሁን ጊዜ ግሶች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ረዳት ግስ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ምሳሌ: ልጁ እየበላ ነው፡፡ በ ‹‹እየ-- ነው›› ምክንያት የአሁን ጊዜ መሆናቸውን ሲያመለክት በአንጻሩ ደግሞ ልጁ እየበላ ነበር፡፡ በ ‹‹እየ--- ነበር›› በተመለከትነው ሰዓት እየበላ ነበር፡፡ ዓረፍተ ነገሩ የሚያሳየው የኃላፊ ጊዜ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ድርጊቱ ማቋረጡን (መጨረሱን ) ያላረጋገጠ ሃሳብ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ተምራችኋል፡፡ በተለይም ስለ መገናኛ ብዙኀን ምንነት፣ ዓይነቶችና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት የሚሉትን ተረድታችኋል፡፡

የድርሰት አይነቶች በስርዓት የተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮች ወይም አንቀጾች ሊመሰርቱት የሚችሉ ጽሁፍ እንደሆነ ተረድታችኋል፡፡ በመቀጠል ከድርሰት ዓይነቶች መካከል አመዛዛኝ /አከራካሪ/ ስለሆኑ ጉደዮች የሚጽፍ፣ አድማጩን(አንባቢን) የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሀሰትነት ለማሳመን የሚጥር ድርሰት እንደሆነ ተረድታችኋል፡፡ ገላጭ ድርሰት ደግሞ የአንድን ነገር ምንነት፣ አሰራር፣ ቅርፅ፣ መጠን ወዘተ. በግልፅ የሚያሳይ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመለክት ወይም የሚመራ ድርሰት እንደሆነ ተረድታችኋል፡፡ በመቀጠል በተሰጣችሁ የድርሰት ርዕስ የራሳችሁን ድርሰት ጽፋችኋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ስለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር መስርታችኋል፡፡ የግስ ጊዜ በተለይም የኃላፊ፣ የአሁንና የትንቢት ጊዜን ቃላትን እየተጠቀማችሁ ዓረፍ ነገር መስርታችኋል፡፡ የግስ ጊዜ የሚባሉ ቃላትን ለይታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. የመገናኛ ብዙኀን የሚባሉትን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ምሳሌዎችን በመጥቀስ በቃል አስረዱ፡፡

፪. መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣ ፌስቡክ፣ ኢሜል፣ ቴሌግራም፣ ቲክቶክና ወዘተ. በሚባሉት መገናኛ ብዙኀን መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

፫. የህትመት የመገናኛ ብዙኀንንና የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀንን በተመለከተ አጭር አመዛዛኝ ድርሰት በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፬. ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቾቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ነፋስ ሐ. ቆቅ

ለ. ዶማ መ. ጨለማ

፭. በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኙ ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቾቻቸውን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| | በደምሳሳው | በጥቅሉ | በነጠላዉ |
| | መናድ | ማፍረስ | መደርደር |
| 1. | ቆንቋና | | |
| 2. | ገሀድ | | |
| 3. | ጨቀነ፣ | | |
| 4. | ምርቃት | | |
| 5. | አዋቀረ | | |
| 6. | አውሸለሸለ | | |

፮. የግስ ጊዜን (የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት ጊዜ) የሚያሳዩ ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን ለእያንዳንዳቸው መስርቱ፡፡

የግንዛቤ ማስተካከያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የመገናኛ ብዙኀን አይነቶችን ተረድቼ መዘርዘር እችላለሁ:: | | | |
| 2. | የማህበራዊ መገናኛ ብዙኀን ጥቅምና ጉዳት ለይቻለሁ:: | | | |
| 3. | በቃል የተለያየን መልዕክት በጥሞና በማዳመጥ ማጠቃለያ ሀሳብ እሰጣለሁ :: | | | |
| 4. | በተለያዩ የመገናኛ ብዙኀን ላይ የሚተላለፉ አወዛጋቢ ንግግሮች ላይ ጠቃሚ የሆኑ ሂሶች መስጠት እችለላሁ:: | | | |
| 5. | የተለያዩ የማንበብ ስልቶችን በመተግበር ዋናውን ሀሳብ መለየት እችላለሁ:: | | | |
| 6. | ምክንያታዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ መልኩ ሙለ በሙለ አከራካሪና ገላጭ ድርሰት እጽፋለሁ:: | | | |
| 7. | የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት እችላለሁ:: | | | |
| 8. | ለተለተያዩ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ መርጬ እጠቀማለሁ :: | | | |
| 9 | በንግግር እና በጽሁፍ ውስጥ ሁሉንም የግዜ ግሶችን በትክክል በመጠቀም ለፈለጉት ውጤት መጠቀም እችላለሁ:: | | | |
| 9 | የግስ ጊዜያትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መመስረት እችላለሁ:: | | | |

፱. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

አማርኛ
፲ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ (፱) ሥራ ፈጠራ

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- አዳምጣችሁ በማስረጃ መስማማታቸውንና አለመስማማታቸውን ታሳያላችሁ፡፡
- ሀሳባችሁን በምክንያት በማስደገፍ በቃል ትገልጻላችሁ፡፡
- ፅሁፍ በማንበብ ለማን እንደ ተጻፈ ትለያላችሁ፡፡
- የአዳዲስ ቃሎቶችን ትርጉም ከፅሁፍ አውድ በመነሳት ትሰጣላችሁ፡፡
- በዓርፍተነገር ውስጥ ተሻጋሪ እና ኢተሻጋሪ ግሶችን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ (፩) ማዳመጥ

### አለቃዬ ስራዬ ነው፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ቤተሰቦቻችሁ ለትምህርታችሁ የሚሰጧችሁ ነጻነት እንዴት ይገለጻል? ሰው ነጻነት አጣ የሚባለው ምንምን ነገሮች ሲጎሉበት ነው፡፡

፪. የጉልበት ብዝበዛ ሲባል ምን ይመስላችኋል? መገለጫዎቹን ዘርዝሩ?

፫. ቤተሰቦቻችሁ ሙያ ሲያስለምዷችሁ በምን መልኩ ነው?

፬. ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ ‹‹አለቃዬ ስራዬ ነው›› የተሰኘ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተ ደግሞ ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት ሃሳባችሁን በመሰብሰብ ከሚቀርበው ሃሳብ አንጻር የምትስማሙበትና የማትስማሙበትን ነጥቦችን ማስታወሻ በመመዝገብ በጉዳዩ ላይ ለክፍል ጓደኞቻቸው የጻፋችሁትን በምክንያት አስደግፋችሁ በቃል አቅርቡ፡፡፡

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉት ቃላት ከምታዳምጡት የወጡ ናቸው፡፡ እናንተ ደግሞ አድምጣጭሁ ለቃላቶቹ አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| - አመድማዶ | - ደጋ |
| - ቢድበሰበሱም | - ፌር |
| - ትርግታ | - ንደፊ |

ለ. ትርፌ ያስጨነቃት ጉዳይ ምንድን ነው? ስንት ጥያቄስ እራሷን ጠየቀች?

ሐ. አውሱኝ ነፃነት፤ አልሙት በባርነት›› አለች፤ የሚለው ሃሳብ በእናት እይታ ምን ማለት ይስላችኋል?

መ. ትርፌ ሥራ የለመደችበትን መንገድ ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ምክንያታችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ለጓደኛችሁ በቃል አስረዱ፡፡

## ክፍል ሁለት(፪) መናገር

፩. የስራ ፈጠራ እና የስራ ፈላጊነትን ውይይት በማድረግ ግላዊ እይታችሁን በማንሳትና ምክንያታዊ በመሆን ሃሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. የስራ ፈጠራ ለወጣቶች የሚሰጠውን ጥቅም ወይም አስፈላጊነት በሀገር ዕድገት ላይ ያለውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ በቡድን ተወያዩባቸው፡፡

ዳቦ ጋጋሪና እንጨት አመላላሽ

አንድ ዕንጨት አመላላሽ አንድ ቀን ወደ ዳቦ ጋጋሪ ቤት ገብቶ ሳለ ጋጋሪው ከዳቦ ገዢ ገንዘቡን እቀበላለሁ ሲል ሌባ በጎን መጣና አንድ ዳቦ ሰርቆ ይዞ ሄደ፡፡ ይህም ዕንጨት አመላላሽ ሰውዬ ይከተለው ኑሮ ሩጦ ሂዶ ጉሮሮውን አንቆ ያዘና ዳቦውን ከሌባው አስጣለው፡፡

ዳቦ ጋጋሪውም ሰውዬው ይህን አይቶ ነበርና በማግስቱ ያንን ዕንጨት አመላላሽ ሰው አግኝቶ ትናንትና ከሌባው ያስጣልከውን ዳቦዬን ወዴት አደረስኸው ብሎ ቢጠይቀው በላሁት ብሎ መለሰለት፡፡ ዳቦ ጋጋሪውም እንግዲያማ ዳቦዬን ከበላህ የዳቦዬን ዋጋ አትሰጠኝም ብሎ ሲጠይቀው ስለ ምን ዋጋ እሰጥሃለው ሌባውን ተከትዬ እስክደክም ሩጬ ዳቦውን ከሌባው ያስጣልሁበት የድካሜ ዋጋ ነው አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ያ ዳቦ ጋጋሪ በነገሩ ተደንቆ ትላንትና በኔ ዘንድ ስንት ወንበዴዎች ኑረውብኝ ኑሯል ብሎ ተናገረ ይባላል፡፡

(ከበደ ሚካኤል ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ 1999 42-43)

፫. ከላይ የቀረበውን አጭር ተረትና ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ ከዳቦ ጋጋሪውና ከዕንጨት አመላላሹ የየትኛውን ሀሳብ እንዳከበራችሁ ለክፍል ጓደኞቻቻችሁ አጋሩ፡፡

## ክፍል ሶስት (፫) ንባብ

### እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት

#### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

፩. ስራ ፈጠራ ማለት ምን ማለት ነው?

፪. ስራ እንዴት ሊፈጠር እንደሚችል ታውቃላችሁ? ስራ ፈጠራ ጥቅሙስ ምንድን ነው?

፫. ስራ በመፍጠር ስኬታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው? የምታውቋቸውን የስራ እድል ፈጣሪዎች ጥቀሱ፡፡

፬. ቀጥሎ እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?



እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት

መስከረም ፫/፲፱፻፴፬ ዓ.ም በመንዝና ይፋት አውራጃ በማፉድ ወረዳ በስንቃ ውሀ ቀበሌ ለቤተሰቦቻቸው ፱ኛ ልጅ ሆነው ተወለዱ፡፡ በልጅነታቸው ዜማ ተምረው ድቁና ወስደው በ፯ና፰ ዓመታቸው ይቀድሱ ነበር፡፡ አባታቸው የቤተ ክህነት ትምህርትን ጠንቅቀው የተማሩ ባለቅኔ ሲሆኑ የሞቱትም በስራ ምክንያት አብረው ስላልነበሩ በደንብ ሳያውቋቸው በተወለዱ በአመታቸው በመሆኑ ያደጉት

በእናታቸውና በአያታቸው እጅ ነበር፡፡ እናታቸው ለዕድገታቸው ከመሰረቱ ጀምሮ ከፍተኛና መተኪያ የሌለው አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የቤተ ክህነት ሰው ቀጥረው እቤት ዳዊት ከማስተማራቸውም በላይ ቅኔ እንዲማሩም ልከዋቸዋል፡፡

ወደ አዲስ አበባ እንደመጡ ተስፋ ኮከብ አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው ተምረዋል፡፡ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ከተመልካችነት ተነስተው እስከመድረክ መሪነት፣ ተዋናይነትና አዘጋጅነት ደርሰዋል፡፡ በ፲፱፻፵፫ዓ.ም የቲያትር ክፍሉ ምክትል ዳይሬክተር ሁነው ነበር፡፡ ግጥምና ዜማንም ያዘጋጁ ነበር፡፡ በዚያም እየሰሩ ራሳቸውን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ የጀመሩበት ወሳኝ ወቅት በመሆኑ በምኒልክ ትምህርት ቤት መደበኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ጎን ለጎንም ማታ ማታ የቋንቋ ትምህርት ይማሩ ነበር፡፡ ሰባት የቴሌቪዥንና ሁለት የመድረክ ቲያትሮችን አሳይተዋል፡፡ ወደ ሱዳን፣ ሶቪየት ህብረትና ቻይና ሄደው አሳይተዋል፡፡

በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በግንቦት ወር በመድረክ አያያዝ ችሎታቸው የተደነቁት ሰዎች ወደ ብሄራዊ ሎተሪ ገብተው ማስታወቂያን ከልዩ ጥበብ ጋር ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያስተዋውቁ ረዷቸው፡፡ ወደ ልጅነት ህልማቸው ተመለሱ፡፡ ዥንጉርጉር አህያ ገዝተው የማስታወቂያ ክፍል ባልደረባ ሆና እንድትሰራ አደረጉ፡፡ ኬሻ ሙሉ ጭድ እያስጫኑ ከኬሻው ዙሪያ አልፎ አልፎ ቀዳዳ አበጅተውና የተወሰኑ የብር ኖቶች በየቀዳዳዎቹ ሽጠው ለተመልካች ሁለት ኬሻ ሙሉ ብር የሚመስለውን ጭነት በፊናንስ ፖሊሶች ግራና ቀኝ አሳጅበው እየነዱ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ‹‹ይህ ሁሉ ብር የእናንተ ነው፣ የአንድ ብር ሎተሪ ትኬት በመግዛት ይህን ሁሉ ብር ውሰዱ፡፡›› እያሉ ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ብሄራዊ ሎተሪን ለማስተዋወቅ ሌሎች ዘዴዎችን ፈጥረዋል፡፡

**አሁን ደግሞ ንባባችሁን ገታ አድርጉና እስካሁን ካነበባችሁት መንደርደሪያ ሃሳብ በመነሳት ስራ ለመፍጠር ቁርጠኝነት ያስፈልጋል ትላላችሁ?**

በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም የራሳቸውን አንበሳ ማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ድርጅትን በ!) ብር ካፒታል ፊሊፕስ ህንፃ ላይ ከፈቱ፡፡ በአቶ ውብሸት አገላለፅ ማስታወቂያ

የንግድ ማንቀሳቀሻ ሞተር የሆነ የአዕምሮ ስራ ውጤት ነው። ታማኝ በመሆን ደንበኞቹን መሳብ ይቻላል። ራስን ጠብቆ፣ ኮራ ብሎና ጥሩ ስራ ከሰሩ ደንበኞች ለዘላለም ያንተ ሆነው ይቀራሉ ይላሉ። ማስታወቂያ ከመስራቱ በፊት ባለሙያው በምርቱ ሊያምንበትና ሊቀበለው እንደሚገባ ይመክራሉ። ‹‹ስልጣን፣ ገንዘብና ታዋቂነት በጥንቃቄ ካልተያዙ አጥፊዎች ናቸው›› የሚሉት አቶ ውብሸት በሳቸው ህይወት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች አሳድረው ብዙ ጉዳት እንዳደረሱባቸው በግልፅ ይናገራሉ።

ከ፲፱፻፶፫ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ዘርፍና ንግድ ማህበራት ፕሬዝዳንት ሆነው ለ፲፪ ዓመታት በትጋት አገልግለዋል። ከዚያም በላይ ካላገለገልክ ተብለው የወጡት በልመና ነበር። ‹‹የኔ ፓርላማ ንግድ ምክር ቤት ነው ብዬ ነው የማምነው፣ እንደቤቴ ነው የማየው፣ እነሱም አንድም ቀን ለይተውኝ አያውቁም›› ይላሉ። በቢዝነሱ ከ፵ ዓመታት በላይ ቆይተዋል። በተለያዩ የአገር ጥሪዎች፣ የልማት፣ የጎርፍና የሌሎችንም ቴሌቶን ፕሮግራሞችን በሀላፊነት እየተመረጡ እየተመደቡና በህዝባዊ ኮሚቴዎች ውስጥም እየገቡ በስኬታማነት ማስተባበር የሚችሉ የህዝብ ይሉኝታና አክብሮት የሚለገሳቸው አስተባባሪ ናቸው።

በተለይ ወጣቶች ሲጋበዟቸው በሙሉ ፍቃደኝነት በምረቃዎች፣ በስበሰባዎችና በመሳሰሉት በመገኘት ሰፊ ልምዳቸውን በማካፈል ያነሳሳሉ፤ ያበረታታሉ፤ ይመክራሉ። ወጣቶችን ያላከበርኩ ማንን አከብራለሁ እያሉ ጥሪዎቻቸው ላይ እየተገኙ ያስተምሯቸዋል። ቢያንስ ፴ ምርቃቶች፣ ፵ ኤግዚቢሽኖች፣ ፫ የመጽሀፍት ምርቃቶች፣ ፲፫ የቁንጅና ውድድሮች ላይ ተገኝተው ንግግሮችን አድርገዋል።

በህይወታቸው አስመስሎ የሚኖር ሰው አይወዱም። የአገር ፍቅር ያለው ሰው ምሉዕ ነው። አገርን የማይወድ ሰው እናትና አባቱን ሊወድና ሊያፈቅር አይችልም። ካልሆነ አስመሳይ ነው። የሰው ልጅ ትንሽም ሆነ ትልቅ ደረጃ ላይ ይድረስ የራሱ ልጓም ሊኖረው ይገባል ይላሉ። አቶ ውብሸት ለራሳቸው መልካም ስራዎችና በቢዝነስ ባመጡት ለውጥ የሽልማት ጎርፍ ጎርፎላቸዋል። በአገር

ውስጥም በውጭም ተሸልመዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ መስከረም ፲፩/፲፱፻፹፩ዓ.ም ከቬንዚዌላ አዘጋጅ ኮሚቴ ሜርኩሪ ኢንተርናሽናል አዋርድን ተሸልመዋል፡፡ ለብዙ እውቅ መሪዎች የሚሰጠውን ይህን አለማቀፍ ሽልማት ከመሪዎች ውጭ በአፍሪካም ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸለሙና ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን አገርንም ያስከበሩ ሆነዋል፡፡ ብዙ መሪዎችና እውቅ ሰዎች በተገኙበት የተሸለሙ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ሆነውበታል፡፡ በክብር ካባቸው ላይ ነበር የወርቁ ሽልማት የተደረገላቸው፡፡ በአዲስ አበባ ወጣቶች፣ በጣሊያን፣ በዩኤስኤ፣ በመካከለኛው ምስራቅ የማስታወቂያ ማህበር፣ በአክሲማርስ፣ ከፊፋ ቴክኒክ ዳይሬክተሮች፣ በአሜሪካ ኤምባሲና በሌሎችም ተሸልመዋል፡፡ በተጨማሪም አለም አቀፍ ማን ማነው (Who is who )መዝገብ ላይ ስማቸው ሰፍሯል፡፡

(ዶ/ር ወሮታው በዛብህ፣ ለራስ ማን እንደራስ!!፣ 2008፣ 57-60 ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

አንብቦ መረዳት

፩. ቀጥሎ ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡ ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

ሀ. አቶ ውብሸት በስንት ዓመታቸው ነው ድቁና ወስደው ይቀድሱ የነበረው?

ለ. የመድረክ መሪ፣ ተዋናይና አዘጋጅ የነበሩት ማን ናቸው?

ሐ. በምንባቡ ውስጥ ለማስታወቂያነትና ለሌሎች ተግባራት ስታገለግል የነበረችው እንስሳ ማን ናት?

መ. በምንባቡ የተገለፀው የንግድ ማንቀሳቀሻ ሞተርና የአዕምሮ ስራ ውጤት የሆነው ምንድን ነው?

ሠ. አቶ ውብሸት ዛሬም ድረስ እንደቤቴ ነው የማየው የሚሉት ምኑን ነው?

ረ. አቶ ውብሸት በህይወታቸው የማይወዱት ምንድን ነው?

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን ‹‹እውነት›› ስህተቱን ‹‹ሀሰት›› በማለት ምክንያታችሁን በጽሁፍ አስረዱ፡፡

ሀ. ውብሸት ያደጉት በእናታቸውና በአያታቸው እጅ ስለነበር ስለአባታቸው እምብዛም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡

ለ. በምንባቡ ውስጥ አስራ ሰባት የቴሌቪዥንና አራት የመድረክ ቲያትሮች ታይተውበታል፡፡

ሐ. በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በመድረክ አያያዝ ችሎታቸው የተደነቁበት ወቅት ነበር፡፡

መ. የአንበሳ ማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ድርጅት በ ፳፻ ብር በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ተከፈተ፡፡

ሠ. ውብሸት በዓለም መድረክ የተለያዩ ሽለማቶችን አግኝተዋል፡፡

፫. ‹‹እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት‹‹ በሚል ርዕስ ያነበባችሁት ጽሁፍ ሰባት አንቀጾችን ይዟል፡፡ ከዚህ በታች በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን አንቀጾች በ‹‹ለ›› ስር ከተሰጡት የአንቀጾቹ ዋና ፍሬ ሀሳቦች ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. የተለያዩ ስራዎች የተከወኑበት |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. የስልጣንና የገንዘብ ሚና |
| 3. አንቀጽ ሶስት | ሐ. የትውልድ ጊዜ |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. የቤት እንስሳት የሰውን ገፀ ባህሪ የተላበሰችበት |
| 5. አንቀጽ አምስት | ሠ.ፈጠራዊ ስራዎች ስለመካተታቸው |
| 6. አንቀጽ ስድስት | ረ. ልምድ ለማካፈል የማይሰሰትበት |
| 7. አንቀጽ ሰባት | ሰ. በተለያዩ ሀገራት ሽልማት ስለመገኘቱ |
| | ሸ. የብዙ ዓመታት አገልግሎት |
| | ቀ. ከሌላ ተሞክሮ ስለመገኘቱ |

፬. ቀጥሎ የቀረቡላችሁ ቃላት እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት ከተሰኘው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ምንባቡን መሰረት በማድረግ አገባባቸውን

በመለየት ያላቸውን አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. መተኪያ
ለ. አዳሪ
ሐ. ኬሻ
መ. ካባ
ሠ. ምሉዕ
ረ. ጭድ

፫. የአሰሳ ንባብ ስልት ባለፈው ምዕራፍ ሶስት በቀረበላችሁ ማስታወሻ መሰረት አድርጋችሁ አንድ ኢልቦለዳዊ ጽሁፍን የአሰሳ ንባብ ስልት ተከትላችሁ በማንበብ ያገኛችሁትን ሃሳብ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፬. ከተለያዩ የመረጃ ምንጮችን የአንድ ግለሰብ ግለ ታሪክ በማንበብ የምታገኙትን መረጃ በጥቅል ንባብ ስልት በቤታችሁ አንብቡ፡፡ ስታነቡ ያስደሰታችሁን፣ ያሳዘናችሁንና የታሪኩን አጠቃላይ ይዘት በተከታዩ ክፍለ ጊዜ በአጭሩ ለጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹ፡፡

## ክፍል አራት (፬) ጽሕፈት

፩. ‹‹በቃል ያለ ይረሳል በጽሁፍ ያለ ይወረሳል፡፡›› ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ይህ አባባል ምን ማለት ይመስላችኋል፡፡

### የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ

ማስታወሻ ስለሚፈልገው ርዕሰ ጉዳይ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በጽሁፍ መዝግቦ የሚያዝበት መንገድ ነው፡፡

1. ማስታዎሻ የሚያዝባቸው አጋጣሚዎች፡-
   - በምናዳምጥበት ጊዜ
   - ጉብኝት በምናደርግበት ጊዜ
   - በግል በምናነብበት ጊዜ ወዘተ.

2. ማስታወሻ ከመውሰዳችን በፊት ትኩረት የምንሰጣቸው ነጥቦች
   - ማስታሻ ወረቀትና ብዕር ወይም እርሳስ ሊኖር ይገባል፡፡

- ማስታወሻ የምንይዝበት ዓላማ ማወቅ

3. ማስታወሻ በምንይዝበት ጊዜ
   - ዋና ዋና ሃሳቦቹን በመለየት መጻፍ፤
   - በቃላት፣ በሀረግ፣ በዓረፍተ ነገር፣ በስዕል፣ በግራፍ፣ በሰንጠረዥ ሃሳብን ማስፈር
4. ማስታወሻውን ከያዝን በኋላ
   - የሃሳብ አወራረዱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ
   - የተጻፈውን ረቂቅ ሳይረሳ መከለስ /ማስተካከል/
   - መረጃ ያገኘንበትን ምንጭ በተገቢው መንገድ መጻፍ
   - ማስታወሻውን ለተገቢው ዓላማ ማዋል። ወዘተ ... ተጠቃሽ ናቸው።

፪. በተማራችሁት የማስታወሻ አያያዝ ስልት መሰረት በአካባቢያችሁ በሥራ ፈጠራ ላይ ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን በማነጋገርና ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻሁ አቅርቡ ።

፫. ወደ ቤተመጽሐፍ ሄዳችሁ አንድ አጭር ልቦለድ አንብቡና የማስታወሻ አያያዝ ስልትን በመጠቀም ማስታወሻ ያዙ። በመቀጠልም የያዛችሁትን ማስታወሻ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ክፍል አምስት (፭) ቃላት

፩. መምህራችሁ አንድ ግጥም ያነብላችኋል፤ እናተ ደግሞ ከዚህ በታች ከግጥሙ ውስጥ የወጡ ሙያዊ፣ እንግዳ /ያልተለመዱ/ ቃላትን ወዘተ... የግጥሙን አውድ መሰረት አድርጋችሁ ትርጉም ስጧቸው።

| | |
|---|---|
| ሀ. መደብር | ሠ. ፈንታ |
| ለ. ከረጢት | ረ. ዘፈን |
| ሐ. ጓዳ | ሰ. እንካ |
| መ. ማለዳ | ረ. ጫማ ሰፊ |

፪. ያዳመጣችሁትን ግጥም እና ከላይ ትርጉም የሰጣችኋቸውን ቃላት ተጠቅማችሁ የግጥሙን ሃሳብ ወደ ዝርው ቀይሩ።

፫. በተለያዩ ሶስት ሙያዎች የምንጠቀምባቸውን ዘጠኝ ሙያዊ ቃላት ለክፍል ጓደኞቻሁ በቃል አስረዱ፡፡

፬. ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. አበለ | ሠ. ቅሪት |
| ለ. ጀምበር | ረ. ባተ |
| ሐ. ባዳ | ሰ. ተወነጨፈ |
| መ. ወናፍ | ሸ. መመኪያ |
| ሠ. ቃኘ | በ. ነጠረ |

## ክፍል ስድስት (፮) ሰዋስው

፩. ገቢርና ተገቢሮ ግስ ሲባል ምን ይመስላችኋል፡፡ በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ምሳሌ በቃል ተናገሩ፡፡

### የግስ ጠባይ

የግሶችን ጠባይ በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

- ገቢር (አድራጊ) ግሶች
- ተገብሮ (ተደራጊ) ግሶች

ሀ. ገቢር (አድራጊ) ግሶች

እነዚህ ግሶች ተግባር መፈፀምን ወይም አደረገና አላደረገም የሚያመለክቱ ግሶች ሲሆኑ ተሻጋሪም ኢተሻጋሪም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተሻጋሪ ግሶች የሚባሉት ገዛ፣ ቀማ፣ ዘረፈ፣ ቀጠቀጠ ወዘተ.

ምሳሌ፡- ልጁ ስልክ ገዛ፡፡

ኢተሻጋሪ ግሶች የሚባሉት ቆመ፣ ተኛ፣ ናቀ፣ ወረደ ወዘተ.

ምሳሌ፡- ሰውዬው ከመኪና ላይ ወረደ፡፡

ለ. ተገብሮ (ተደራጊ) ግሶች

እነዚህ ግሶች ደግሞ ድርጊት ተቀባይነትን ወይም ተደረገ አልተደረገም

የሚያመለክቱ ሲሆኑ ‹‹ተ›› የተሰኘውን የተደራጊነት መነሻ ቅጥያ የሚቀበሉ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል ተገደለ፣ ተገዛ፣ ተሰቀለ፣ ተሸጠ ወዘተ. ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ለቡሔ በዓል ጮማ በሬ ተገዛ፡፡

፩. በሚከተሉት ዓረፍ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶችን ገቢር/አድራጊ/ወይም ተገብሮ /ተደራጊ/ በማለት ጻፉ፡፡

ሀ. እውቁ የማስታወቂያ ባለሙያ የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር በጥሩ ሁኔታ አስተዋወቀ፡፡

ለ. ዘሪቱ ክፍለ ሀገር ያሉ ዘመዶቿን ትናንት ተዋወቀች፡፡

ሐ. የሞኝነት ዘመናችን ተቋጭቶ በህዳሴው ብርሃን ደምቀናል፡፡

መ. አዛውንቱ በልጆች መጥፎ ተግባር ተቆጡ፡፡

ሠ. ሀገሬ ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ኮራች፡፡

፪. የሚከተሉትን ገቢር ግሶች ወደ ተገብሮ ተገብሮዎችን ደግሞ ወደ ገቢር ግስ ለውጣችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ተሰራ | መ. ረገፈች |
| ለ. መረቀ | ሠ. ቀማ |
| ሐ. አጠናቀቀ | ረ. ሳቀች |

፫. ገቢርና ተገብሮን የሚሳዩ ከስድስት ያላነሱ ግሶችን መርጣችሁ ዓረፈፍተ ነገር መስርቱ፡፡

፬. የሚከተለውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ቃላት ወደ ሂደታዊ ድርጊት በመቀየር ዓረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡ ሮጠች

ሰርካዓለም ወደ ትምህር ቤት እየሮጠች ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. በላ | መ. ተደሰተች |
| ለ. ቀመመ | ሠ. አደገች |
| ሐ. ወለወለ | ረ. አመሰገነ |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለስራ ፈጠራ የአንድ ሰው ታሪክ በማንሳት ተምራችኋል። ማዳመጥና መናገር በሚለው ክፍል ‹‹አለቃዬ ስራዬ ነው›› የሚል ምንባብ አዳምጣችሁ የምትስማሙበትንና የማትስማሙበት ሃሳብ እያነሳችሁ ተወያይታችኋል። በተጨማሪም ‹‹ስራ ፈላጊ ስራ ፈጣሪ‹‹ በሚል ርዕስ ውይይት አድርችኋል።በመቀጠልም የቀረበላችሁን ታሪክና ምሳሌ መሰረት በማድረግ አቋማችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናግራችኋል። ‹‹እውቁ የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት‹‹ በሚል ርዕስ የማንበብ ክሂላችሁን ተጠቅማችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል። ይህንንም ለማጠናከር የአሰሳ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ በመከተል የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባቸው ሃሳብ ወስዳችኋል። የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የማስታወሻ አያያዝ በሚል የቀረበውን ሃሳብ መሰረት አድርጋችሁ ማስታወሻ በመያዝ የያዛችሁትን ለጓደኞቻችሁ አቅርባችኋል።

በተጨማሪም የተለያዩ ቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ፤ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ከግጥም ውስጥ የወጡ ሙያዊ፣ እንግዳ /ያልተለመዱ/ ቃላትን ወዘተ... የግጥምን አውድ መሰረት አድርጋችሁ ትርጉም ሰጥታችኋል። ለቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርታችኋል። የግጥምን ሃሳብ ወደ ዝርው ቀይራችኋል።

ገቢርና ተገብሮ ግሶችን ተመልክታችኋ፡ ገቢር ግሶች ተግባር መፈፀምን ወይም አደረገንና አላደረገም የሚያመለክቱ ሲሆኑ ተገብሮ የሚባሉት ግሶች ደግሞ ድርጊት ተቀባይነትን ወይም ተደረገ አልተደረገም የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህን ግሶች ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር መመስረት ችላችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

፩. በስራ ፈጠራ ዓለም የምታደንቋቸውን ሰዎች በማንሳት ያደነቃችሁባቸውን ምክንያት ተናገሩ።

፪. ከኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ አንድ ታሪክ በጥልቅ የንባብ ስልት በማንበብና ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓኞቻችሁ አስረዱ።

፫. ገቢርና ተገብሮ ቃላት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ዓረፍ ነገር በመመስረት ልዩነታቸውን አስረዱ።

፬. በሚከተሉት ቃላት ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው።

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰራ | መ. ተከናወነ |
| ለ. ተጓዘ | ሠ. ወጣ |
| ሐ. መራች | ረ. አስመጣ |

፭. የተለያዩ ግጥሞችን በማንበብ የሙያ ቃላት፣ እንግዳ /ያልተለመዱ/ ቃላትን ወዘተ... በማንበብ ፍቻውን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

፮. ለሚከተሉት በ ‹‹ሀ›› ረድፍ ለሚገኙት ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከሚገኙት ቃላት በፍቺ የሚመስሏቸውን በማዛመድ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ነዋይ | ሀ. ገንዘብ |
| 2. ድንገት | ለ. ሁለት |
| 3. ሽሙጥ | ሐ. ማፌዝ |
| 4. ጥንድ | መ. መከለል |
| 5. ግርዶሽ | ሠ. ሳይታሰብ |
| | ረ. ፍቃደኛነት |

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ (?) ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ (X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አዳምጣጩ በማስረጃ መስማማቴንና አለመስማማቴን መግለጽ እችላሁ። | | | |
| 2. | ሀሳባችሁን በምክንያት በማስደገፍ ግላዊ እይታ በቃል እገልጻለሁ። | | | |
| 3. | ፅሁፍን በማንበብ ለማን እንደተጻፈ መለይት እችላለሁ። | | | |
| 4. | አንድን ጽሁፍ ለተለያየ ዓላማ በለሆሳስና በጥልቅ የማንበብ ስልትን መጠቀም እችላለሁ | | | |
| 5. | የተለያዩ አይነት የማስታወሻ አያያዝ ስልቶችን መጠቀም ማስታወሻ ፤ ዋና ሀሳብን እና የተብራራ ሀሳብን መያዝ እችላለሁ። | | | |
| 6. | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያዳመጥኩትን ንግግር ጠቃሚውን ለይቼ ማስታወሻ መያዝ እችላለሁ። | | | |
| 7. | ከፅሁፍ አውድ ውስጥ የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም እሰጣለሁ። | | | |
| 8. | በዓርፍተነገር ውስጥ ተሻጋሪ እና ኢተሻጋሪ ግሶችን ትጠቀማላችሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ የ(?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው፣ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

## አባሪዎች

### ዋቢ ጽሑፎች

ሀዲስ አለማየሁ።(1996)። ፍቅር እስከ መቃብር። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚዎች ድርጅት።

መንግስቱ ለማ። (1955)። የግጥም ጉባኤ ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

መንግስቱ ታደሰ። (2012)። ሜጋ የአማርኛ ሰውስው አጋዥ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር።

ማንኩሳ አታሚና አሳታሚ። (2009)። የጳውሎስ ኞኞ ስብስብ ስራዎች። አዲስ አበባ፣ መላ ማተሚያ ድርጅት።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ። (2007) ። ቁጥር 5 ቅጽ 11

በዓሉ ግርማ። (2010)። ከአድማስ በአሻገር። አዲስ አበባ፤ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት።

በዳግማይ ነቅዓጥበብ። (2007)። አዲስ ፲፰፻፸፱። አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

በድሉ ዋቅጅራ። (2007)። ቋንቋን በሥነጽሁፍ ማስተማር። አዲስ አበባ፣

ባዬ ይማም። (2002) ። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ብርሃኑ ለማ።(ዓ.ም ያልተጠቀሰ)። የታዋቂ የኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካና የፍቅር ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ፋርኢ ስትትሬዲን ኃ/የ/የግልማህበር።

ብርሃኑ ገ/ጻዲቅ። (2012)። አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምሪያ። አዲሰ አበባ፣ በረከት ማተሚያ ኃላ/የተ/የግ/ማ።

ብርሃኑ ገበየሁ።(2003)። የአማርኛ ሥነግጥም። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ነብይ መኮንን ። (2006)። ስውር ስፌት ። አዲስ አበባ፣ ስውር ስፌት ሕትመት። አከፋፋይ ኃ/የተ/የግ/ማህበር።

አያልነህ ሙላቱ:: (1984):: ማን ይሆን የበላ:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

አፈወርቅ ገብረየሱስ:: (1958):: ጦቢያ:: አስመራ፣

ከበደ ሚካኤል:: (1994):: የቅኔ ውበት :: አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

ከበደ ሚካኤል:: (1999):: ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ

______________ ::(1999):: ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ

ወረታው በዛብህ (ዶ/ር):: (2008):: ለራስ ማን እንደራስ የስኬታማነት የግል መርህ መውጫ ቁጥር አንድ:: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች

ኃ.የተ. የግ.ማህበር::

ዘሪሁን አስፋው:: (2002):: የስነጽሁፍ መሰረታውያን:: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ:: (2012) :: ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር 20፣ አዲስ አበባ፣ መጋቢት 16/2012ዓ.ም:: አዋጅ ቁጥር 1176/2012ዓ.ም::

ይስመዐከ ወርቁ:: (2001)::ዴርቶጋዳ:: አዲስ አበባ፣

____________::(2009) :: ዮቶድ:: አዲስ አበባ፣ ዴርቶጋዳ ማተሚያ ቤት::

ደረጀ ገብሬ:: (1996):: ተግባራዊ የጽህፈት ማስተማሪያ:: አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት::

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ:: (2012):: አማርኛ ከ9 እና10 ክፍል:: አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት::

ደበበ ሰይፉ:: (1980):: የብርሃን ፍቅር:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ዘሳታሚ ድርጅት::

ዳኛቸው ወርቁ:: (1962) :: አደፍርስ:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ጌታሁን አማረ። (1989) ። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀለሳል አቀራረብ። አዲሰ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ጌታቸው በለጠ።(2004)።የጥበባት ጉባኤ።አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጳውሎስ ኞኞ። (1955)። በአንድነት ለአንድ ዓላማ እንሰለፍ ። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ድምፅ።ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የግ.ማህበር።

ፍጹም ወ/ማርያም።(2005)። ያልተዘመረላቸው፣ ቅፅ2:: አዲስአበባ፣ ፋርኢ ስትትሬዲን ኃ/የ/የግልማህበር።

### ሙዳየ ቃላት

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ሀመልማል | ልምላሜ፣ አረንጓዴነት |
| ሁዳድ | ሠፊ፣ የእርሻ ቦታ |
| ህላዌ | በህይወት መኖር |
| ህቡዕ | ስውር፣ ድብቅ |
| ለዛ | ውበት፣ ወዝ |
| ልጨኛ | ቁም ነገረኛ |
| መረን | ልቅ፣ ስድ፣ ባለጌ |
| መርህ | መመሪያ |
| መቋደሻ | ቁርስ፣ የዶሮ ብልት |
| መግነጢስ | የስበት ኃይል |
| ምንዝር | አለቃ ያልሆነ፣ የበታች ሰራተኛ |
| ሽፈጠ | ከዳ፣ ካደ፣ ዋሸ |
| ቁርሾ | ቂም |
| ባይተዋር | እንግዳ |
| ባድማ | ጠፍ፣ ወና፣ ባዶ ቦታ |
| ነቁጥ | ነጥብ (አንድ ነጥብ)፣ ምልክት |

| | |
|---|---|
| ነቂስ | ሁሉ /በሙሉ/ |
| ነውጥ | ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ሽብር |
| ነጻብራቅ | ብልጭልጭታ፣ አንድን ሁኔታ |
| አሜኬላ | እሾህ |
| አምበልጋ | ፈሪ፣ ቡከን |
| ወርች | ጡንቻ፣ የፊት እግር እጅ |
| ዚቀኛ | ተረበኛ፣ ተረብ አዋቂ |
| ዝሃ | ድር |
| ጓጓ | ተመኘ |
| ጥሪት | ሀብት |
| ጦስ | ሰበብ፣ ምክንያት |

## ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| ሁሉ አማረሽ | ያየችውን ሁሉ የምትከጅል |
| ሂያጅ | አመንዝራ |
| ሐረግ መዘዘ | ዘር ቆጠረ |
| ልበ ሙት | ሰነፍ |
| ልጓም አጥባቂ | ፈሪ፣ ቡከን፣ አምበል |
| መሬት ላሰ | ተለማመጠ |
| ሰኔና ሰኞ | ድንገተኛ አጋጣሚ |
| ሰው ሆነ | ራሱን ቻለ |
| ስመ ጥሩ | ዝነኛ |
| ቅቤ አንጓች | እወደድ ባይ፣ አስመሳይ |
| ቆርጦ ቀጥል | ቀጣፊ |
| በደረቁ ላጨ | አታለለ |

| | |
|---|---|
| ባዝራ | ሴት ፈረስ |
| ብው አለ | ተናደደ |
| አመድ አፋሽ | ሰጥቶ የማይመሰገን |
| አሚን ሚስት | የህግ ሚስት |
| አራስ ነብር | ኃይለኛ ሰው፣ ቁጡ |
| አርቆ አሳቢ | አስተዋይ |
| አናዘዘው | በግድ አናገረው |
| አንገተ ሰባራ | ዓይናፋር |
| አድሮ ቃሪያ | የማይሻሻል |
| አጉራ ዘለል | ባለጌ |
| አጉራ ጠናኝ | ጭብጥህ ጠነከረብኝ |
| አግድም አደግ | ያልተቀጣ፣ ባለጌ |
| እንባ ጠባቂ | ተቆርቋሪ |
| እንፉጭ | ሞኝ ሰው |
| እግረ ነጭ | ገደቢስ |
| ወረተኛ | ጊዜ አይቶ የሚከዳ፣የጊዜ ወዳጅ |
| የቀለም ቀንድ | ሊቅ፣ አዋቂ፣ |
| የአህያ ምላስ | ተንኮለኛ፣ ሞገደኛ |
| የአዞ እንባ | የውሸት ሀዘን |
| የዛር በቅሎ | ቀዥቃዣ |
| የግንባር ስጋ | ግልፅ |
| የጥርስ ስጋ | ነዝናዣ፣ ጨቅጫቃ |
| ጅራቱን ይቆላል | ይለማመጣል |
| ግድ የለሽ | ቸልተኛ |
| ጥቁር እንግዳ | መጥቶ የማያውቅ ወዳጅ |

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩___1 | ፲፩___11 | ፴___30 | ፻፲ ___110 | ፳፻ __2000 | ፲፻፻_100,000 |
| ፪___2 | ፲፪___12 | ፵___40 | ፪፻ ___200 | ፴፻__3000 | ፳፻፻ _200.000 |
| ፫___3 | ፲፫___13 | ፶___50 | ፫፻ ___300 | ፵፻___4000 | ፴፻፻_300.000 |
| ፬___4 | ፲፬___14 | ፷___60 | ፬፻ ___400 | ፶፻___5000 | ፵፻፻__400,000 |
| ፭___5 | ፲፭___15 | ፸___70 | ፭፻ ___500 | ፷፻___6000 | ፶፻፻__500,000 |
| ፮___6 | ፲፮___16 | ፹___80 | ፮፻ ___600 | ፸፻___7000 | ፷፻፻__600,000 |
| ፯___7 | ፲፯___17 | ፺___90 | ፯፻ ___700 | ፹፻ __8000 | ፸፻፻__700,000 |
| ፰___8 | ፲፰___18 | ፻ ___100 | ፰፻ ___800 | ፺፻___9000 | ፹፻፻__800,000 |
| ፱___9 | ፲፱___19 | ፻፩___101 | ፱፻ ___900 | ፻፻_10,000 | ፺፻፻__900,000 |
| ፲___10 | ፳ ___20 | ፻፪___102 | ፲፻___1000 | ፪፻፻_20,000 | ፻፻፻_1,000,000 |

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግእዝ | ካዕብ | ሳልስ | ራብዕ | ሓምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

አስረኛ ክፍል

የተማሪ መጽሐፍ